# የሆሣዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር ጥናት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም. ኤ. ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ

ዑመር ዳውድ
ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል


# የሆሣዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር ጥናት


በ

ዑመር ዳውድ

ቋንቋ ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል


የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምስጋና ........................................ i

የሰንጠረዥ ማውጫ ........................................ ii

አጠቃሎ ........................................ iii

ምዕራፍ አንድ ........................................ 1

መግቢያ ........................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2. የጥናቱ ዓላማ ........................................ 3

1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት ........................................ 4

1.4. የጥናቱ ወሰን ........................................ 4

ምዕራፍ ሁለት ........................................ 5

ክለሳ ድርሳናት ........................................ 5

2.1.የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ ........................................ 5

2.1.1. ታሪካዊ ዳራ ........................................ 5

2.1.2. የንዑስ ቡድን ማስተማር ምንነት ........................................ 6

2.1.3. የንዑስ ቡድን ማስተማር ጠቀሜታ ........................................ 6

2.1.4. በንዑስ ቡድን ማስተማር ዙሪያ የሚነሱ ችግሮች ........................................ 8

2.2. በንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደት የመምህራን ተግባራት ........................................ 9

2.2.1. ለንዑስ ቡድን ማስተማር መዘጋጀት ........................................ 10

2.2.2. ቡድኖችንና የመማሪያ ክፍልን ማደራጀት ........................................ 14

2.2.2.1. ቡድኖችን ማደራጀት ........................................ 14

2.2.2.2. የመማሪያ ክፍልን ማደራጀት ........................................ 18

2.2.3. የቡድን ዓላማንና የቡድን ስራን ግልፅ አድርጎ ማቅረብ ........................................ 19

2.2.4. የቡድን ስራዎችን መከታተል ........................................ 23

2.2.5. የቡድን ስራዎችን መገምገም ........................................ 26

2.2.6. የንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደት ላይ ዕብረቃ (Reflection)ማካሄድ ........................................ 29

2.2.7 የክለሳ ድርሳናት ሃሳቦች ማጠቃለያ ........................................ 31

ምዕራፍ ሶስት ........................................................................................................ 33

የአጠናን ዘዴ ........................................................................................................ 33

3.1. የተጠኚዎች አመራረጥ ........................................................................................ 33

3.1.1. የኮሌጁ አመራረጥ ........................................................................................ 33

3.1.2. የተጠኚ መምህራን አመራረጥ ........................................................................ 33

3.1.3. የተማሪዎች አመራረጥ ........................................................................................ 33

3.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ........................................................................................ 34

3.2.1. ቃለመጠይቅ ........................................................................................................ 34

3.2.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ ........................................................................................ 35

3.2.3. የፅሁፍ መጠይቅ ........................................................................................ 36

3.3. የጥናቱ መረጃ አተናተን ........................................................................................ 37

ምዕራፍ አራት ........................................................................................................ 38

የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ ........................................................................................ 38

4.1. የመረጃ ትንተና ........................................................................................................ 38

4.1.1. ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ምላሽ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................ 38

4.1.1.1. የመምህራኑ ግላዊ መረጃ ........................................................................................ 38

4.1.1.2. የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ የማድረግ መንስዔ ........................................ 38

4.1.1.3. የመምህራኑ የንዑስ ቡድን ማስተማር ዝግጅት ........................................................ 40

4.1.1.4. መምህራኑ ቡድኖችንና የመማሪያ ክፍሎችን የሚያደራጁባቸው መንገዶች 40

4.1.1.5. የንዑስ ቡድን መማር አላማንና የቡድን ስራን የመግለጽ ሁኔታ ........................ 43

4.1.1.6. የመምህራኑ የቡድን ስራ ክትትል ........................................................................ 45

4.1.1.7. የመምህራኑ የቡድን ስራዎች ግምገማና ውጤት አሰጣጥ ........................................ 48

4.1.1.8. የንዑስ ቡድን ማስተማር ዕብረቃን የማካሄድ ሁኔታ ........................................ 50

4.1.2. ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................................ 52

4.1.2.1. የቡድኖችና የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት ........................................................ 52

4.1.2.2. የቡድን ስራን ግልፅ የማድረግ ሁኔታ ........................................................ 54

4.1.2.3. የክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትል ........................................................ 54

4.1.3. ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................................................ 56

4.1.3.1. የቡድኖችና የክፍሎች አደረጃጀትን በተመለከተ ከመጠይቆቹ የተገኘ መረጃ.56

4.1.3.2. የቡድን ስራ አላማና የቡድን ስራ ገለፃ ..... 59
4.1.3.3. የቡድን ስራ ክትትል ..... 61
4.1.3.4. የቡድን ስራ ግምገማና ውጤት አሰጣጥ ..... 64
4.1.3.5. የቡድን መማር ዕብረቃ ..... 66
4.2. ማብራሪያ (Discussion) ..... 66
ምዕራፍ አምስት ..... 73
ማጠቃለያና አስተያየት ..... 73
5.1. ማጠቃለያ ..... 73
5.2. አስተያየት ..... 75
ዋቢ መፅሐፍት ..... 77
አባሪዎች

# ምስጋና

አማካሪዬ አቶ ጌታቸው እንዳላማው (ረዳት ፕሮፌሰር) እያንዳንዱን የጥናት ክፍል በትኩረት በመመልከት፣ እርማትና አስተያየታቸውንም ሳያዘገዩ ወዲያው ወዲያው በመስጠት ላደረጉልኝ እገዛ ከልብ ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡ እንዲሁም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጥናቱን ወጪ ስለሸፈነልኝ አመሰግናለሁ፡፡

የሆሣዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሠረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራንና ተማሪዎች ለጥናቱ መረጃ በመስጠት፣ አቶ ቦጋለ ኃይሌ፣ አቶ ተስፋ አከለ እና አቶ አንለይ አዳነ የመጠይቅና የቃለመጠይቅ ጥያቄዎችን በመገምገምና አስተያየት በመስጠት፣ ወይዘሪት ንብረት ኃይሉ የጥናት ፅሁፉን በኮምፒዩተር በመፃፍ ሁሉም ስላደረጉልኝ ትብብር ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

# የሰንጠረዥ ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ሰንጠረዥ አንድ: የመምህራኑ ግላዊ መረጃ ........................................ 38

ሰንጠረዥ ሁለት: ስለ ቡድኖችና ክፍሎች አደረጃጀት ከምልከታ
የተገኘ መረጃ ........................................ 52

ሰንጠረዥ ሶስት: የቡድን ስራዎቹን ግልፅ ማድረግን በተመለከተ ከምልከታ
የተገኘ መረጃ ........................................ 54

ሰንጠረዥ አራት:- ስለ ክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትል ከምልከታ
የተገኘ መረጃ ........................................ 54

ሰንጠረዥ አምስት: የቡድን አቀማመጥን በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ
የተገኘ መረጃ ........................................ 58

ሰንጠረዥ ስድስት: የቡድን ስራ አላማና የቡድን ስራ ገለፃን በተመለከተ፣
ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........................................ 59

ሰንጠረዥ ሰባት: የመምህራኑን የክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትልን
በተመለከተ የተማሪዎች መጠይቅ መረጃ ........................................ 61

ሰንጠረዥ ስምንት: ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎች ክትትልን
በተመለከተ የተማሪዎች መጠይቅ መረጃ ........................................ 62

ሰንጠረዥ ዘጠኝ:- የቡድን ሰራ ግምገማና ውጤት አሰጣጥን በተመለከተ
ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........................................ 64

ሰንጠረዥ አስር:- የቡድን መማር ዕብረታ ማካሄድን በተመለከተ
ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........................................ 66

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራንን የንዑስ ቡድን ማስተማር አተገባበር ማጥናት ነው። ጥናቱ ገላጭ ምርምር ሲሆን ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችም ለመምህራኑ ቃለመጠይቅ በማድረግ፣ የክፍል ምልከታን በማካሄድና ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ በማድረግ ተሰብስቧል። በመረጃ ስብሰባው ወቅት የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅጽ፣ መቅረፀ ድምፅ፣ መቅረፀ ምስልና ፎቶግራፍ ማንሳትን በመጠቀም የተሟላ መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ተደርጓል። መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በተለያዩ ጭብጦችና ንዑሳን ጭብጦች ተደራጅተው በዓይነታዊ ምርምር አተናተን ዘዴ ትንተና ተካሂዶባቸዋል። የትንተና ውጤቶቹም፣ የመምህራኑ የንዑስ ቡድን ማስተማር አተገባበር ምሁራን ከሚያነሷቸው ሀሳቦች አንፃር ሲታዩ በቂ ዝግጅት የማይደረግባቸው፣ በአብዛኛው ተገቢ የቡድን አደረጃጀት ስልትን የማይከተሉ፣ ተማሪዎችን ስለቡድን መማር ዓላማም ሆነ ተባብሮ መስራት ስለሚቻልበት ሁኔታ የማያስተዋውቁ፣ ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎች ክትትልን ቸል ያሉ፣ በአብዛኛው የቡድን ስራዎችን በተገቢው መንገድ የማይገመግሙና የቡድን ማስተማር ፅብረቃ (Teaching Reflection) የማይካሄድባቸው እንደሆኑ አሳይተዋል። በሌላ በኩል ግን፣ ከቡድን መማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት፣ ከክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትልና የቡድን ስራን ግልፅ አድርጎ ከማቅረብ አኳያ፣ በአብዛኛው ምሁራኑ ከሚያነሷቸው ሀሳቦች ጋር የሚጣጣሙና አዎንታዊ ገጽታ ያላቸው መሆናቸውን የትንተና ውጤቶቹ አመልክተዋል። በጥናቱ መጨረሻ፣ ከነዚህ የጥናት ውጤቶች በመነሳትም፣ ኮሌጁም ሆነ መምህራኑ ወደፊት ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አጥኚው የራሱን አስተያየት አቅርቧል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በመማር ማስተማር ሂደት ንቁ መማርን ያስገኛሉ ከሚባሉ ስነ-ዘዴዎች አንዱ፣ የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ ነው (Garifield 1993)፡፡ በዚህ ዘዴ ተማሪዎች፣ አንድን ስራ እርስ በርስ እየተረዳዱና እየተወያዩ በመስራት እንዲማሩ ይደረጋል (Ur 1996)፡፡

ይህ የማስተማሪያ ዘዴ፣ በርካታ የስነ-ትምህርትና የስነ-ልቦና ትውፊቶችን መሰረት ያደረገ ነው (Sharan 1990)፡፡ ዘዴው የተማሪና የትምህርት ተቋማትን ግንኙነት በማጠናከር፣ የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት በማሳደግ፣ የትምህርት ውጤት እንዲሻሻል፣ የተግባቦት ክሂሎት እንዲዳብር፣ በጋራ የመስራት ባህል እንዲጎለብት፣ ለአንድ የትምህርት አይነት ጥሩ አመለካከት እንዲኖር በማገዝና የመማር ተነሳሽነትን በማሳደግ ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ እንዳለው የምርምር ውጤቶች ያስረዳሉ (McKeachie 1998)፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትም ሆኑ ሌሎች የንዑስ ቡድን ማስተማር ትምህርታዊም ሆኑ ማህበራዊ ጠቀሜታዎች ሊገኙ የሚችሉት ግን፣ መምህራን በዘዴው በትክክል ማስተማር ሲችሉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እንደሚገመተው ቀላል አለመሆኑን Matiru, et al (1995፣198):

> *የንዑስ ቡድን ማስተማር ከምንገምተው በላይ ውስብስብና ፈታኝ ነው፡፡ ምክንያቱም፣ በየጊዜው ከሁኔታዎች ጋር ማስማማትና ማለዋወጥን፣ ከፍተኛ የማስተባበርና ግንኙነት የመፍጠር ብቃትን፣ እንዲሁም ከፍተኛ የማቀድ ችሎታንና የማቀናጀት ብቃትን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ፣ ለትምህርቱ ስኬት ከሌሎች ዘዴዎች በተለየ ሁኔታ በንዑስ ቡድን ማስተማር ወቅት የመምህሩ ብቃት ወሳኝ ነው፡፡...*

በማለት ይገልፃሉ፡፡

ይሁን እንጂ፣ በርካታ መምህራን የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴን በሚገባ የመተግበር ችግሮች ይታይባቸዋል (Chilver 1990)፡፡ የንዑስ ቡድን ማስተማር፣ "መምህር ብቸኛ የዕውቀት ምንጭ ነው" ከሚል አመለካከት መላቀቅንና ሚናው "የተማሪዎች የመማር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው" የሚል አመለካከት ማዳበርን ይጠይቃል፡፡ አንዳንድ መምህራን ግን፣ ይህ ከቀጥተኛ ዕውቀት አስተላላፊነት ወደ የመማር ሁኔታ አመቻችነት መቀየርን፣ በክፍል ውስጥ ያላቸውን

የበላይነት እንደመነጠቅ አድርገው ይመለከቱታል በማለት Exley and Dennick (2004) ችግሩ የአመለካከት ጭምር መሆኑን ይገልፃሉ::

በብዙዎቹ የአፍሪካ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም በመምህራን ዘንድ ፣ የንዑስ ቡድን ማስተማርን ጨምሮ፣ ሌሎች የተማሪ ተኮር ዘዴዎችን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ፣ የጎሉ ችግሮች እንዳሉ Matiru et al (1995) ይጠቁማሉ:: Graan (1999:60)ም "በርካታ መምህራን፣ የተማሪ ተኮር አቀራረብን ተግባራዊ የማድረግ ፍላጎት ይታይባቸዋል:: ይሁን እንጂ፣ ብዙዎቹ ስለተማሪ ተኮር አቀራረብ ምንነትም ሆነ የክፍል ውስጥ አተገባበር ስልቶች የጠለቀ ዕውቀትና ክሂሎት የላቸውም" በማለት አሳሳቢነቱን ይገልፃሉ::

በኢትዮጵያ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ውስጥም፣ ተማሪ ተኮር ዘዴን ተግባራዊ የማድረግ ችግሮች አሉ:: የየኮሌጆቹ መምህራን የሚያስተምሩበት ዘዴ፣ በአብዛኛው መምህር ተኮር አቀራረብን መሰረት ያደረገ ነው:: ይህ ደግሞ፣ ወደፊት በየትምህርት ቤቶች በመምህርነት ለሚሰማሩት እጩ መምህራን ጥሩ ምሳሌ (Model) የሚሆን አይደለም:: ስለዚህ፣ የየኮሌጁ መምህራን አሰልጣኞችን ከተማሪ ተኮር አቀራረብ ጋር የሚያስተዋውቅ ልዩ ስልጠና ያስፈልጋል (Livingston et al 2002)::

ከላይ በቀረበው የመፍትሄ ሀሳብ መሰረት፣ ከ2003 (1996 ዓ.ም) ጀምሮ፣ በተለይ ለመምህራን አሰልጣኞች፣ በማስተማር ስነ-ዘዴ ላይ ያተኮረ የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም (Higher Diploma Program-HDP) በመሰጠት ላይ ይገኛል::

ይሁን እንጂ፣ አሁንም ቢሆን የተማሪ ተኮር ስነ-ዘዴን ተግራዊ በማድረግ ረገድ ችግሮች እንዳሉ አንዳንድ ጥናቶች ይጠቁማሉ:: በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር፣ የቡድን መማርን ጨምሮ አጠቃላይ ተማሪ ተኮር አተገባበርን በተመለከተ በሙሉጌታ (1996 ዓ.ም.) በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ እንዲሁም በኤልያስ (1997ዓ.ም.) በአዳማና ሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጆች የተደረጉትን ጥናቶች ለአብነት መጥቀስ ይቻላል::

የሙሉጌታ (1996 ዓ.ም.) ጥናት ውጤት፣ የኮሌጁ አማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ተማሪ ተኮር በሆነ አቀራረብ ትምህርቱን ለማቅረብ ሙከራ እንደሚያደርጉ፣ ይሁን እንጂ፣ ካሉት በርካታ የተማሪ ተኮር ዘዴዎች በጥቂቶቹ ላይ ብቻ እንደተወሰኑ፣ በተጨማሪም፣ መርሃ ትምህርቱ

ለተማሪ ተኮር አተገባበር አመቺ እንዳልሆነና ተማሪዎቹም ቢሆኑ በዘዴው ለመማር ዝግጁ እንዳልሆኑ ይገልፃል:: የኤልያስ (1997 ዓ.ም.) የጥናት ውጤት ደግሞ፣ ሁለቱም ኮሌጆች በተማሪ ተኮር ዘዴ እንደሚያስተምሩ፣ ነገር ግን፣ ከተማሪዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች፣ ተማሪዎች መልሱን እንዲሞክሩ ያለማድረግ፣ መምህራኑ ሰፊ የንግግር ጊዜን የመውሰድና በሞጁዩል ዝግጅት ተማሪዎችን ያለመሳተፍ ችግሮች እንዳሉ ያመለክታል::

በውጭ ቋንቋዎች ትምህርት ክፍል፣ የመምህራንን የንዑስ ቡድን ማስተማር አተገባበርን አስመልክተው የተደረጉ ጥናቶችም፣ ችግሮች እንዳሉ ይጠቁማሉ:: Birhanu G/Michael (2000) መምህራኑ ትብብራዊ የመማር ዘዴን በብዛት እንደማይጠቀሙ፣ ቢጠቀሙም አተገባበራቸው ችግሮች ያሉበት መሆኑን ይገልፃሉ:: Girma Gezahegn (2003) አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን በሀገራችን የክፍል ሁኔታ፣ የቡድን መማርን ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪና ውጤት አልባ ነው ብለው እንደሚገምቱ፣ ይህም ግምታቸው፣ በአብዛኛው ስለ ቡድን ስራ ካላቸው ግንዛቤና ክሂሎት ማነስ የመነጨ ሊሆን እንደሚችል ይገልፃሉ:: Zeleke Teshome (2006) የ2ኛ ደረጃ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የቡድን ስራ አመራር፣ በርካታ ችግሮች ያሉበት መሆኑን ያስረዳሉ::

እነዚህ በቡድን ማስተማር ዙሪያ በመምህራን ዘንድ የታዩ የአመለካከትና የአተገባበር ችግሮች ተጨማሪ ጥናትን የሚጋብዙ ናቸው:: በተለይ ደግሞ፣ የአማርኛ መምህራን ስለ ቡድን ስራ ያላቸውን የአመለካከትም ሆነ የአተገባበር ሁኔታ አስመልክቶ የተደረገ ጥናት አጥኚው አለማግኘቱ፣ ይህንን ጥናት ለማጥናት ዋነኛ ምክንያት ሆኖታል:: በተጨማሪም አጥኚው በሆሣዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በቆየባቸው ሶስት አመታት ያስተዋላቸው ሁኔታዎች፣ በቡድን ማስተማር ዙሪያ (የቡድን ስራን በመስጠት፣ ስራዎቹን በመከታተል፣ በመገምገም ወዘተ.) ችግሮች እንዳሉ የሚያሳዩ ነበሩ:: ይህም በጥናቱ እንዲገፋበት ተጨማሪ ምክንያት ሆኖታል::

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፣ የሆሣዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን፣ የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴን በተገቢው መንገድ ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጋቸውን ማጥናት ነው::

ይህን አጠቃላይ ዓላማ መሰረት አድርጎ የተነሳው ይህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

1. መምህራኑ በንዑስ ቡድን ለማስተማር በምን አይነት ቅድመ ዝግጅትን ያደርጋሉ?
2. የንዑስ ቡድኖችንና ክፍሎችን እንዴት ያደራጃሉ?
3. የቡድን ስራ ዓላማንና የቡድን ስራዎችን ለተማሪዎቻቸው ያስረዳሉ?
4. የንዑስ ቡድኖች ስራዎች ክትትላቸው ምን ይመስላል?
5. የንዑስ ቡድን ስራዎችንና የንዑስ ቡድን መማር ሂደትን በሚገባ ይገመግማሉ?

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል::

- የሆሣዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሠረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን በንዑስ ቡድን ማስተማር በመዘጋጀት፣ የንዑስ ቡድኖችንና የቡድን መማሪያ ክፍሎችን በማደራጀት፣ የንዑስ ቡድን መማር ዓላማንና የንዑስ ቡድን ስራዎችን በማስረዳት የንዑስ ቡድን ስራዎችን በመከታተል፣ የንዑስ ቡድን ስራዎችን በመገምገምና የንዑስ ቡደን ማስተማ ዕብረቃን በማካሔድ ረገድ ያሏቸውን ጠንካራ ጎኖችና ያሉባቸውን ችግሮች እንዲለዩ ይረዳቸዋል::
- በንዑስ ቡድን ማስተማር ዙሪያ፣ ወደፊት ጥናት ማድረግ ለሚሹ መነሻ ሃሳብን ይሰጣል::

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በሆሣዕና ከተማ በሚገኘው የሆሣዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ነው:: የጥናቱ ትኩረትም በ2000 ዓ.ም በኮሌጅ እየተሰጠ በሚገኘው የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ፣ መምህራን በሚያከናውኑት የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር ላይ ነው:: ይህ የተጠቀሰው ኮርስ በቀን /በመደበኛው/ እንዲሁም በማታው ፕሮግራም የሚሰጥ ቢሆንም ጥናቱ የሚያተኩረው ግን በመደበኛ ፕሮግራም በሚሰጠው ላይ ብቻ ነው:: ተማሪዎች የቡድን ስራዎችን የሚሰሩት ወይም መምህራን ተማሪዎችን በቡድን ሆነው እንዲማሩ የሚያደርጉት በክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከክፍል ውጭም ጭምር ነው:: ይህ ጥናት የሁለቱንም አተገባበር ይመለከታል::

## ምዕራፍ ሁለት
## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1.የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ

#### 2.1.1. ታሪካዊ ዳራ

ከተማሪ ተኮር ዘዴዎች አንዱ የሆነው የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ እየታወቀ መሄድ የጀመረው እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ1930 ጀምሮ እንደሆነ Brumfit (1984) Cortis (1971:1)ን ጠቅሰው ያስረዳሉ:: ለዘዴው መጀመር አስተዋጽኦ ካደረጉት መካከል፣ John Dewey የተባሉ አሜሪካዊ የትምህርት ፈላስፋ በ1916 ያቀረቡት ፍልስፍና ዋና ተጠቃሽ መሆኑንም ጨምረው ይገልፃሉ::

Dewey፣ ትምህርት የተማሪውን ውስጣዊ ፍላጎት መሰረት አድርጎ መነሳትና ፍላጎቱንም ተከትሎ መገንባት እንዳለበት፤ በዚህ ሂደትም የመምህሩ ሚና ዕውቀትን ማስተላለፍ ሳይሆን፣ የተማሪውን የመማር ሁኔታ ማመቻቸት መሆን እንደሚገባው መግለፃቸውን Exley and Dennick (2004) ያስረዳሉ:: ከዚህ የ“Dewey” ፍልስፍና በተጨማሪ በቡድን መስራት በተለያዩ የስራ መስኮች ውጤታማ ሆኖ መገኘቱም የትምህርት ባለሙያዎች ትኩረት እንዲሰጡትና ለማስተማሪያ ዘዴነት እንዲያውሉት አድርጓቸዋል (Sharan 1990):: እኚሁ ምሁር ጨምረው እንደሚያስረዱት በአሁኑ ሰዓት ለትምህርት ተግባር የምናውለውና ትብብራዊ ቡድን (Cooperative Group) በመባል የሚታወቀው የቡድን መማር፣ ከ “Dewey” የትምህርት ፍልስፍና በተጨማሪ፣ የቡድን አባላት ግንኙነት ሂደት ትውረትን (Group Dynamics Theory)፣ የኮንስትራክቲቪዝም ትውረትንና የውስጣዊ ተነሳሶት ትውረትን (Intrinsic Motivation Theory) መሰረት ያደረገ ነው::

ይህ የቡድን መማር ዘዴ በተለይ ባለፉት ሶስት አስርት አመታት ውስጥ በማህበራዊ ግንኙነት(social relationships)፣ በቡድን አባላት የእርስ በርስ ግንኙነት ሂደት (Group Dynamics)፣ እንዲሁም በመማር-ማስተማር ዙሪያ በተደረጉ ትውረታዊ ምርምሮች (theoretical researches) እና ተግባራዊ ምርምሮች (applied researches) እየዳበረ ለመሄድ ችሏል (Antil. et al. 1998)::

### 2.1.2. የንዑስ ቡድን ማስተማር ምንነት

Billson (1986፣143) Mills (1967፣ 2)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት ንዑስ ቡድን ማለት፡

> *ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች ችግር መፍታት፣ የተሻለ ነገርን መፍጠር፣ አስደሳች ሁኔታን መፍጠር ወዘተ. የመሳሰሉትን ግቦች ግቦቻቸው አድርገው፣ በተወሰነ አጀንዳ ዙሪያ ፊት ለፊት መተያየት በሚችሉበት ሁኔታ የሚሰበሰቡበት ሂደት ነው:: እያንዳንዱ ተሳታፊም ከሂደቱ ውጤት ተጠቃሚ ወይም ተጎጂ መሆኑን አውቆ በኃላፊነት ስሜት የሚሳተፍበትም ነው:: በእርስ በርስ ግንኙነቱም የተሻለ መቀራረብን ለመፍጠር የሚያስችል፣ ንዑስ ቡድኑ በሚኖሩት የተለያዩ ሚናዎችም እኩል ተሳታፊ የመሆን እድልን የሚያስገኝ ነው:: ንዑስ ቡድን ብዙውን ጊዜ አንድ መደበኛ መሪ ያለው ሲሆን በሂደት ሌሎቹ የቡድኑ አባላትም የመሪነቱን ዕድል የሚያገኙበት ነው::*

የንዑስ ቡድን ማስተማር (Small Group Teaching) ሲባልም፣ በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን፣ አነስተኛ የተማሪዎች ቁጥር ባላቸው የተለያዩ ንዑሳን ቡድኖች አደራጅቶ፣ ተማሪዎቹ እርስ በርስ እየተረዳዱ እንዲማሩ ማድረግ ነው (Bejarno 1987):: በተመሳሳይም እንደ Lou, et al (1996፣ 425) ገለፃ "የንዑስ ቡድን ማስተማር ማለት የአንድ ክፍል ተማሪዎች፣ በተለያዩ ንዑሳን ቡድኖች ተደራጅተው እንዲማሩ ማድረግ ነው ..."

### 2.1.3. የንዑስ ቡድን ማስተማር ጠቀሜታ

የንዑስ ቡድን ማስተማር ዓላማ ንቁ መማርን (Active learning) መፍጠር ነው (Garfield 1993):: አሁን ላለንበትና በአንድ ክፍል ውስጥ ብዙ የተማሪዎች ስብጥር ለሚገኝበት ሁኔታ፣ እንደ ሌክቸር ዘዴ ያለውን ጥንታዊ የማስተማር ዘዴን ብቻ መጠቀሙ በቂ አለመሆኑንና እንደ ንዑስ ቡድን ማስተማር ያሉ አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ በመማር ማስተማር ሂደት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን Putnam (1997) የስረዳሉ:: Davis (1993፣1) በበኩላቸው:

> *ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የሚማሩት በሂደቱ ላይ ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ ነው:: የጥናት ውጤቶች እንደሚያመለክቱት፣ ተማሪዎች የአንድን ትምህርት ይዘት በቡድን ሆነው ሲማሩ የሚኖራቸው የመረዳትና የማስታወስ ችሎታ፣ ያንኑ ይዘት በሌሎች በማናቸውም ዘዴዎች ቢማሩ ከሚኖራቸው የመረዳትና የማስታወስ ችሎታ የላቀ ነው::*

በማለት የቡድን መማር አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት ይገልፃሉ:: Exley and Dennick (2004፣ 4-5) Entwistle et al (1992፣ 41)ን ዋቢ በማድረግ የንዑስ ቡድን ማስተማር በጥንቃቄ ከታቀደና ተግባራዊ ከሆነ ለተማሪዎች ሊያስገኝ የሚችላቸውን ጠቀሜታዎች እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ::

- ተማሪዎች ተባብረውና ተደጋግፈው በመስራት ልምዳቸውን ይለዋወጣሉ::
- በጥልቀት ማሰብንና ችግሮችን መፍታትን፣ ለምሳሌ:- መተንተንን፣ መገምገምን፣ ማስረጃ ማቅረብን፣ ተጠየቃዊ ምክንያት መስጠትንና ሃሳቦችን ማዛመድን በማጎልበት የዕውቀትና የሙያ ችሎታቸውን ያዳብራሉ::
- ለውይይት በሚቀርቡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ፣ ማብራሪያ በመስጠት፣ በማዳመጥና በመጠየቅ የተግባቦት ችሎታቸውን ያዳብራሉ::
- በሚደረጉ ክርክሮችና ውይይቶች ተሳታፊ በመሆን፣ ዕሴቶቻቸውንና አመለካከቶቻቸውን ይገመግማሉ፤ ስለራሳቸው አዎንታዊ አመለካከትንና በራስ የመተባበር መንፈስን ያዳብራሉ::
- ስለሚማሩት የሙያ ዘርፍ ከመምህሮቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር በቅርበትና በጥልቀት በመወያየት፣ የሙያውን ምንነት እንዲሁም ሙያው የሚጠይቀውን ስነ-ምግባር በበለጠ ይገነዘባሉ::
- በንዑስ ቡድን መማር ሂደት በሚቀርቡ ተግባራትና ውይይቶች እያንዳንዳቸው የስራ ድርሻና ኃላፊነት ስለሚኖራቸው፣ ኃላፊነት የመውሰድና የመወጣት ልምድን ያዳብራሉ::
- በንዑስ ቡድን መማር፣ ተማሪዎች መሪነትን ጨምሮ በቡድን ስራ ወቅት ያሉ እንደ ማቀድ፣ ማስተባበር፣ ማደራጀት፣ መቆጣጠር፣ ሌሎችን መርዳትና ማበረታታት፣ ስራ ማከፋፈልና ስራ መቆጣጠርን የመሳሰሉት ልዩ ልዩ ኃላፊነቶችን ተግባራዊ ማድረግን ይለማመዳሉ::
- ተማሪዎች በቡድን ሆነው በሚሰሩዋቸው ስራዎች ላይ የዕብረታ ተግባርን (Reflection Practice) ስለሚያካሂዱ፣ ከድክመትና ጥንካሬ ተምሮ ለወደፊት የተሻለ ዕቅድ ማቀድን ይለማመዳሉ::

የቡድን ስራ በተለይ ለቋንቋ መማር ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ Long and Porter (1985) የቡድን ስራ፣ የተማሪዎች ቋንቋን በተግባር የመጠቀም ዕድል እንደሚያሰፋ፣ የንግግር ችሎታን

እንደሚያዳብር፣ ከግለሰብ አቅም ጋር የተገናዘበ የቋንቋ መልመጃ ለመስጠት እንደሚያስችል፣ እንዲሁም ጥሩ የመማር መንፈስንና ተነሳሽነትን እንደሚፈጥር ይገልፃሉ:: ከዚሁ ጋር በተቀራረበ መልኩ Ur (1996) የንዑስ ቡድን መማር ከሰፊ ክፍል መማር አንፃር ሲታይ፣ ለተማሪዎች የንግግር ዕድልን የመፍጠር አቅሙ ከፍተኛ እንደሆነ፣ ይህም በተለይ የንግግር ችሎታን ለማዳበር የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ያስረዳሉ:: በተመሳሳይ፣Berhanu (2000) Long et al (1976)ን በመጥቀስ እንደሚገልፁት፣በንዑስ ቡድን ሆነው የሚማሩ ተማሪዎች ፣መምህር ተኮር በሆነ የክፍል ሁኔታ ውስጥ ከሚማሩ ተማሪዎች አንፃር ሲታዩ፣ በቋንቋ አፍልቆት ችሎታቸው የተሻሉ ናቸው:: Jones and Jones (2004፣124) Plex (1999)ን ጠቅሰው እንዲሚያስረዱት ደግሞ በትብብራዊ የመማር ሂደት ከቢጤዎቻቸው ጋር በመማር ራሳቸውንም ሆነ ቢጤዎቻቸውን የሚረዱ ተማሪዎች፣ በሂሳብ፣ በንባብና በቋንቋ ብቃት መለኪያ ፈተና (Standardized test) ውጤታቸው ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል::"

### 2.1.4. በንዑስ ቡድን ማስተማር ዙሪያ የሚነሱ ችግሮች

የንዑስ ቡድን ማስተማር ከላይ በዝርዝር እንደቀረበው በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ቢሆንም ከችግር ግን የፀዳ አለመሆኑን የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ:: እንደ Harmer (2006) አገላለፅ፣የንዑስ ቡድን መማር ከፍተኛ ድምፅና ጫጫታ ይኖረዋል በሚል፣ አንዳንድ መምህራን ለቁጥጥር አስቸጋሪ እንደሆነ ይገምታሉ:: አንዳንድ ተማሪዎችም ቢሆኑ፣ በቡድን መማር በግል ያገኙት የነበረውን የመምህር ትኩረት፣ ስለሚቀንስባቸው አይወዱትም:: ከዚህ በተጨማሪ፣ አንዳንድ ተማሪዎች በቡድን ስራ ተሳታፊ ላይሆኑ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ በስራው ላይ ብቸኛ ተዋናይ ሊሆኑ ይችላሉ:: ከጊዜ አንፃርም ቢሆን፣ የቡድን ስራ ጊዜ የሚፈጅ ሊሆን ይችላል:: Ur(1996፣232) በንዑስ ቡድን ለማስተማር መምህራን ያለባቸውን ስጋት በተመለከተ:

> *... መምህራን በቡደን ስራ ወቅት፣ በቡድን ስራው ሂደት በተማሪዎች በሚፈጠረው ጫጫታ የክፍል አመራሩ ከቁጥጥራችን ውጭ ሊሆን ይችላል፤ ተማሪዎችም ለትምህርት ከቀረበው ቋንቋ ይልቅ፣ በብዛት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ሊጠቀሙ ይችላሉ፤ የቡድን ስራውንም በደንብ ላይሰሩ ወይም ጭራሽ ላይሰሩ ይችላሉ የሚል ስጋት ያድርባቸዋል:: ይህም ስጋታቸው አንዳንዴ ዕውነትነት ያለው ሆኖ ይገኛል::*

በማለት ስጋት ብቻ ሳይሆን፣ በተጨባጭ ችግሮች ሲፈጠሩ እንደሚችሉ ያስገነዝባሉ:: Atkins et al (1996፣ 210)ም Woodward (1995)ን በመጥቀስ ከላይ የቀረቡትን ጨምሮ ሌሎች የቡድን መማር ሂደት ችግሮችን እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ::

ሀ. ተማሪዎች አብረዋቸው ከተመደቡ ተማሪዎች ጋር መስራትን ላይፈልጉ ይችላሉ::

ለ. አንዳንድ ቡድኖች ገና በመስራት ላይ እያሉ፣ ሌሎቹ ቡድኖች ቀድመው ስራቸውን ሊጨርሱ ይችላሉ::

ሐ. አንዳንድ ቡድኖች ደግሞ ምን መስራት እንዳለባቸው በደንብ ባለመገንዘብ ወይም በቋንቋ ችሎታ ማነስ፣ ስራውን ጨርሶ ላይሰሩ ይችላሉ::

መ. አንዳንድ ተማሪዎች ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ሳይሆን፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሊወያዩ ይችላሉ::

ሠ. አንዳንድ ተማሪዎች በቡድን ቢቀመጡም፣ ከሌሎቹ ጋር ሳይወያዩ በግላቸው ሊሰሩ ይችላሉ::

ረ. አንዳንዶቹ የቡድን ስራውን ትተው፣ ከስራው ጋር ግንኙነት የሌለውን የግል ወሬያቸውን ሊያወሩ ይችላሉ::

ሰ. አንዳንዶቹ ከተሳትፎ ራሳቸውን ሲያገሉ የተወሰኑት ደግሞ የቡድን ስራውን ብቻቸውን በበላይነት ሊቆጣጠሩ ይችላሉ::

ሸ. የትብብራዊ መማር ልምድ የሌላቸው ተማሪዎች ወደ ግጭትና ፉክክር ሊያመሩ ይችላሉ::

ቀ. በቡድን ውስጥ የሚመደቡት ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ የተለያየ ሊሆን ይችላል::

በ. ተማሪዎች በቡድን እንዲሰሩት የተሰጣቸው ስራ ላይጥማቸው ይችላል::

## 2.2. በንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደት የመምህራን ተግባራት

በንዑስ ቡድን የማስተማር ሂደት (Small Group Teaching) መምህራን የሚኖራቸው ሚና፣ በሰፊ ክፍል ማስተማር ሂደት (Large Class Teaching) ከሚኖራቸው ሚና የተለየ ነው:: በንዑስ ቡድን ማስተማር ወቅት መምህራን ሚናቸው ብቸኛ የዕውቀት ምንጭ በመሆን ዕውቀትን ወደ ተማሪው ማስተላለፍ ሳይሆን፣ ተማሪዎቹ በራሳቸው ጥረት ዕውቀታቸውን የሚያዳብሩበትን ሁኔታ መፍጠር ነው(Johnson and Johnson 1990፣ Garfield 1993፣

Thorley and Gregory 1994፣ Putnam 1997)። ይህንኑ አስመልክተው Exley and Dennick (2004፣ 32) እንደሚገልፁት፡

> *… ዘመናዊ ትምህርት ቀድሞ ከነበረው የመምህር ተኮር አቀራረብ በመራቅ የተማሪው ፍላጎት፣ ቀዳሚ ልምድና ዕውቀት ግምት ተሰጥቶት ንቁ፣ ትብብራዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ የመማር ሂደት፣ ዕውቀት ወደሚገነባበት የተማሪ ተኮር አቀራረብ አዘንብሏል። በዚህ የትምህርት ማዕቀፍ ውስጥ የመምህሩ ሚና፣ ተማሪዎች በትምህርት ሂደት ያላቸውን ባለቤትነትና ሃላፊነት አምኖ በመቀበል፣ የመማር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። የተሳካ የንዑስ ቡድን ማስተማር እንዲኖር ከተፈለገ፣ መምህሩ የዚህ አይነት አመለካከት ሊኖረው ይገባል።*

Westberg and Jason (1996) (Colling፣ Brown፣ and Newnan 1989)ን ዋቢ አድርገው እንደሚያቀርቡት ደግሞ ፣ በንዑስ ቡድን ማስተማር ወቅት መምህራን የተማሪዎችን የትምህርት ፍላጎትና ግብ መለየት፣ ለተማሪዎቹም ምሳሌ (model) ሆኖ ስራዎችን ማሳየት፣ ቀስ በቀስም ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለው የሚማሩበትን ሁኔታ በመፍጠር፣ እነሱ ሂደቱን መከታተልና መቆጣጠር ይኖርባቸዋል። ስለዚህ፣ በንዑስ ቡድን ማስተማር ወቅት የመምህራን ሚና ዕውቀት ማስተላለፍ ሳይሆን ለተማሪዎቹ የመማር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው(GDE 1999)። በማመቻቸቱ ሂደትም ያሉትን የመምህራኑን ዋና ዋና ተግባራትን በስድስት መክፈል ይቻላል። እነሱም፣ ለንዑስ ቡድን ማስተማር መዘጋጀት (Preparation) ፣ የንዑስ ቡድኖችንና ክፍሎችን ማደራጀት (Organization)፣ የንዑስ ቡድን ዓላማንና የቡድን ስራዎችን ግልፅ አድርጎ ማቅረብ (Presentation)፣ የንዑስ ቡድን ስራዎች ሂደትን መከታተል (Monitoring) ፣ የንዑስ ቡድን ስራዎችን መገምገም (Evaluation) እና የንዑስ ቡድን ማስተማር ፅብረቃ (Reflection) ማካሄድ ናቸው (Westberg and Jason 1996፣ Putnam 1997፣ Exley and Dennick 2004)።

### 2.2.1. ለንዑስ ቡድን ማስተማር መዘጋጀት

በንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደት የመጀመሪያውና ወሳኙ ተግባር በቂ ዝግጅት ማድረግ ነው (Westberg and Jason 1996፣ Putnam 1997)። ምክንያቱም Exley and Dennic (2004:13) እንደሚያስረዱት፡"…በንዑስ ቡድን ማስተማር ዙሪያ የሚከሰቱ በርካታ ችግሮችን፣ አስቀድሞ በመገመትና በቂ ዝግጅት በማድረግ እንዳይከሰቱ ማድረግ ይቻላል።"

ይሁን እንጂ፣በርካታ መምህራን የንዑስ ቡድን ማስተማርን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት፣ ለዝግጅት በቂ ትኩረትን እንደማይሰጡ Matiru et al (1995)ይገልፃሉ:: ይህ ሁኔታ ግን ትክክል እንዳልሆነ ይልቁንም፣ በንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ በተሳካ ሁኔታ ለማስተማር መምህራን በቡድን አደረጃጀት፣ በቡድን አባላት የእርስ በርስ ግንኙነት፣ በትምህርት መርጃ መሳሪያ አጠቃቀም፣ በትምህርት አቀራረብና አገማገም ሂደት ሊኖሩ የሚችሉ ውስብስብ ተግባራትን አስቀድመው መገመትና መዘጋጀት እንደሚጠበቅባቸው Thorly and Gregory (1994) ያስረዳሉ::

በነዚህ የተለያዩ የንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደቶች ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በመገመት የተሳካ የቡድን ማስተማር ዝግጅት ለማድረግ፣ የመምህራን ተቀዳሚ ተግባር የተማሪዎቹን ቀዳሚ ልምድና ወቅታዊ የትምህርት ፍላጎት ማወቅ ነው:: በሌላ አነጋገር ተማሪዎቹ ማናቸው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው:: በመሆኑም የንዑስ ቡድኖችን ከመመስረትና ተማሪዎችን በቡድን አደራጅቶ ከማስተማር በፊት፣ ስለተማሪዎቹ ማንነት ዝርዝር መረጃን መሰብሰብ ይገባል::

> *... ለተማሪዎች ጠቃሚ የሆኑ የቡድን ልምዶችን ለማቀድ፣ በቅድሚያ ለተማሪዎቹ ተገቢ ግምትና ክብር በመስጠት፣ ስለ ቀዳሚ ልምዶቻቸውና ወቅታዊ የትምህርት ፍላጎታቸው በቂ መረጃን ማግኘት አለብን:: መረጃዎቹንም፣ በቡድን ማስተማር ከመጀመራችን በፊት፣ ተማሪዎቹን በተናጠል በማነጋገር ወይም የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ በማድረግ ማግኘት ይቻላል:: ... በቡድን ማስተማር ከጀመርን በኋላም ቢሆን በየጊዜው ተማሪዎቹን የበለጠ ለማወቅ መጣር ጠቃሚ ነው (Westberg and Jason 1996:31)::*

በተጨማሪም ፣ መምህራኑ በንዑስ ቡድን ለማስተማር ሲዘጋጁ፣ በአላማ ቀረፃ ላይ ጥንቃቄ ማድረግን አስመልክተው Johnson and Johnson (1990፣ 122)::

> *የንዑስ ቡድን ማስተማር ሲታቀድ፣ በግልፅ መቀመጥ ያለባቸው ሁለት ዓላማዎች ናቸው:: አንደኛው፣ ከተማሪዎቹ የትምህርት ደረጃ ጋር የተመጣጠነ የትምህርት ዕውቀት ዓላማዎች (academic objectives) ሲሆኑ ሁለተኛው ደግሞ፣ ተማሪዎቹ እንዲያዳብሯቸው የሚጠበቁ የትብብር ክሂሎት ዓላማዎች (Cooperative Skills Objectives) ናቸው:: የብዙዎቹ መምህራን የጋራ ችግር፣ የትምህርት ዕውቀት ዓላማውን ብቻ አቅዶ የትብብር ክሂሎት ዓላማን መዘንጋት ነው::*

በማለት፣ ሁለቱም ዓላማዎች እኩል ክብደት ተሰጥቷቸው መታቀድ እንዳለባቸው ያስረዳሉ:: እነዚሁ ምሁራን በዚያው ዕሁፋቸው ገፅ 29 ላይ እንደሚያስገነዝቡት፣ "በቡድን ሆኖ እንዴት መስራት እንደሚቻል ትምህርት ካልተሰጣቸው ተማሪዎች፣ በቡድን መስራትን መጠበቅ አይቻልም::"

የትብብር (Cooperative) ወይም የማህበራዊነት (Social) ክሂሎት ሲባልም፣ አጠቃላይ የተማሪዎቹን የእርስ በርስ ግንኙነት ብቃት የሚመለከቱ፣ እንደ የንግግር ተግባቦት ፣ በንቃት የማዳመጥ ፣ የሀሳብ ልዩነትን የመቀበል ፣ ግጭት ሲፈጠር የመታገስና የመፍታት ፣ ቡድን የመምራት ፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ችሎታዎች በሙሉ ያካትታል (Tribe 1994)::

Putnam (1997:34) (Sharan and Sharan, 1992: 149)ን በመጥቀስ እንደሚገልፁት:-

> *የመማሪያ ክፍል ከማህበራዊ ሁነቶች ገለልተኛ የሆነ ቦታ አይደለም:: ይሁን እንጂ፣ ብዙ መምህራን የክፍል ማህበራዊ ገፅታ ችላ በማለት በትምህርታዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኩራሉ:: አንድ መምህር ምንም አይነት የማስተማሪያ ዘዴን ይምረጥ ዘዴው በተማሪዎች የእርስ በርስ ግንኙነቶች ላይ አንዳች ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀሬ ነው:: ግንኙነቶቹ ደግሞ በበኩላቸው ተማሪዎቹ ለትምህርት ቤትም ሆነ ለትምህርት ባላቸው አመለካከቶች ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ::*

በሌላ በኩል የንዑስ ቡድን አላማ ሲቀረጽ፣ ተማሪዎቹ በቡድን ሆነው እንዲያዳብሩት የሚፈለገው ምን እንደሆነ በግልፅ መቀመጥ አለበት:: Jaques (1989) እንደሚያስረዱት ብዙ መምህራን የንዑስ ቡድን ስራን በቡድን መወያየት ብቻ አድርገው ይገምታሉ:: በመሆኑም፣ በዕቅዳቸው ላይ "ይወያያሉ" የሚለውን የዝርዝር ዓላማ መግለጫ ብቻ ያሰፍራሉ:: ነገር ግን፣ የንዑስ ቡድን አባላት በጋራ ሲያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራት በርካታ በመሆናቸው፣ እንደ ሁኔታው "ይለያሉ"፣ "ያወዳድራሉ"፣ "ይገምታሉ"፣ "ይመርጣሉ"፣ "ያደረጃሉ"፣ ወዘተ. ተብለው መገለፅ ይኖርባቸዋል::

በንዑስ ቡድን ማስተማር ዝግጅት ወቅት፣ ሌላው ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ የቡድን ስራ ጥያቄዎች አዘገጃጀት ነው:: ተማሪዎች ከቡድን ስራ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆኑት በስራው ላይ የራሳቸውን ሃሳብ በመስጠት፣ የሌሎቹን ሃሳብና አመለካከት በማዳመጥ፣ ለቡድኑ አባላት እገዛን በማድረግና እነሱም እገዛን ሲሹ በመጠየቅ ነው:: ስለዚህ ለቡድን ስራ የሚሰጡ ተግባራት አንድ ቁርጥ ያለ ምላሽ የሌላቸው ወይም አወያይና አከራካሪ ቢሆኑ ይመረጣል

(Blumenfeld et al 1996)። በተመሳሳይ Westberg and Jason (1996) ለንዑስ ቡድን ስራ የሚዘጋጁ ጥያቄዎች፣ ክፍት ጥያቄዎች ሆነው የተማሪዎቹን የማሰብና የመመራመር አድማስ የሚያሰፉ፤ እንዲሁም፣ ሀሳብ የሚያጭሩ (Thought Provoking) መሆን እንደሚገባቸው ይገልፃሉ።ይህ ሳይሆን ቀርቶ ፣የቡድን ስራ ጥያቄዎቹ ጥንቃቄ የጎደላቸውና ተገቢ ያልሆኑ ከሆኑ፣ የተማሪዎቹን ጊዜ በከንቱ ከማባከናቸውም ሌላ የመማር ፍላጎታቸው እንዲቀንስ ሊያደርጉ እንደሚችሉ Matiru et al (1995) ያስገነዝባሉ።

በአጠቃላይ የንዑስ ቡድኖችን ከማደራጀትና በቡድን ከማስተማር በፊት መምህራን ለበርካታ ጥያቄዎች ምላሽና ውሳኔ ሊሰጡ እንደሚገባ፣ Westberg and Jason (1996፣52)፣ በሚከተለው መልኩ ይዘረዝራሉ።

- ቡድኖቹን እንዴት ማደራጀት አለብኝ? የየቡድኖቹ አባላት ብዛት ስንት መሆን አለበት? ስብጥሩስ ምን መምሰል አለበት?
- የተማሪዎቹ የትምህርት ፍላጎትና ግብ ምንድነው? ጥንካሬና ድክመታቸውስ?
- የትምህርት አላማዎቹ ግልፅ፣ ተተግባሪና ተጨባጭ ናቸው?
- የቡድን ስራዎቹ ከነባራዊው ዐውድ ጋር የተገናዘቡና ንቁ መማርን (Active learning) የሚፈጥሩ ናቸው?
- ለንዑስ ቡድን መማር ሂደቱ፣ ምን አይነት የትምህርት መርጃ መማሪያዎች ያስፈልጋሉ?
- ምን አይነት አመራርን ተግባራዊ ማድረግ አለብኝ?
- የቡድን ስራው ከመጀመሩ በፊት፣ በቡድን ስራው ሂደትና ከቡድን ስራው በኋላ የኔ ተግባር ምን መሆን አለበት?
- የተማሪዎቹ ሚናና ተግባርስ ምን መሆን አለበት?
- የንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደቱ ላይ ዕብረቃ ለማድረግና ጠቃሚ ምላሽ (Feedback) ለማግኘት ምን አይነት ስልትን መቀየስ አለብኝ?

Putnam (1997) እንደሚገልፁት፣ በዝግጅቱ ወቅት መምህራኑ ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽና ውሳኔን መስጠት ብቻ ሳይሆን፣ እያንዳንዱን ዝርዝር ጉዳይ የቡድን ማስተማርን ለማቀድ በሚያስችል የትምህርት ዕቅድ ቅጽ[1] ላይ በግልፅ ማስፈር አለባቸው።

1 የቡድን ማስተማር ትምህርት እቅድ ቅፁን ከአባሪ 1 ይመልከቱ

### 2.2.2. ቡድኖችንና የመማሪያ ክፍልን ማደራጀት

የቡድን ማስተማር ዘዴን ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግና ተማሪዎች እርስ በርስ እየተረዳዱ እንዲማማሩ ለማድረግ ቡድኖችንና የመማሪያ ክፍሎችን በሚገባ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

#### 2.2.2.1. ቡድኖችን ማደራጀት

**የትብብር መማር ቡድን ዓይነቶች**

ለማስተማር ተግባር የሚያደራጁ ሶስት አይነት የትብብራዊ መማር ቡድኖች (Cooperative Learning groups) አሉ፡፡ እነሱም፣ ኢ-መደበኛ የትብብራዊ መማር ቡድኖች (Informal cooperative Learning groups)፣ መደበኛ የትብብራዊ መማር ቡድኖች (Formal cooperative learning groups) እና የትብብራዊ መሰረት ቡድኖች (Cooperative base groups) ናቸው (Johnson and Johnson 1990፣ Davis 1993)፡፡

ኢ-መደበኛ ቡድኖች:- ኢ-መደበኛ የመማር ቡድኖች፣ በአንድ ክፍለ ጊዜ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ወይም ለአንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ የሚመሰረቱ ጊዜያዊ (ad hoc) ቡድኖች ናቸው፡፡ አላማቸውም ለአጭር ጊዜያት ያህል ተማሪዎች በጋራ ሆነው ሀሳብ እንዲለዋወጡ ወይም በአጭር ጊዜያት የሚሰራ ስራን እንዲሰሩ ማድረግ ነው (Davis 1993)፡፡ ኢ-መደበኛ የመማር ቡድኖች አብዛኛውን ጊዜ የሌክቸር ዘዴን ማገገሪ ወይም ማጠናከሪያ ሆነው ያገለግላሉ (Johnson and Johnson 1990)፡፡

መምህራን ኢ-መደበኛ ቡድኖችን ለመመስረት የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ:- ጓደኝነት ወይም ችሎታን መሰረት አድርገው መመስረት ይችላሉ፡፡ ወይም ደግሞ ተማሪዎች ፊታቸውን አጠገባቸው ወዳሉ ተማሪዎች እንዲያዞሩ በማድረግ፣ ቁጥር እንዲጠሩ በማድረግ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዘዴ ተጠቅመው ሊመሰርቱ ይችላሉ (Davis 1993፣ Putnam 1997)፡፡ ተማሪዎች ቁጥር እንዲጠሩ በማድረግ፣ አንድ አካባቢ የተቀመጡ ተማሪዎች አንድ ላይ እንዲሆኑ በማድረግ ወዘተ. የሚመሰረቱ ቡድኖች የተማሪዎች ቅይጥነት (heterogeneity) መፍጠር ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ አይነት የቡድን ምስረታ እንደ አጋጣሚ ተመሳሳይ ፆታ፣ ተመሳሳይ ችሎታ ወዘተ. ያላቸው ተማሪዎች አንድ ላይ እንዲሆኑ ሊያደርግ ስለሚችል ትክክለኛ ትብብራዊ መማርን የሚፈጥር አይደለም፡፡ በክፍል ውስጥ ቡድኖችን ለመመስረት

ከሚያስችሉ በርካታ ዘዴዎች ቅይጥነትን በመፍጠር ረገድ በእጣ የሚደረገው ምደባ የተሻለ ነው (Harmer 2006)::

**መደበኛ ቡድኖች:-** መደበኛ የትብብር መማር ቡድኖች፣ ሰፊ ጊዜን ለሚፈልጉ የቡድን ስራዎች ለምሳሌ:- የቡድን የፕሮጀክት ስራን ለመስራት፣ ስለአንድ ጉዳይ በቡድን ዘገባን ለማዘጋጀት፣ በቡድን መፅሀፍን ለመገምገም፣ በቡድን ድርሰትን ለማንበብ፣ በቡድን ድርሰትን ለመፃፍ፣ ወዘተ. የሚደራጁ ቡድኖች ናቸው:: እነዚህ ቡድኖች ለተከታታይ ክፍለ ጊዜያት ወይም ለተከታታይ ሳምንታት፣ አንዳንዴም ለአንድ ሙሉ ሴሚስተር፣ የቡድን አባላቱ አንድ ላይ ሆነው የሚሰሩባቸው ናቸው(Johnson and Johnson 1990፣ Davis 1993)::

**የትብብራዊ መሰረት ቡድኖች:-** የትብብራዊ መሰረት ቡድኖች የሚባሉት ደግሞ፣ የቡድን አባላቱ ከአንድ ሴሚስተር ለበለጠ ጊዜ አብረው የሚቆዩባቸው ናቸው:: አባላቱ ለአንድ ሙሉ አመት ወይም ለሁለትና ለሶስት አመታት ሳይነጣጠሉ አብረው ይቆያሉ:: የዚህ አይነት ቡድኖች አላማቸው፣ ተማሪዎች በቆይታ ብዛት የበለጠ እንዲዋሀዱ ለማድረግና በከፍተኛ ደረጃ አንዱ ሌላውን እየደገፈ፣ እየረዳና እያበረታታ በመማር፣ የሚፈለገውን የትምህርት ግብ ለማሳካት ነው (Johnson and Johnson 1990፣ Davis 1993)::

**የቡድን አባላት ብዛት**

በንዑስ ቡድኖች አደረጃጀት ዙሪያ፣ ከሚነሱ ቀዳሚ ጉዳዮች አንዱ የቡድን አባላት ብዛት ስንት መሆን አለበት? የሚለው ነው:: ለውጤታማ የንዑስ ቡድን ማስተማር፣ የቡድን አባላት ቁጥር ማነስ ጠቃሚ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ይስማሙበታል:: ቁጥሩ ምን ያህል መሆን አለበት በሚለው ላይ ግን የተለያዩ ሃሳቦችን ያቀርባሉ::ለምሳሌ Burden (2003) ለውጤታማ የንዑስ ቡድን ማስተማር፣ የቡድን አባላት ቁጥር ቢያንስ አራት ቢበዛ ደግሞ ስድስት መሆን አለበት በማለት ሀሳብ ያቀርባሉ:: እንደ Westberg and Jason (1996) እና Exley and Dennick (2004) ሃሳብ ደግሞ፣ የንዑስ ቡድን አባላት ቁጥር ከአምስት እስከ ስምንት ቢሆን ይመረጣል:: እንደ እነዚህ ምሁራን ገለፃ፣ የንዑስ ቡድን አባላት ቁጥር፣ ከአምስት ካነሰ የተለያዩ ሀሳቦችንና አመለካከቶችን የማግኘት እንዲሁም ጥሩ የእርስ በርስ ግንኙነት የመፍጠር ሂደት ደካማ ይሆናል:: በሌላ በኩል ቁጥሩ ከስምንት ከበለጠ ደግሞ፣ እያንዳንዱ የቡድን አበላት እኩል የመሳተፍ እድላቸው እየቀነሰ ይሄዳል:: Jaques (1989) በበኩላቸው፣ ብዙዎቹ በንዑስ ቡድን ማስተማር ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ምሁራን የሚስማሙበት የቡድን አባላት ቁጥር፣ ከአምስት

እስከ ሰባት ነው ይላሉ:: በሌላ በኩል Harmer (2006) ጥሩ የእርስ በርስ ግንኙነትን ለመፍጠር ተመራጩ የንዑስ ቡድን አባላት ቁጥር አምስት እንደሆነ በመግለፅ፣ አምስት የመሆኑ ጠቀሜታ ጥሩ የእርስ በርስ ግንኙነት ለመፍጠር አመቺ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ቁጥሩ ጎደሎ በመሆኑ በድምፅ ብልጫ መወሰን ያለባቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በድምፅ ለመወሰን ማመቺቱ ጭምር እንደሆነ ያስረዳሉ::

**የንዑስ ቡድን አባላት አመራረጥ**

አንድን ንዑስ ቡድን ተማሪዎች በፍላጎታቸው እንዲመራረጡ በማድረግ ወይም ደግሞ መምህሩን ተመሳሳይነትን (Homogeneity) ወይም ቅይጥነትን (heterogeneity) መሰረት አድርገው ተማሪዎችን በመምረጥ ማደራጀት ይችላሉ (Garfield 1993)::ንዑስ ቡድኖችን በተባሉት መንገዶች ማደራጀት ቢቻልም፣ በተማሪዎች ምርጫና በተመሳሳይነት መሰረት የሚራጁ ቡድኖች፣ ውጤታማ የሆነ ትብብራዊ መማርን እንደማያስገኙ በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል:: ለምሳሌ:- Burden (2003፣ 162) (Cohen 1994፣ Johnson and Johnson 1999፣ እና Slavin 1991)ን ዋቢ አድርገው እንደሚገልፁት:

> *የቡድን ስራ አንዱ አላማ፣ የእርስ በርስ ግንኙነትን ማዳበር ስለሆነ አባላቱን ከፆታም፣ ከብሔርም አንፃር ማሰባጠር አስፈላጊ ነው:: የአካል ጉዳተኞችም ቢሆኑ የአካለ ጉዳተኞች ካልሆኑት ጋር መሰባጠር አለባቸው:: ምንም እንኳን ለአንዳንድ ተግባራት ሲባል የተመሳሳይነት መስፈርትን በመጠቀም፣ተመሳሳይ ቡድኖችን (Homogenous groups) ማደራጀት ቢያስፈልግም በአጠቃላይ ሲታይ ግን ምሁራን የሚመክሩት ቅይጥ ቡድኖችን (heterogeneous groups) መጠቀምን ነው::*

በተመሳሳይነት (Homogeneity) መስፈርት ከሚደራጁ ቡድኖች ይልቅ፣ በቅይጥነት (heterogeneity) መስፈርት የሚደራጁ ንዑስ ቡድኖች ለመማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ ናቸው:: በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን ፆታ፣ ዕድሜ፣ ባህላዊ ዳራ፣ ሀይማኖት፣ ብሔረሰብ፣ የትምህርት ችሎታ፣ የቤተሰብ ሁኔታ ወዘተ. ከግምት ባስገባ መልኩ ቡድኖችን ማደራጀት አለባቸው (Jagues 1989፣ Bruke 2000፣ Campbell 2004)::

በቡድን ማስተማር ጊዜ፣ በተለይ ብሔረ ብዙ (Multi-ethnic) በሆነ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን፣ የተለያዩ ብሔረሰቦችን በማሰባጠር ቡድኖችን ቢመሰርቱ ትምህርታዊ (Academic) እንዲሁም ማህበራዊ (Social) ጠቀሜታ እንዳለው በርካታ ጥናቶች ያመለክታሉ (Cowie et al

1994):: ከችሎታ አንፃርም የቡድን አባላት ቅይጥ ሊሆኑ ይገባል። በችሎታ መራራቅ ሊከሰት የሚችለውን ችግር ለማጥበብም የተሻለው ዘዴ፣ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች (High-ability students) መካከለኛ ችሎታ ካላቸው ተማሪዎች (Middle-ability students) ጋር፣ መካከለኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች (Middle-ability students) ደግሞ ዝቅተኛ ችሎታ ካላቸው ተማሪዎች (Low-ability students) ጋር መመደብ ነው በማለት Blumenfeld et al (1996) ያስረዳሉ።

**የቡድን አባላት አብሮ ቆይታ**

የቡድን አባላት አብረው ለምን ያህል ጊዜ መቆየት አለባቸው? የሚለው ጥያቄ የብዙ መምህራን ጥያቄ መሆኑን (Putnam 1997፣ 60-61) እንደሚከተለው ይገልፃሉ።

> *ብዙ ጊዜ መምህራን የቡድን አባላት ለምን ያህል ጊዜ አብረው መቆየት አለባቸው? በማለት ይጠይቃሉ:: ለዚህ ቁርጥ ያለ መልስ የለም:: ይህን የሚወስነው የሚሰጠው የቡድን ስራ አይነት ነው:: በአጠቃላይ ግን፣ የቡድን አባላት፣ የአንድ ቡድን አባልነት ስሜት እንዲሰማቸው፣ ረዘም ላለ ጊዜ አብረው መቆየት ይኖርባቸዋል...*

በቡድን አባላት ግንኙነት ሂደት (Group Dynamics) ዙሪያ የተደረገ በርካታ ጥናቶች እንደሚያስረዱት፣ የቡድን አባላት የእርስ በርስ ግንኙነት ተጠናክሮ ውሁድ (Coherent) የሆነና በጋራ መንፈስ የሚሰራ ቡድን ለመፍጠር በቂ ጊዜ ያስፈልጋል (Luft 1984):: ጥናቶቹ እንደሚያስረዱትም፣ ውሁድ የሆነ ቡድን ለመፍጠር፣ አባላቱ አራት ደረጃዎችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል:: እነሱም የቡድን ምስረታ (Forming)፣ ግጭትና የመላመድ ውጣ ውረድ (Storming)፣ የቡድን ደንብን መቀበል (Norming) እና በመተባበር መንፈስ መስራት (Performing) ናቸው:: ስለዚህ፣ ተማሪዎች በሚገባ እስኪተዋወቁ፣ አንዳቸው የሌላቸውን ድክመትና ጥንካሬ እስኪለዩ፣ እንዲሁም እርስ በርስ መደጋገፍንና መቆጣጠርን እስኪያዳብሩ ድረስ፣ ረዘም ላለ ጊዜ በአንድ ቡድን ውስጥ አብረው መቆየት ይኖርባቸዋል:: ይህን ማድረግ የሚቻለውም፣ ረዥምም ጊዜን የሚፈልጉ የፕሮጀክት ስራዎችንና ልዩ ልዩ ተግባራትን በመስጠት ነው:: ብዙ ምሁራንም፣ የቡድን አባላት ለአንድ ሴሚስተር ያህል አብረው ቢቆዩ የተሻለ እንደሚሆን ይመክራሉ (Mills 1998)::

ሌሎች እንደ Matiru et al (1995)፣ Westberg and Jason (1996) ፣ Campbell (2004) ያሉ ምሁራንም ፣ የተሳካ ትብብራዊ መማር የሚኖረው የቡድን አባላቱ ረዘም ላለ ጊዜ አብረው ሲቆዩ መሆኑን ይስማሙበታል። Johnson and Johnson (1990) እንደገለፁትም፣ ለትብብራዊ የንዑስ ቡድን መማር፣ በየጊዜው እየፈረሱ በአዲስ መልክ ከሚመሰረቱ ኢ-መደበኛ ቡድኖች ይልቅ፣ ተማሪዎች ረዘም ላለ ጊዜ አብረው የሚቆዩባቸው የመደበኛና የትብብር መሰረት ቡድኖች ውጤታማ ናቸው። በመሆኑም፣መምህራን በነዚህ ሁለት ቡድኖች ላይ ማተኮር አለባቸው።

## 2.2.2.2. የመማሪያ ክፍልን ማደራጀት

የንዑስ ቡድን አባላት አቀማመጥ ሁኔታ፣ በመካከላቸው የሚኖረው ቅርበትና ርቀት፣ በአባላቱ የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖን የማሳረፍ አቅም አላቸው። ስለዚህ የቡድን አባላቱ የሚማሩባቸው ክፍሎች ቅርፅና መጠን እንዲሁም የወንበሮችና የጠረጴዛዎች አደረጃጀት ትኩረት የሚሹ ጉዳች ናቸው (Jaques 1989)።

የንዑስ ቡድን አባላት፣ በቀላሉ እርስ በርስ ሊደማመጡና ሌሎች ቡድኖችን ሳይረብሹ ሊነጋገሩ በሚችሉበት ቅርበት መቀመጥ አለባቸው። በተጨማሪም፣ አባላቱ እርስ በርስ መተያየትና በጋራ የሚጠቀሙባቸውን የትምህርት መሳሪያዎች በቀላሉ ማየት በሚችሉበት ሁኔታ መቀመጥ አለባቸው። ተቀራርቦ መቀመጥ ውሁድነትን (Cohesiveness) ሲጨምር፣ በአንፃሩ ደግሞ በረገኛርም ጠረጴዛዎች የተነሳ የሚፈጠር መራራቅ፣ በአባላቱ ዘንድ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ መራራቅን ይፈጥራል (Putnam 1997)።እንደ (Johnson and Johnson, 1990፣ 123-124) አገላለፅ፡

> *የአንድ ንዑስ ቡድን አባላት፣ የትምህርት መሳሪያዎችን በቀላሉ በሚቀባበሉበት፣ በዝቅተኛ ድምፅ እየተነጋገሩ በሚደማመጡበትና አይን ለአይን በሚተያዩበት ሁኔታ ተቀራርበው መቀመጥ አለባቸው።... መምህራን የንዑስ ቡድን አቀማመጥን ሲያደራጁ ተዘውትረው ከሚከሰቱ ስህተቶች፣ አንደኛው ሁሉም ተማሪዎችን አይን ለአይን መተያየት በማይችሉበት ማዕዘናዊ አቀማመጥ ማስቀመጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መቀመጫዎችን በረዥሙ ወደ ጎን በመደርደር፣ ተማሪዎች በዝቅተኛ ድምፅ ሊደማመጡና የትምህርት መሳሪያዎችን በቀላሉ ሊዋዋሱ በማይችሉበት ሁኔታ ማስቀመጥ ነው።*

የንዑስ ቡድን አባላት በሚተያዩበትና በሚደማመጡበት ሁኔታ ተቀራርበው ሊቀመጡ የሚችሉባቸው የተለያዩ አማራጮች አሉ፡፡ ክባዊ አቀማመጥ፣ ትይዩ አቀማመጥ፣ የ "U" ቅርፅ አቀማመጥ የሚጠቀሱ ናቸው (Jaques 1989፣ Matiru et al 1995፣ Burke, 2000፣ Wragg 1999)፡፡[2]

በአቀማመጥ አደረጃጀት ወቅት መታሰብ ያለበት ጉዳይ የተማሪዎቹ ተቀራርቦ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን፣ አጠቃላይ የክፍሉ አደረጃጀት ቅርፅ ጭምር ነው፡፡ በንዑስ ቡድን ማስተማር ወቅት የክፍሉ ጠረጴዛዎችና ወንበሮች እንደተገኘ የሚደራጁ ከሆነ፣ በትምህርት ሂደቱና በቡድኖቹ የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖን ያሳድራል (Jaques 1989)፡፡ስለዚህ በቡድን ስራ ወቅት፣ የመማሪ ክፍሉ ጠረጴዛዎችና ወንበሮች በሚገባ መደራጀት አለባቸው፡፡ ጥንቃቄ በተሞላበት የክፍል አደረጃጀት ተጠቃሚ የሚሆኑት ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ መምህራንም ጭምር ናቸው (Bruke 2000)፡፡ እኚሁ ምሁር፣ የንዑስ ቡድን መማሪያ ክፍሎች ሲደራጁ፣ መምህራን ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ነጥቦችን በተመለከተም (Evertson፣ Emmer፣ Clements and Worsham፣ 1997)ን በመጥቀስ:

1. በየቡድኖቹ መካከል በቂ መተላለፊያ ቦታ መኖሩን አረጋግጥ፡፡
2. ሁሉም ተማሪዎች፣ በመምህሩ በቀላሉ መታየት በሚችሉበት ሁኔታ መቀመጣቸውን አረጋግጥ፡፡
3. ለቡድን ስራው የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች፣ ተማሪዎቹ በቀላሉ ሊያገኟቸው በሚችሉበት ሁኔታ መቀመጣቸውን አረጋግጥ፡፡
4. የቡድን ስራዎቹ ውጤት ዘገባና ገለፃዎች ሲቀርቡ፣ ሁሉም ተማሪዎች በሚከታተሉበት፣ የሚታይ ነገር ካለም በሚያዩበት ሁኔታ መቀመጣቸውን አረጋግጥ፡፡

ሲሉ ይዘረዝራሉ፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ከሚፈጥሩ የክፍል አደረጃጀቶች መካከልም አባሪ 3ሀ ላይ የተመለከተው ፣ አንድ አማራጭ ሊሆን እንደሚችል በስዕላዊ መግለጫ ያሳያሉ፡፡ (Jaques (1989)ም በአባሪ 3 ለ ያለው የክፍል አደረጃጀት ሌላው አማራጭ እንደሆነ ያሳያል፡፡

### 2.2.3. የቡድን ዓላማንና የቡድን ስራን ግልፅ አድርጎ ማቅረብ

ለትብብራዊ የንዑስ ቡድን መማር ተማሪዎችን በሚፈለገው ቁጥርና ስብጥር ማደራጀት እንዲሁም የክፍል አቀማመጣቸውን በሚገባ ማደራጀት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ ጥሩ

2 የቡደን አባላት አቀማመጥ ምሳሌዎችን ከአባሪ 2 ይመልከቱ፡
3የክፍል ውስጥ አደረጃጀትን ከአባሪ 3 ይመልከቱ፡

የትብብራዊ መማር ሂደት እንዲፈጠር መምህራን ፣ተማሪዎች የንዑስ ቡድን መማር ዓላማንና በቡድን ስራ ወቅት ማሳየት የሚገባቸውን የእርስ በርስ ግንኙነት ሊያሳውቋቸው ወይም በንዑስ ቡድን መማር ሂደት ምን ማድረግ እንዳለባቸውና ምንስ ማድረግ እንደሌለባቸው ሊያስረዷቸው ይገባል (Gregory and Thorly 1994፣ Putnam 1997፣ Hougen 1998፣ Exley and Dennick 2004፣ Harmer 2006)::

ይህ ካልሆነ ግን ተማሪዎች፣ መምህራን የቡድን ስራ የሚሰጧቸው ለማስተማር በመስነፍና በመሰላቸት ሊመስላቸው ይችላል:: ይህ አመለካከት ደግሞ ተገቢ ትብብራዊ መማር እንዳይኖር ያደርጋል:: በአንፃሩ መምህራን ለተማሪዎቹ የንዑስ ቡድን ስራ አላማንና ጠቀሜታውን ካስረዱ፣ ብዙ ተማሪዎች በቡድን ስራ ላይ በጉጉትና በፍላጎት ይሳተፋሉ (Hougen 1998)::

Atkins et al (1996፣ 212) ተባብሮ የመስራት ክሂሎትን የማስተማር አስፈላጊነትን በተመለከተ (Christison 1990)ን በመጥቀስ::

> *ተባብሮ የመስራት ችሎታን የሰው ልጆች ሲወለዱ ደመነፍሳዊ በሆነ መንገድ ይዘውት የሚወለዱት አይደለም:: በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችም፣ በንዑስ ቡድኖች እንዲደራጁናቸው ወዲያውኑ ተባብረው መስራትን አይጀምሩም:: ስለዚህ፣ ልክ እንደ ሂሳብ፣ ጽህፈትና ንባብ ክሂሎት ሁሉ ተባብሮ የመስራት ክሂሎትንም በትምህርትነት የግድ ሊያገኙ ይገባል:: ብዙ ተማሪዎች የዚህ ክሂሎት ትምህርት ስለማይሰጣቸው፣ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተባብሮ መስራት አይሆንላቸውም...*

የንዑስ ቡድን መማር ዓላማንና አሰራርን ከማስተዋወቅ በተጨማሪ ዘላቂ የሆነ ትብብራዊ መማር እንዲኖር፣ መምህራን ከጅምሩ ከተማሪዎቹ ጋር በመወያየት የንዑስ ቡድን መማር መተዳደሪያ ደንብ መቅረፅ እንደሚኖርባቸው የተለያዩ ምሁራን ያሳስባሉ:: ይህንኑ አስመልክቶ Putnam (1997፣ 100) እንደሚገልፁት "ግልፅና ምክንያታዊ የሆኑ የክፍል ደንቦችንና አሰራሮችን መቅረፅ፣ የትብብራዊ መማር ክፍል አመራር፣ መሰረታዊ ጉዳይ ነው::... ያለነዚህ መሪ መመሪያዎች ተማሪዎችን ተባብሮና ተደጋግፎ የመስራት ክሂሎትን ማስተማር አስቸጋሪ ነው::..." የንዑስ ቡድን መማር መመሪያዎቹ ሲዘጋጁም፣ እንደ መረዳዳትና ፍትሃዊነት የመሳሰሉ ሰብዓዊ መርሆች ላይ ተመስርተው መዘጋጀት አለባቸው:: በተጨማሪም፣ እያንዳንዱ የመመሪያው ህግ ላይ፣ በመምህሩና በተማሪዎቹ በቂና ነፃ ውይይት መካሄድ አለበት:: ይህንን ማድረግ፣ ተማሪዎቹ በቡድን ስራ ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸው፣ ምንስ ማድረግ

እንደሊለባቸው ከመነሻው እንዲያውቁ ከማድረግ ባሻገር፣ ወደፊት በቡድን ስራ ወቅት ሊከሰቱ ለሚችሉ የባህሪ ችግሮች ከወዲሁ መፍትሄ እንደ መፈለግ ይሆናል Campbell (2004)፡፡ Exley and Dennick (2004፣21)ም ለንዑስ ቡድን ማስተማር የመተዳደሪያ ደንብን አስፈላጊነት በመደገፍ፣ በደንቡ ውስጥ ሊካተቱ ከሚገባቸው ነጥቦች ውስጥ የሚከተሉትን በምሳሌነት ያቀርባሉ፡፡

- ማንኛውም ተማሪ፣ በቡድን ውይይት ወቅት የችሎታውን ያህል ሀሳብና አስተያየት መስጠት አለበት፡፡
- የሌሎችን አመለካከት አክብር፡፡
- ማንንም ቢሆን እየተናገረ ሳለ አታቋርጥ፡፡
- በውይይት ወቅት እኔ ብቻ ልናገር አትበል፤ ለሌሎችም ዕድል ስጥ፡፡
- የሰዎችን ሀሳብ እንጂ ስብዕናቸውን አትንቀፍ፡፡
- ሌሎች የሚሉትን አድምጥ፡፡
- በትምህርቱ አላማና ግብ ላይ አተኩር፡፡
- ተመርጦ በቀረበው የቡድን ስራ ላይ ብቻ አተኩር፡፡
- እያንዳንዱ አባል፣ የቡድኑን አላማ ለማሳካት ሃላፊነት አለበት፡፡
- ለቡድን ስራው መሳካት፣ በግልህ ማድረግ ያለብህን ዝግጅት ሁሉ ተግባራዊ አድርግ፡፡

ከዚህ አጠቃላይ መተዳደሪያ ደንብ ጎን ለጎን፣ በያንዳንዱ የንዑስ ቡድን ስራ መጀመሪያ ላይ፣ የስራውን አላማና አሰራር እንዲሁም ስራው የሚፈጀውን ጊዜና የስራውን መገምገሚያ መስፈርት፣ መምህራን ግልፅ አድርገው ማቅረብ እንደሚገባቸው በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ Putnam (1997፣ 57-58) "…ተማሪዎች ምን እንደሚያከናውኑ ግልፅ ሊሆንላቸው ይገባል፡፡ የቡድን ስራ ሲሰጥ፣ለተማሪዎቹ የቡድን ስራውን አላማና የመገምገሚያ መስፈርትን በቃልና በፅሁፍ ማስረዳት ጠቃሚ ነው፡፡" በማለት ሲያስረዱ፣ Ur (1996፣234)ም በበኩላቸው:

> *በቡድን ስራ መጀመሪያ ላይ የሚሰጠው ትዕዛዝ ወሳኝ ነው፡፡ ተማሪዎች ምን እንደሚሰሩ በትክክል ካላወቁ ትርፉ ሰዓት ማባከን፣ መደናገር፣ ያልሆነ ስራን መስራት፣ ብሎም መምህሩ ክፍሉን መቆጣጠር አለመቻል ነው፡፡…ስለዚህ፣ በቡድን ስራ ወቅት በቀላሉ ልታስረዳው የምትችለውን ስራ ምረጥ … የስራውንም ትዕዛዝ፣ ለተማሪዎቹ ማቴሪያሎቹን ከመስጠትህና ክፍሉን በቡድን ከማደራጀትህ በፊት ብትገልፅ ተመራጭ ነው፡፡…*

ይላሉ:: የሚቀርበው የቡድን ስራ ትዕዛዝ፣ ተማሪዎቹ ምንድነው የምንሰራው ስራ? በማለት ግራ የማይጋቡበትና ጊዜ የማያባክኑበት ወይም ትዕዛዙን ባለመረዳት የተነሳ፣ በተሳሳተ አቅጣጫ የማይሄዱበት መሆን አለበት (Garfield 1993):: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ Johnson and Johnson (1990) መምህራን በቅድሚያ ስለ ቡድን ስራው ለተማሪዎቹ ገለፃ በማድረግ፣ ተማሪዎቹ የሚሰሩትን ስራና የትምህርቱን አላማ እንዲረዱ ማድረግ አለባቸው:: በዚህ ጊዜም መምህራን ተማሪዎቹ ስለ ቡድን ስራው አሰራር ለሚቀርቧቸው ጥያቄዎች ተገቢ ማብራሪያ መስጠት አለባቸው በማለት ያስገነዝባሉ::

Harmer (2006) የቡድን ስራው የሚፈጀው ጊዜ ከመነሻው ለተማሪዎቹ በደንብ መገለፅ እንደሚኖርበት ሲያስረዱ Gregory and Thorley (1994፣ 128)ደግሞ ለስራው የሚያስፈልገው ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ስራው የሚገመገምበት መስፈርትም መገለፅ ያለበት፣ በስራው መጀመሪያ ላይ መሆኑን "... ከመነሻ የቡድን ስራንና ስራው የሚገመገምበትን መስፈርት ግልፅ ማድረግ ጠቃሚ ነው:: እንዲያ ከሆነ ተማሪዎች በየትኛው አቅጣጫ መጓዝ እንዳለባቸው አወቁ ማለት ነው::..."በማለት ይገልፃሉ::

ከዚህ በተጨማሪ፣ የቡድን ስራ ሲሰጥ ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ለንዑስ ቡድን አባላቱ የስራ ድርሻን ወይም የያንዳንዳቸውን ሚና (Role) ለይቶ መስጠት ነው:: Davis (1993) የንዑስ ቡድን አባላት በሙሉ ለቡድን ስራው ተመጣጣኝ የሆነን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱና ቡድኑ ወደሚፈለገው ግብ እንዲደርስ፣ ተመራጩ ስልት፣ መምህራን የሚሰጠው የቡድን ስራን ለክፍፍል እንዲያመች አድርገው በማዘጋጀት፣ ሁሉም እንዲሳተፉ ማድረግ እንደሆነ ያስረዳሉ::

> *የተዋጣለት ትብብራዊ መማር፣ የአባላትን ቡድናዊ ሀላፊነትንም፣ ግላዊ ሀላፊነትንም አጣምሮ መያዝን ይጠይቃል... የቡድን አባላት ግላዊ ኃላፊነት እንዲሰማቸው ለማድረግ፣ በስራው ወቅት ሊመዘገቡ የሚገባቸው ነገሮችን አንዱ እንዲመዘግብ፣ አንዱ ደግሞ ከመምህሩ ጋር አገናኝ እንዲሆን፣ ወዘተ. ማድረግ ይቻላል:: ከአንድ ስራ ወደ ሌላ ስራ ሲገባም፣ የቡድን አባላቱ የስራ ድርሻ ሊቀያየር ይችላል:: ቢያንስ ቢያንስ ግን በቡድን ስራ ወቅት የቡድን መሪ፣ የቡድን ፀሐፊ፣ የቡድኑ አገናኝና ጥያቄ አቅራቢ ሊኖሩ ይገባል*(Kain 2003፣17)::

በተመሳሳይ Jacobs (1988) በትብብራዊ መማር፣ ግለሰቦች ግባቸውን የሚመቱት አብረዋቸው የሚሰሩት አባላት በሙሉ ግባቸውን መምታት ሲችሉ እንደሆነ ያስረዳሉ::

### 2.2.4. የቡድን ስራዎችን መከታተል

መምህራን የቡድን ስራዎችን ከሰጡ በኋላ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አለባቸው (Hougen 1993፣ Putnam 1997፣ Jaques 1998)::ይህንን አስመልክተው Matiru et al (1995፣212) እንደሚያስረዱት፡

> *በቡድን ስራ ወቅት ከያንዳንዱ የቡድን አባል ንቁ ተሳትፎና አስተዋጽኦ ይጠበቃል:: ብዙ ጊዜ እንደሚታየው ከሆነ ግን፣ ይህ ሁኔታ ያለ መምህሩ ክትትል ሊገኝ አይችልም:: የመምህሩ ክትትል ተማሪቹን ለቡደን ስራው ፍላጎት እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ተሳትፎአቸውን ማበረታታት፣ በተሰጠው ስራ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግና ስራውን በተሰጠው የጊዜ ገደብ እንዲያጠናቅቁ ማድረግን ያካትታል::....::*

መምህራን የቡድን ስራዎችን መከታተል ያለባቸውም ተማሪዎቹ ስራቸውን መስራት ከጀመሩበት ደቂቃ ጀምሮ ነው:: አብዛኛው የመምህራኑ ሰዓት መዋል ያለበትም፣ ተማሪዎቹ የቡድን ስራውን በመስራትም ሆነ፣ እርስ በርስ ግንኙነት የሚያጋጥማቸውን ችግሮች በመለየትና በመፍታት ነው (Johnson and Johnson 1990):: Yunfeng በበኩላቸው፣ (Brown 1991)ን በመጥቀስ በንዐስ ቡድን ስራ ወቅት መምህራን የሚከተሉትን መፈፀም እንደማይገባቸው ያስገነዝባሉ::

- ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠህ ወረቀት አታርም
- ከክፍል ወጥተህ እረፍት አታድርግ
- አንድ ቡድን ጋ ሄደህ ከሚገባው በላይ አትቆይ

ተማሪዎች የቡድን ስራ በሚሰሩበት ወቅት፣ መምህራን በክፍሉ ውስጥ በመንቀሳቀስና ወደ ተማሪዎቹ በመቅረብ፣ ለተማሪዎቹ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፣ የሚቸግራቸው ነገር ካለም መፍትሄ መጠቆም አለባቸው:: በተጨማሪም፣ ተማሪዎቹ በስራው ላይ ምን ያህል ትኩረት ሰጥተው እንደሚሳተፉና እርስ በርስ ሀሳብ እንደሚለዋወጡ በማጤን ግምገማ ማድረግ አለባቸው (www.unicef.org)::

በክትትሉ ሂደትም፣ ተማሪዎቹ ለሚያደርጉት አነስተኛ ሙከራም ቢሆን ማበረታቻ መስጠት ያስፈልጋል:: መምህራኑ ተማሪዎቹ የተናገሩትን ደግመው ከተናገሩ በኋላ ማበረታቻቸውን ቢሰጡ

ደግሞ ይበልጥ ይመረጣል:: ምክንያቱም፣ ተማሪዎቹ በመምህራኖቻቸው መደመጣቸው ስለሚያስደስታቸው ይበልጥ ለተሳትፎ ይነሳሳሉ (Hougen 1998)::

መምህራን የቡድን ስራዎችን በሚከታተሉበት ወቅት፣ አንዳንድ ቡድኖች ቀድመው ስራቸውን ጨርሰው ሊያገኙ ይችላሉ:: ትኩረታቸው በስራ ላይ እንዲሆን ሌላ ተጨማሪ ስራን መስጠት ይቻላል:: ለዚህም ተግባር ሲባል አስቀድመው መጠባበቂያ ስራዎችን አዘጋጅተው ቢይዙ የተሻለ ነው።በተጨማሪም፣መምህራኑ እንደ ሁኔታው፣ በተማሪዎቹ የቡድን ስራ መሀል ጣልቃ በመግባት፣ አስፈላጊ ድጋፍ ማድረግ፣ ችግር ያጋጠማቸውን ተማሪዎች መርዳት፣ ተማሪዎቹ ለትምህርት የቀረበውን ቋንቋ ብቻ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ እንዲሁም ተሳትፎውን በበላይነት ብቻቸውን የተቆጣጠሩ ተማሪዎችን ወይም በተቃራኒው ተሳትፎ የማያደርጉ ተማሪዎችን በመከታተል በልዩ ልዩ ጥበብ እኩል ተሳትፎ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል (Ur 1996)::

በንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደት ብዙዎች ተሳታፊ ሲሆኑ ጥቂቶች ግን ገለልተኛና የማይሳተፉ ሊሆኑ ይችላሉ:: የእነዚህን የማይሳተፉ ተማሪዎች ተሳትፎ ለማሳደግ፣ ከክፍል ውጭ ተማሪዎቹን በግል በማነጋገር ችግሮቻቸውን መለየት እንዲሁም ቀዳሚ ልምድና ባህላዊ ዳራቸውን መለየት ይገባል (Rose 2005)::

የቡድን ስራው ከክፍል ውጭ የሚሰራ ከሆነና ረዘም ያለ ጊዜን የሚፈልግ ከሆነ ደግሞ፣ ከተማሪዎቹ ጋር በመወያየት፣ ስራው ደረጃ በደረጃ የሚከናወንበትን የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት ያስፈልጋል:: በጊዜ ሰሌዳው መሰረትም ስራውን በየጊዜው መከታተል ይገባል (Davis 1993)::

የተሳካ የቡድን መማር እንዲኖር፣ በቡድን አባላቱ መካከል የግድ ጤናማ የእርስ በርስ ግንኙነት ሊኖር ይገባል:: በመሆኑም፣ መምህራኑ በየጊዜው፣ በየቡድኖቹ አባላት መካከል ጤናማ የሆነ የእርስ በርስ ግንኙነትና የመረዳዳት መንፈስ መኖሩን መከታተል አለባቸው (Johnson and Johnson 1990፣ Davis 1993፣ Exley and Dennick 2004):: ጤናማ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲኖር የማድረጊያ አንዱ መንገድም ተማሪዎቹ ግጭቶች ሲፈጠሩ፣ ራሳቸው የሚፈቱበትን መንገድ ማስተማር መሆኑን Putnam (1997፣ 110) "በቡድን ስራ ወቅት፣ በቡድን አባላት መካከል አለመግባባት መፈጠሩ አይቀሬ ነው:: … ከትብብራዊ መማር የክፍል ውስጥ አመራር የሚጠበቅ አንዱ ዋና ተግባርም፣ ተማሪዎች አለመግባባቶችን የሚፈቱባቸውን

ገንቢ የሆኑ ክሂሎችን ማስተማር ነው።"ሲሉ ያስረዳሉ:: Devis (1993:4) Wolvoord (1986)ን ዋቢ አድርገው እንደሚገልፁትም:

> *አንድ ቡድን በጥሩ ሁኔታ እየሰራ ባይሆን እንኳን የቡድን አባላቱን መነጣጠል አይገባም:: ... ምክንያቱም ተማሪዎችን ችግር ፈጥረዋል ብሎ ወደ ሌላ ቡድን እንዲሄዱ ማድረግ፣ በጥሩ ሁኔታ እየሰሩ ያሉ ተማሪዎችን መረበሽ ከመሆኑም በተጨማሪ ችግር የፈጠሩት ተማሪዎችን፣ በቡድን መማር ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችን እየፈቱ የመማር ልምድ እንዳያዳብሩ ያደርጋቸዋል::*

በቡድን ማስተማር ሂደት መምህራን ሊያተኩሩበት የሚገባ ሌላው ጉዳይ አስፈላጊ የትምህርት መርጃ መማሪያዎችን እየተከታተሉ የማቅረብ ሁኔታ ነው:: Richards and Rodgers (2001) እንደሚያስገነዝቡት፣ ተማሪዎች አንድን ስራ በመተባበር መንፈስ እንዲሰሩ እድል ከመፍጠር አኳያ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ከፍተኛ ሚናን ይጫወታሉ:: በተመሳሳይ Exley and Dennick (2004፣ 15)ም እንደሚያስረዱት፡

> ምንም እንኳን፣ በርካታ የንዑስ ቡድን መማር ክፍለ ጊዜያትን ያለ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የተሳታፊዎቹን ልምድና ዕውቀትን መሰረት በማድረግ ብቻ ማካሄድ ቢቻልም፣ አንዳንዴ ግን የመርጃ መሳሪያዎችን መጠቀም የግድ የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል:: ... በዚህ ጊዜ እንደ መፅሀፎችን፣ ወርክሽቶችን፣ የተባዙ ጽሁፎችን፣ ፖስታዎችን፣ ካርዶችን፣ ትራንስፓረንሲዎችን፣ ማርከሮችን፣ የስዕሎች ማንጠልጠያዎችን፣ ፍሊፕ ቻርቶችን ወዘተ. ማቅረብ ያስፈልጋል::

እያንዳንዱ ቡድን የተሰጠውን ስራ በትክክል መስራት አለመስራቱን የመከታተያ አንዱ መንገድ ደግሞ በማጠቃለያ ወቅት የስራ ውጤቶቻቸውን ማዳመጥ ነው:: በመሆኑም መምህራኑ የሰዓት አጠቃቀማቸውን በማስተካከል፣ በቂ የትምህርት ማጠቃለያ ሰዓት ሊኖራቸው ይገባል (Westberg and Jason, 1996፣ Exley and Dennick 2004)::

በአጠቃላይ በንዑስ ቡድን ማስተማር ክትትል ወቅት መምህራን የሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው Westberg and Jason (1996፣109) በሚከተለው መልኩ ይዘረዝራሉ::

- ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን አመቻች::
- የተማሪዎቹን የቡድን ስራ የሚያደናቅፉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን ተከታተል::
- የንዑስ ቡድን አባላቱ፣ በስራው ላይ እንዲያተኩሩ አድርግ::

- በቡድን ስራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ተማሪዎች ካሉ፣ ተማሪዎቹን በማነጋገር ችግሮቹ እንዲፈቱ አድርግ::
- እገዛና ድጋፍ ለሚፈልጉ ቡድኖችና ተማሪዎች ዕገዛና ድጋፍ አድርግ::
- በቡድን አባላት መካከል አለመግባባቶች ካሉ፣ ተማሪዎችን ባሳተፈና ገንቢ በሆነ መልኩ አለመግባባቶቹ እንዲፈቱ አድርግ::
- በያንዳንዱ የቡድን ስራ ተማሪዎቹ የደረሱበትን ውጤት እንዲያቀርቡ አድርግ::
- በመጨረሻም የቡድን ስራ ውጤቶቹ እንዲቀርቡ አድርግ::

### 2.2.5. የቡድን ስራዎችን መገምገም

በንዑስ ቡድን ማስተማር፣ መምህራን ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ አንዱ ጉዳይ የንዑስ ቡድን ስራዎች ግምገማና ውጤት አሰጣጥ ነው (Johnson and Johnson 1990፣ Putnam, 1997፣ Mills 1998):: በመሆኑም፣ በቡድን የሚማሩ ተማሪዎች፣ ከያንዳንዱ የቡድን ስራ በኋላ ወይም እንደ አመቺነቱ በየመሀሉ ስራዎቻቸው ሊገመገሙ ይገባል (Putnam 1997):: Gregory and Thorley (1994፣ 181)የከፍተኛ ትምህርት የቡድን ስራ ግምገማን አስመልክተው "… በተለምዶ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን የሚገመግሙት በተናጠል ነው:: አሁን አሁን ግን ተማሪዎች የግል ችሎታቸው እንደሚገመገም ሁሉ፣ ተባብሮ የመስራት ችሎታቸውም መገምገም አለበት በሚለው የለውጥ ሂደት ላይ ነን…" በማለት የትብብራዊ መማር ክሂሎትን የመገምገም አስፈላጊነትን ያስረዳሉ::

የቡድን ስራዎችን የመገምገም አስፈላጊ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ቢያስረዱም፣ አገማገሙን አስመልክቶ ግን ልዩነቶች ይታያሉ:: የልዩነቶቹ ማጠንጠኛ ጥያቄዎችም፣ የቡድን ስራ እንዴት ይገመገማል? የቡድን ስራ ውጤት ለአባላቱ በሙሉ ተመሳሳይ መሆን አለበት ወይስ የተለያየ? ተመሳሳይ ውጤት መስጠት ተገቢ ነው? ካልሆነስ የያንዳንዱን አባል ግላዊ ተሳትፎ እንዴት መለካት ይቻላል? የሚሉት ናቸው::

በቡድን ስራ ወቅት አንዳንድ ተማሪዎች የስራ ድርሻቸውን በሚገባ ላይወጡ ይችላሉ::መምህራን ይህንን ሳያጣሩ አንድ አይነት ውጤት ለቡድኑ አባላት በሙሉ የሚሰጡ ከሆነ፣ በስራው ላይ ያልተሳተፉ ተማሪዎችን ያለ ድካም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል:: በአንፃሩ ደግሞ፣ በስራው ላይ የደከሙት ተማሪዎች የሌሎች መጠቀሚያ እንደሆኑ

ሆነ በቡድን በመስራት ያገኘውን የትምህርት እውቀትና ማህበራዊ ክሂሎት በተሻለ ሁኔታ መለካት የሚቻለው በግላዊ ግምገማ ነው(Dolmans et al 2003)፡፡

Davis (1993:5) (Johnson, Johnson and Simith 1991)ን ዋቢ አድርገው እንደሚመክሩት:-

> *የያንዳንዱን የቡድን አባል ተሳትፎ መገምገምህንና በቡድኖቹም የቡድን አባላቶቻቸው እንዴት እየሰሩ እንደሆነ እንዲያውቁ ማድረግህን እርግጠኛ ሁን፡፡ ቡድኖች አንድን ስራ ሲሰሩ፣ ከመሀከላቸው ማን የበለጠ እገዛን /ድጋፍን/ እንደሚፈልግ ማወቅ አለባቸው፡፡ ማናቸውም ቢሆኑ ስራውን በሌሎች ላይ ጥለው፣ ነፃ ሆነው ያለ ስራ መቀመጥ እንደማይችሉም ማወቅ አለባቸው፡፡...*

Putnam (1997)ና Exley and Dnnick (2004) የቡድን ስራን በመገምገም ሂደት መምህራን የሚከተሉትን አማራጮች ሊጠቀሙ እንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡

1. **ግላዊ ውጤት መስጠት**:- ተማሪዎች ስራውን በቡድን ከሰሩ በኋላ፣ በየግላቸው ስለ ስራው ዘገባ እንዲፅፉ በማድረግ፣ ከቡድን ስራው የወጡ ጥያቄዎችን በመፈተን፣ ስለ ስራው እንዲያስረዱ በመጠየቅ ወዘተ. ያላቸውን እውቀትና በቡድን ስራው ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ መለካት፡፡
2. **ቡድናዊ ውጤት መስጠት**:- ተማሪዎቹ በቡድን ለሰሩት ወይም በቡድን በክፍል ውስጥ ላቀረቡት ስራ፣ እንደስራው ጥንካሬና ድክመት አንድ ውጤት መሰጠት፣ ያንንም ውጤት እያንዳንዱ የቡድኑ አባል እንዲያገኝ ማድረግ፡፡
3. **ውጤት ማከፋፈል**:- ለቡድን ስራው አንድ ውጤት ከተሰጠ በኋላ፣ ተማሪዎቹ በቡድን ውስጥ እንዳላቸው ተሳትፎ መጠን ውጤቱን ማከፋፈል፡፡
4. **ግላዊም ቡድናዊም ውጤት መስጠት**:- ለአንድ የቡድን ስራ አንድ ውጤት መስጠት፣ ያንንም ውጤት በተመሳሳይ ሁሉም የቡድኑ አባላት እንዲያገኙ ማድረግ፣ በመቀጠል ደግሞ የቡድኑ አባላት በስራው ላይ ያደረጉትን ተሳትፎና ያገኙትን ዕውቀት በልዩ ልዩ መንገድ በመፈተን የተለያዩ ግላዊ ውጤቶችን መስጠት፡፡

በቡድን ስራ ግምገማ ወቅት ለሚፈጠሩ ችግሮች አንዱ መፍትሔ፣ ግምገማው መስፈርትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህ የመገምገሚያ መስፈርትም ከመነሻው ለተማሪዎቹ ግልፅ ሊደረግላቸው ይገባል (Stone 1994)፡፡

መምህራን እነሱ ከሚያደርጉት ግምገማ በተጨማሪነት፣ ተማሪዎቹን ስለ ራስ ግምገማ (Self-assessment) እና ስለ ቢጤ ግምገማ (peer assessment) በማስተማር፣ በየጊዜው ራሳቸውንና ጓደኞቻቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ አለባቸው (Gregory and Thorley 1994)::

### 2.2.6. የንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደት ላይ ዕብረቃ (Reflection)ማካሄድ

እንደ ማንኛውም የማስተማር ሂደት፣ የንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደት የሚጠይቀው አንዱ ተግባር፣ የማስተማር ሂደቱ ምን ይመስል እንደነበር ለመረዳት፣የማስተማር ዕብረቃ (Teaching Reflection) ማካሄድ ነው። ይህንን አስመልክተው Jaques (1998) እንደሚያስረዱት "... ማንኛውም የማስተማር ሂደት፣ በተለይ ደግሞ የቡድን ማስተማር፣ በሂደቱ ላይ በተሳተፉ ሁሉ መለስ ብሎ ቢገመገም ጠቃሚ ይሆናል:: እንዲህ ከሆነ፣ ለተገኘው ውጤት በሂደቱ የተሳታፉ በሙሉ በጋራ ሃላፊነትን ይወስዳሉ::" Botes (1994፣ 23) ከዚህ ሃሳብ በተቀራረበ መልኩ፣ የማስተማር ሂደት ላይ ዕብረቃ የማካሄድ አስፈላጊነት:

> *የማስተማር ዕብረቃ (Teaching Reflection) እንዴት ማስተማር እንደሚገባ የማወቂያ መንገድ፣ እንዲሁም ራስን የመገምገሚያ ዘዴ ነው:: በትክክለኛ መስመር እየተጓዘን መሆናችንን ወይም ልናስተካክለው የሚገባን ነገር መኖሩን መለስ ብለን በመፈተሽ ሳናረጋግጥ የምናደርገው የማስተማር ሂደት፣ የጭለማ ውስጥ ማስተማር ነው::*

በማለት ይገልፃሉ:: አያይዘውም እንደሚያስረዱት፣ የማስተማር ዕብረቃን ማካሄድ፣ ከተማሪዎቹ ጋር የነበረኝ ግንኙነት እንዴት ነበር? ጥያቄ ሲጠይቁኝ አመላለሴ እንዴት ነበር? ፊጥሬው የነበረው የክፍል ውስጥ ድባብ ምን ይመስል ነበር? የማስተማር ሂደቱ በዕቅዱ መሰረት የተካሄደ ነበር? ወይስ ደመነፍሳዊ ሃደት ነበር? ተማሪዎቼ ተሳታፊዎች ነበሩ? ትምህርቱ በጥሩ ሁኔታ ያልተካሄደው ለምንድነው? ትምህርቱ ለምን በሚገባ ተሳካ? የሚሉትን አይነት ጥያቄዎች ለማንሳትና ለመመለስ ያስችላል:: ይህም የወደፊት የማስተማር አቀራረብን እያሻሻሉ ለመሄድም ይረዳል:: Larrivee (2005) በበኩላቸው በተለይ ከቡድን ማስተማር ሂደት በኋላ መምህራን የማስተማር ሂደታቸው ላይ ዕብረቃን ሲያካሂዱ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት እንደሚገባቸው ይገልፃሉ::

- በክፍለ ጊዜው ያለ ስራ የባከነ ረዥም ጊዜ ነበር?
- በሂደቱ ላይ ከዕቅዱ አንፃር ያልተጠበቀ የሰዓት፣ የአቀራረብና የቅደም ተከተል ለውጦች ነበሩ?
- የተሰጡት ስራዎች ለተማሪዎቹ ጠቃሚና ተገቢ ነበሩ?
- የቡድን ስራዎቹ አነቃቂና ሀሳብ የሚያጭሩ (Thought Provoking) ነበሩ?
- እያንዳንዱ ተማሪ እኩል የመሳተፍና የመማር ዕድል አግኝቷል?
- ብዙ ያልተሳኩ ነገሮች ነበሩ?
- የእርስ በርስ ፉክክር ጎልቶ ይታይ ነበር?

Petty (2004) እንዲህ አይነቱ ጥያቄዎችን እያነሱ ወደ ኋላ በመመለስ የማስተማር ሂደት ላይ ዕብረቃን (Reflection) የማካሄድ ተግባር ፣ ቀደም ብሎ የታቀደውን የትምህርት አላማና ግብ መሰረት ማድረግ እንደሚገባው በማስገንዘብ፣ ለዚሁ ተግባር ተብሎ በቅድሚያ የተዘጋጀ ቅፅን በመሙላት ወይም በሀተታ መልክ በፅሁፍ ሀሳብን በመግለፅ ማካሄድ እንደሚቻል ይገልፃሉ:: Botes (1994) እንሚያስረዱት ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ሁሉም መምህር የየእለት ማስተማር ሂደቱን መለስ ብሎ መቃኘቱ ወይም ማሰቡ አይቀርም:: ይህ ግን የማስተማር ሂደቱ ላይ በሚገባ ዕብረቃን (Reflection) አካሂዷል አያሰኘውም:: ምክንያቱም የትምህርት ሂደት ላይ ዕብረቃን (Reflection) ማካሄድ ራሱን የቻለ ጊዜ ተሰጥቶት፣ በሰከነ አእምሮ በጥንቃቄ የሚተገበር ጉዳይ በመሆኑ ነው ሲሉ ያስረዳሉ::

ይህ ዕብረቃ የማካሄድ ተግባር፣ የመምህራን ብቻ ሲሆን እንደማይገባውና ተማሪዎችም ቢሆኑ የራሳቸውን የመማር ሂደት መለስ ብለው መገምገም እንደሚገባቸው፣ ለዚህም መምህራኑ ሃላፊነት እንዳለባቸው Putnam (1997፣17) "ተማሪዎች በመረዳዳት ተግባራትን እንዲያከናውኑ እንደሚደረግ ሁሉ፣ የቡድን ግባቸውንም ምን ያህል ስኬታማ እንዳደረጉ መለስ ብለው እንዲገመግሙ ማበረታታት ይገባል:: ግምገማቸው ችግር መኖሩን ካመለከተ፣ ተማሪዎቹ የችግሩን ምንጭ በመለየት፣ የሚፈታበትን መንገድ ይቀይሳሉ:: ..." ሲሉ ይገልፃሉ:: Dolmans, et al (2003) ይህንኑ ሀሳብ በመደገፍ እንደሚገልፁት፣ በቡድን መማር ማስተማር የተለያዩ ሂደቶች ማለትም፣ የቡድን መማርን በማቀድ፣ የቡድን ስራዎችን በመከታተልና በመገምገም ተማሪዎቹ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ መምህራን መርዳት አለባቸው:: ለዚህም፣ በማስተማር ሂደት ላይ ዕብረቃ (Reflection) ማካሄድ አንዱና ዋናው መንገድ ነው::

Atkins et Al (1996) Cristison (1990፣213)ን ዋቢ አድርገው የተማሪዎቹን በቡድን መማር ሂደት የራስ ግመገማና የቢጤ ግምገማን ማድረግ አስፈላጊነትን በተመለከተ እንደሚያስረዱት

"ተባብሮ በመስራት ሂደት ላይ ተማሪዎች የግዴታ ዕብረታን ማካሄድ አለባቸው ... መምህራን ተማሪዎቹ የራሳቸውን ወይም የቡድን አባላቶቻቸውን የቡድን መማር ሂደት መገምገም እንዲችሉ፣ ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ እንዲሁም የሚሞሉ ፎርሞች አዘጋጅቶ በመስጠት ሊረዷቸው ይችላሉ::" Davis (1993:5) (Johnson, Johnson and Simith 1991)ን መሰረት አድርገው:-

> *በያንዳንዱ የቡድን ስራ፣ ተማሪዎች በቡድን በመስራታቸው ምን ያህል ስኬታማ እንደሆኑና እንዳልሆኑ እንዲገመግሙ እድሉን ስጣቸው:: የቡድን ስራውን እየሰሩ ሳለም፣ አንዴ ወይም ሁለቴ፣ አባላቱ ቆም ብለው፣ የሚከተሉት ሁለት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ አድርግ:: እያንዳንዱ አባል ለስራው ጠቃሚ የሆነ ምን አይነት ተግባርን እያከናወነ ነው? ቡድኑ ከነበረበት ሁኔታ እንዲሻሻል እያንዳንዱ የቡድን አባል ምን አይነት አስተዋጽኦን እያደረገ ነው? በፕሮጀክቱ መጨረሻ ደግሞ፣ የቡድን አባላቱ አጠቃላይ የቡድኑንና የአባላቱን ውጤታማነት በመገምገሚያ ፎርም ላይ እንዲገልፁ አድርግ:: ...*

### 2.2.7 የክለሳ ድርሳናት ሃሳቦች ማጠቃለያ

በዚህ የክለሳ ድርሳናት ምዕራፍ የንዑስ ቡድን ማስተማር ምንነትን፣ ጠቀሜታንና አተገባበርን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ያቀረቧቸው ሃሳቦች ተዳሰዋል። ከነዚህ ሃሳቦች መረዳት እንደሚቻለው፣ የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ፣ ትምህርትን ንቁና አሳታፊ አድርጎ ለማቅረብ ከሚረዱ የተማሪ ተኮር ዘዴዎች አንዱ እንደሆነ ነው። ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ማህበራዊ ክሂሎትን (social skills)ጭምር ለማዳበር የሚረዳ በመሆኑ፣ በተለይ ባለፉት ጥቂት አስርት አመታት ተቀባይነቱ እየጨመረ ለመሄድ ችሏል። ይሁን እንጂ፣ አሁንም ቢሆን በርካታ መምህራን ዘዴውን በሚገባ የመገንዘብና የመተግበር ችግር ይታይባቸዋል።

እንደ አብዛኞቹ ምሁራን ሃሳብ ተማሪዎች በቡድን ስለሆኑ ብቻ ትብብራዊ የቡድን መማር ተገኝቷል ማለት አይቻልም። Nunan(1992፣34-35) (D.W. Johnson and R.T.Johnson 1987፣ 1989፣ D.W. Johnson et al 1990፣ Brabdit 1987) ዋቢ አድርገው እንሚገልፁት የተሳካ የቡድን መማር ተካሂዷል ማለት የሚቻለው፣ የሚከተሉት አምስት የቡድን መማር መገለጫዎች ሲታዩ ነው።

1. ጤናማ የእርስ በርስ ግንኙነት ( Positive Interdependence) ሲኖር:- ተማሪዎቹ ለጋራ የቡድን ዓላማ በመተባበርና በመረዳዳት መንፈስ መስራት በሌላ አገላለፅ፣ እያንዳንዱ የቡድን አባል ስለራሱ መማር ብቻ ሳይሆን ስለሌላውም መማር የሚጨነቅ ሲሆን።

2. ግለሰባዊ ተጠያቂነት (Individual Accountability) ሲሰፍን :- እያንዳንዱ የቡድን አባል የሃላፊነት ስሜት ተሰምቶት፣ የራሱን የስራ ድርሻ በመወጣት ለቡድኑ ግብ መሳካት የበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያደርግ ሲሆን። በሌላ አገላለፅ፣ የቡድን ስራው ጫና በጥቂቶች ላይ ብቻ ተጭኖ ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ነፃ የሚሆኑበት ሁኔታ ቀርቶ፣ እያንዳንዱ የቡድን አባል በቡድን ስራው ላይ እኩል ተሳትፎ የሚያደርግበት ሁኔታ ሲፈጠር።

3. የፊት ለፊት ግንኙነት( Face-to-Face Interaction) ሲኖር:- የቡድኑ አባላት ውይይት፣ ክርክር ወዘተ. በሚያካሂዱበት ወቅት ሁሉም የቡድኑ አባላት ፊት ለፊት የሚተያዩበት ሁኔታ ሲኖር።

4. ተገቢ የማህበራዊ ክሂሎት(Sufficient Social Skills) ሲኖር:- እንደ የቡድን አመራር ክሂል ፣ የተግባቦት ክሂል፣ እርስ በርስ መተማመን የመፍጠር ክሂል፣ ግጭትን የመፍታት ክሂል ወዘተ. የመሳሰሉትን ማህበራዊ ክሂሎት በማስተማር የተማሪዎቹን ተባብሮ የመስራት ችሎታ ማሳደግ ሲቻል።

5. የቡድን ፅብረቃን( Team Reflection) ማካሄድ ሲቻል:- በየተወሰነ ጊዜያት የቡድን አባላት ፣ የቡድን መማር ሂደታቸውን ቆም ብለው በመገምገም ጥንካሬና ድክመታቸውን መለየት፣ ከድክመታቸውም እየተማሩ ቀጣይ የቡድን መማር ሂደታቸውን ማሻሻል የሚችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር።

በመሆኑም፣ በዚህ ምዕራፍ ስር የተጠቀሱ በርካታ ምሁራን እንደሚያስረዱት፣ እነዚህ ሁኔታዎችን በሚያሟላ መልኩ የንዑስ ቡድን ማስተማርን ተግባራዊ ማድረግ ቀላል ተግባር አይደለም። እንደ ብዙዎቹ፣ ምሁራን ሃሳቦች፣ የተሳካ የቡድን ማስተማርን ተግባራዊ ለማድረግ በቡድን ማስተማር ሂደት መምህራን ስድስት ዋና ተግባራትን በጥንቃቄ ማከናወን ይኖርባቸዋል። እነሱም፣ ለቡድን ማስተማር በቂ ዝግጅት ማድረግ፣ ቡድኖችንና ክፍሎችን በሚገባ ማደራጀት፣ የቡድን መማር ዓላማንና የቡድን ስራን ግልፅ ማድረግ፣ በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎችን ሂደት ትኩረት ሰጥቶ መከታተል፣ ተጨባጭ የሆኑ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ የቡድን ስራዎችን በመገምገም እንዳስፈላጊነቱ ግላዊ ወይም ቡድናዊ ውጤትን መስጠትና በየጊዜው የቡድን ማስተማር ሂደቱ ላይ ፅብረቃ በማድረግ የማስተማር ሂደቱን እያሻሻሉ መሄድ ናቸው።

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ተጠኚዎች አመራረጥ፣ የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የመረጃ መተንተኛ ስልቶች የሚከተሉትን ይመስላሉ::

## 3.1. የተጠኚዎች አመራረጥ

### 3.1.1. የኮሌጁ አመራረጥ

በሀገራችን ካሉት በርከታ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች፣ የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ለጥናቱ የተመረጠው፣ በሶስት ዋና ምክንያቶች ነው:: አንደኛ አጥኚው የሚሰራበት ኮሌጅ በመሆኑ የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብም ሆነ ሌሎች ትብብሮችን ለማግኘት አመቺ ሆኖ በመገኘቱ፣ ሁለተኛ አጥኚው በስራ ላይ በነበረበት ወቅት በቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር ዙሪያ ችግሮች እንዳሉ በማስተዋሉ፣ ሶስተኛ ኮሌጁ ስራ ከጀመረ ገና አምስተኛ ዓመቱ በመሆኑ በኮሌጁ ችግሮች ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች በጣም አነስተኛ በመሆናቸው ነው::

### 3.1.2. የተጠኚ መምህራን አመራረጥ

በኮሌጁ የመደበኛ ፕሮግራም ያሉት የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን ሶስት ናቸው:: ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ ሁሉም በመረጃ ሰጪነት ቢሳተፉ ጥናቱን የበለጠ ውጤታማ እንደሚያደርገው በማመን የመምህራኑ ምርጫ በጠቅላይ ንሞና (comprehensive sampling) ዘዴ ተካሂዷል:: በመሆኑም ሁሉም በጥናቱ ተካተዋል::

### 3.1.3. የተማሪዎች አመራረጥ

በሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ መደበኛው ፕሮግራም በአማርኛ ትምህርት ክፍል ውስጥ የ1ኛ፣ የ2ኛ እና የ3ኛ ዓመት ተማሪዎች አሉ:: ከነዚህ ተማሪዎች ውስጥ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስን የሚወስዱት የ2ኛ አመት ተማሪዎች ብቻ ናቸው:: እነዚህ ተማሪዎች ብዛታቸው 108 ሲሆን 23ቱ ወንዶች፣ 85ቱ ደግሞ ሴቶች ናቸው:: የሚማሩትም በሦስተ ክፍሎች ሲሆን፣ ከያንዳንዱ ክፍል ግማሽ ያህሉን የተማሪዎቹን ቁጥር ለመወከል እንዲቻል 20 ተማሪዎችን በድምሩ 60 ተማሪዎችን በየክፍሉ ዕጣ እንዲያወጡ በማድረግ፣ በቀላል የእጣ ንሞና (Simple Random Sampling) በመምረጥ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል::

## 3.2. የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች

የዚህ ጥናት መረጃዎች የተሰበሰቡት በሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ነው:: እነሱም፣ ቃለመጠይቅ፣ የክፍል ውስጥ ምልከታና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው:: ቃለ መጠይቁ ከክፍል ውጭ ስለሚካሄደው የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር መረጃን ለማሰባሰብ በዋና የመረጃ ምንጭነት ያገለገለ ሲሆን፣ የክፍል ውስጥ ምልከታው ደግሞ በክፍል ውስጥ ስለሚደረገው የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር በዋና የመረጃ ምንጭነት አገልግሏል:: የጽሑፍ መጠይቁ ደግሞ ለሁለቱም ማለትም ከክፍል ውጭም በክፍል ውስጥም ለሚደረጉት የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበሮች በደጋፊ የመረጃ ምንጭነት አገልግሏል:: የያንዳንዱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አተገባበር የሚከተለውን ይመስላል::

### 3.2.1. ቃለመጠይቅ

ለዚህ ጥናት አንዱ ዋና የመረጃ ማሰባሰቢያ ተደርጎ የተመረጠው ቃለ መጠይቅ ነው:: ቃለ መጠይቁ የተደረገውም በ2000 ዓ.ም መሰረታዊ አማርኛ ኮርስን ላስተማሩ ሶስት መምህራን ነው:: ቃለመጠይቁንም ለማድረግ በቅድሚያ በክለሳ ድርሳናት ክፍል የቀረቡትን፣ በንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ መምህራን ሊያከናውኗቸው የሚገቧቸው ተግባራትን (ለቡድን ማስተማር መዘጋጀት፣ ቡድኖችንና ክፍሎችን ማደራጀት፣ የቡድን ስራ አላማንና የቡድን ስራን መግለጽ፣ የቡድን ስራዎችን መከታተል፣ የቡድን ስራዎችን መገምገምና የቡድን ማስተማር ዕብረቃ ማካሄድ) መሰረት በማድረግ 16 ከፊል ነፃ (Semi structured) ጥያቄዎች በፅሁፍ ተዘጋጅተዋል:: የተዘጋጁት ጥያቄዎችንም ሁለት አማርኛን በማስተማር የድህረ ምረቃ ተማሪዎችና አንድ በስነ-ትምህርት የድህረ ምረቃ ፕሮግራም የሚከታተል ተማሪ በድምሩ ሶስት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች እንዲመለከቱትና አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል:: በአስተያየታቸው መሰረትም መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበታል:: በተጨማሪም፣ የጥናቱ አማካሪ እንዲያዩት ተደርጎ ቃለ መጠይቁ ተካሂዷል:: በቃለ መጠይቁ ወቅትም የመምህራኑ ምላሾች በሶስት የተለያዩ ካሴቶች በመቅረፀ ድምፅ ተቀድተዋል::

### 3.2.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ

ለዚህ ጥናት ሌላው ዋና የመረጃ ማሰባሰቢያ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን ተማሪዎችን በቡድን አደራጅተው ሲያስተምሩ የተደረገ የክፍል ምልከታ ነው:: ምልከታው የተሳካ እንዲሆን በቅድሚያ ለመምህራኑ የምልከታውን አላማ በማስረዳት፣ በቡድን የሚያስተምሩባቸውን ቀናትና የክፍለ ጊዜ ፕሮግራም አጥኚው መዝግቦ ይዟል:: በዚህም መሰረት፣ አምስት የቡድን ማስተማር ዘዴ ተግባራዊ የተደረገባቸው ክፍለ ጊዜዎችን ለመመልከት ተችሏል:: ምንም እንኳን፣ አጥኚው ስምንት ምልከታዎች ለማድረግ ቢያቅድም፣ ከነበረው የጊዜ ጥበትና መምህራኑ በቡድን ለማስተማር ከነበራቸው ዕቅዶች አንፃር ከአምስት በላይ ምልከታዎችን ለማካሄድ አልተቻለም::

በምልከታውም ሂደት የመምህራኑን የቡድን ማስተማር አተገባበርን ለመመዝገብ የሚያስችል የክፍል ምልከታ መከታተያ ቅፅ (classroom observation checklist) "SEAL" በድረገጹ ያቀረበውን ለዚህ ጥናት እንዲያመች ተደርጎ ከተዘጋጀና የጥናቱ አማካሪ እንዲያዩት ከተደረገ በኋላ በስራ ላይ ውሏል:: በቅፁ ውስጥ ከላይ በቃለ መጠይቅ ጥያቄ ወቅት ትኩረት የተሰጣቸው የቡድን ማስተማር ዘዴ ዋና ዋና  ተግባራት እንዲካተቱ ሆኗል:: ከያንዳንዱ ተግባር ፊት ለፊትም ተግባሩ በምልከታው ወቅት ነበር /አልነበረም የሚሉ ሳጥኖች እንዲይዝ ተደርጓል:: በተጨማሪም፣ ተግባሩ መተግበር አለመተግበሩን ብቻ ሳይሆን አተገባበሩ ምን መልክ እንደነበረው ለመዘርዘር የሚያስችል ባዶ ቦታ ከያንዳንዱ ተግባር ፊት ለፊት እንዲኖር ተደርጓል:: አጥኚው በምልከታው ወቅት ከያንዳንዱ ተግባር ፊት ለፊት ነበረ ወይም አልነበረም በሚለው ስር የ "✓" ምልክት በማድረግና ነበር ወይም አልበረም የተባሉበትን ዝርዝር ምክንያትና ማብራሪያ በአንፃሩ በሚገኘው ሰፊ ክፍት ቦታ በዝርዝር በመፃፍ የምልከታ መረጃውን ለመሰብሰብ ችሏል::

ከዚህ በጽሁፍ ከተዘገበው የምልከታ መረጃ ጎን ለጎን፣ የክፍል ውስጥ የቡድን ማስተማር አተገባበሩን በመቅረፅ ምስል ቀረፃ (Video-recording) እና ፎቶግራፍ በማንሳት መረጃውን እንዲጠናከር ተደርጓል:: መቅረፀ ምስሉም ሆነ ፎቶግራፍ ማንሳቱ የተካሄደው በባለሙያ ሲሆን አጥኚው ቀደም ብሎ የመቅረፀ ምስሉ ቀረፃና የፎቶ ግራፍ ማንሳቱን አላማ ለባለሙያው አስረድቷል:: ከዋናዎቹ ቀረፃዎች በፊትም የተማሪዎቹን የመቅረፀ ምስል ትኩረት ለመቆጣጠር በያንዳንዱ ክፍል ከ15-20 ደቂቃ የሚደርስ የማስመሰል ቀረፃ (false-recording) የተደረገ ሲሆን

ዋናውን ቀረፃን በተመለከተ ግን በሶስቱም ክፍሎች ለአንድ አንድ ሙሉ ክፍለ ጊዜያት (50 ደቂቃ) በድምሩ የ 2 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ቀረፃ ተካሄዷል:: ከቀረፃው በኋላ አጥኚው የመቅረፀ ምስል ካሴቶቹን ደጋግሞ በማየት፣ በመከታተያ ቅፁ ሳይመዘገቡ የቀሩ ነጥቦችን አሟልቶ ለመመዝገብ ችሏል::

### 3.2.3. የፅሁፍ መጠይቅ

ሶስተኛው ደጋፊ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ የጽሁፍ መጠይቅ ነው:: መጠይቁ የቀረበውም የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስን ለሚከታተሉና በእጣ ጥሞና ዘዴ (Simple Random Sampling) ለተመረጡ የ2ኛ ዓመት ተማሪዎች ነው:: መጠይቁም ሶስት ክፍሎች አሉት:: አንደኛው ስማቸውን ሳይጨምር ስለራሳቸው አጠቃላይ መረጃ የሚሰጡበት ክፍል ነው:: ሁለተኛውና ሶስተኛው ክፍሎች ደግሞ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራኖቻቸውን የቡድን ማስተማር አተገባበር በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡባቸው ናቸው:: በክፍል ሁለት የቀረቡት ጥያቄዎች የምርጫ ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ እያንዳንዳቸው አምስት አማራጮች ይዘዋል:: እነሱም ሁል ጊዜ፣ አብዛኛውን ጊዜ፣ አንዳንድ ጊዜ፣ አልፎ አልፎና በጭራሽ የሚሉ ናቸው:: እነዚህ አማራጮች የተመረጡበት ምክንያት አንድ ተደጋግሞ የሚታይ ነገር ድግግሞሽን ለመለካት ጥሩ አማራጮች ሆነው በመገኘታቸው ነው (ያለው እንደወቀ 1996):: አማራጮቹ (በተለይ አንዳንድ ጊዜ እና አልፎ አልፎ የሚሉት) ተማሪዎቹን እንዳያሻሟቸው ለማድረግ፣ አማራጮቹ የሚይዙት ነጥብ በቁጥር ከ5-1 መሆኑ ከምርጫዎቹ ጋር አብሮ ተሰጥቷል:: ሶስተኛው የመጠይቁ ክፍል ደግሞ፣ ከፊል ነፃ (Semi-structured) የሆኑ ጥያቄዎችን የያዘ ነው:: ለያንዳንዱ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጡባቸው በቂ ባዶ ቦታዎችም ከጥያቄዎቹ ስር ተሰጥቷል::

በምርጫ ክፍሎቹም ሆነ በፅሁፍ በሚመለሰው ክፍል ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች እንደ ቃለመጠይቁና የምልከታ ቅፁ ሁሉ መሰረት ያደረጉት ጥናቱ ይዟቸው የተነሳውን ጥያቄዎችና በክለሳ ድርሳናት ምዕራፍ የተነሱትን ሀሳቦች ነው:: በተቻለ መጠን በቃለ መጠይቁና በምልከታ ቅፁ ከተዘረዘሩት ሀሳቦች ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው ጥረት ተደርጓል:: እነዚህ መጠይቶችን ተማሪዎች እንደሚሏቸው ከመደረጉ በፊትም በ15 ተማሪዎች ላይ የሙከራ ጥናት (Pilot study) ተደርጓል:: ከሙከራ ጥናቱ በመነሳትም ጥያቄዎቹን የማሻሻልና ቅደም ተከተላቸውን የማስተካከል ስራ ተሰርቷል:: ከዚህ በኋላ ተማሪዎቹ እንደሞሏቸው ተደርጓል::

በአጠቃላይ በእነዚህ ሶስት የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ የጥናቱ ትንተና በሚከተለው መልኩ ተካሂዷል::

## 3.3. የጥናቱ መረጃ አተናተን

ይህ ጥናት ስለ አንድ ርዕስ ጉዳይ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን እያመሳከረ የሚገልፅ፣ የሚተነትንና የሚያብራራ ገላጭ ምርምር ነው:: በመሆኑም የመረጃ አተናተኑ የአይነታዊ ምርምር (qualitative research) ፈለግን የተከተለ ነው::

የጥናቱን መረጃ ለመተንተን በቅድሚያ በመቅረፀ ድምፅ የተቀረፁ የመምህራኑ ምላሾች ወደ ፅሁፍ ተገልብጠዋል:: እነዚህን በወረቀት የተገለበጡ የቃለ መጠይቅ ምላሾች በስድስቱ ቀደም ሲል በተጠቀሱት ጭብጦች እና በነሱ ስር በሚካተቱ ንዑሳን ጭብጦች እንዲደራጁ ተደርጓል::

የምልከታ ቅፅ መረጃዎቹንም በመቅረፀ ምስሉ ከሚታየው ጋር በማመሳከር መረጃውን የተሟላ ለማድረግ ጥረት ከተደረገ በኋላ፣ በሶስት ዋና ጭብጦች (የንዑስ ቡድንና ክፍሎችን ማደራጀት፣ የቡድን ስራዎችን ግልፅ ማድረግና የንዑስ ቡድን ስራዎችን መከታተል) በሚሉ ስር በማጠቃለል በሰንጠረዥ ተደራጅተዋል::

ከላይ እንደተገለፀው 60 ተማሪዎች መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረገ ቢሆንም ሁለት መጠይቆች ተሟልተው ባለመገኘታቸው፣ በመረጃ መረጣ ወቅት እንዲወጡ ተደርጓል:: ቀሪዎቹ 58 መጠይቆች ግን በተሟላ መልኩ ምላሽ የተሰጡባቸው በመሆናቸው፣ ለጥናቱ በመረጃነት ውለዋል:: በመጠይቁ ክፍል ሁለት የተገኙት ምላሾች ታሊ ከተደረጉ በኋላ በጭብጥ በጭብጣቸው በሰንጠረዥ እንዲደራጁ ተደርጓል:: ለያንዳንዱ ጉዳይ የተገኙ ምላሾችም በተማሪ ቁጥርና መቶኛ(%) ተሰልተው ቀርበዋል:: በክፍል ሶስት በፅሁፍ የተሰጡ ምላሾችንም በመልቀም እንደ አስፈላጊነቱ፣ ምን ያህሉ ተማሪ ምን ብሎ ምላሽ ሰጠ? የሚለው የምላሽ ድግግሞሽ በመቶኛ ተሰልቷል::

ከነዚህ የማደራጀት ስራዎች በኋላ፣ ከያንዳንዱ የመረጃ ምንጭ የተገኙት መረጃዎች በተናጠል ተተንትነዋል:: ትንተናው ከገለፃ በተጨማሪ በሰንጠረዥና በፎቶ ግራፍ ጭምር ተደግፎ ቀርቧል:: ከትንተናው በኋላ በያንዳንዱ ጭብጥ ላይ ከሶስቱ የመረጃ ምንጮች የተገኙትን የትንተና ውጤቶች፣ እርስ በርስ ያላቸው የሀሳብ ዝምድን እንዲሁም በክለሳ ድርሳናት ከተነሱት ሀሳቦች ጋር ያላቸውን የሀሳብ ተዛምዶ በማመሳከር ማብራሪያ ተሰጥቷል::

## ምዕራፍ አራት
## የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ

### 4.1. የመረጃ ትንተና

በዚህ ንዑስ ክፍል ከተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች የተገኙ መረጃዎች እየተተነተኑ ይቀርባሉ::

#### 4.1.1. ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ምላሽ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጭ፣ ለሶስቱ የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራን የቀረበው ቃለ መጠይቅ መሆኑ በቀዳሚው ምዕራፍ ተገልጿል:: ከቃለ መጠይቁ የተገኙት መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል::

##### 4.1.1.1. የመምህራኑ ግላዊ መረጃ

ሰንጠረዥ አንድ: የመምህራኑ ግላዊ መረጃ

| ተ.ቁ | መምህራን | የትምህርት ደረጃቸው | የአገልግሎት ዘመን | የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መ1 | ቢ..ኤ.ዲ.. በአማርኛ | 9 ዓመት | ተከታትለዋል |
| 2 | መ2 | ኤም.ኤ.አማርኛን በማስተማር | 20 ዓመት | ተከታትለዋል |
| 3 | መ3 | ኤም.ኤ.አማርኛን በማስተማር | 7 ዓመት | ተከታትለዋል |

ከነዚህ መምህራኑ ከሰጧቸው ግላዊ መረጃዎች በመነሳት፣ መምህራኑ በማስተማር ሙያ ከፍተኛ ልምድና ሙያዊ ብቃት እንዳላቸው መገመት ይቻላል::

##### 4.1.1.2. የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ የማድረግ መንስዔ

መምህራኑ የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴን ምን ያህል እንደሚያስተምሩበት ለቀረበላቸው ጥያቄ:

... ርዕሰ ጉዳዩ ለቡድን ስራ የሚጋብዝ ከሆነ የቡድን ስራን ... ተግባራዊ አደርጋለሁ /መ1-5/:: ... ለተማሪዎቹ በቡድን ሆኖ ተከፋፍሎ ለመስራት አመቺ ሆኖ ሲገኝ ሁሉ አሰራለሁ /መ2-6/:: ... በየንዑስ ምዕራፎቹ እንደኮርሱ ባህሪ በቡድን የሚሰሩበት ... አጋጣሚዎች አሉ /መ3-6/::

በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል:: በቡድን ሆኖ መማር ለተማሪዎች የሚኖረውን ጠቀሜታ እንዲያስረዱ ለቀረበላቸው ጥያቄም የሚከተሉትን ነጥቦች ዘርዝረዋል::

- ያለ ሀፍረትና ያለ ፍርሃት ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ያደርጋል::
- እርስ በርስ እንዲማማሩ ያደርጋል::
- ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ ይረዳል::
- አዳዲስ ሀሳቦችን እንዲያፈልቁ እድል ይፈጥራል::
- ያሳትፋል::
- ያስተሳሰብ ለውጥ ያገኙበታል::
- እውቀታቸውን ለማሻሻል ይረዳል::
- የቋንቋ ክሂሎችን ያዳብራል::

ስለ ቡድን ማስተማር ዘዴ ግንዛቤ የፈጠሩላቸውን ሁኔታዎች መ2 እና መ3 በኮሌጅ የተከታታሉት የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም ብቻኛ እንደሆነ "... ከሀየር ዲፕሎማ ውጭ ለዚህ የቡድን ስራ ልምድ ያገኘሁበት ሌላ ማንበቢያ ነገር የለም..." (መ2-21):: በማለት አስረድተዋል:: መ1 ግን ከሁለቱ መምህራን በተለየ ሁኔታ "... በመምህራን ስልጠና ላይ በተለይ የቱሶ ፕሮግራም ከመጣም ወዲህ፣ ከዚያ በፊትም የቡድን ስራዎችን በተመለከተ አንዳንድ ስልጠናዎችን ወስጃለሁ" (መ1-9) በማለት ስለ ቡድን ማስተማር ግንዛቤ ያዳበሩባቸው ስልጠናዎች በርካታ እንደሆኑ ገልፀዋል::

ከዚህ በላይ መምህራኑ ከሰጧቸው ምላሾች መረዳት እንደሚቻለው፣ ሁሉም መምህራን በመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ የማስተማር ሂደት፣ አስፈላጊ ነው ብለው ሲገምቱ የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋሉ:: ይህንንም የሚያደርጉት በቡድን መማር ለተማሪዎች ተሳትፎን ከመፍጠሩ በተጨማሪ፣ በራስ የመተማመን መንፈስን ለማዳበር፣ ልምድን

ለመለዋወጥ፣ የቋንቋ ክሂሎትን ለማዳበር፣ እውቀትን ለማሻሻልና ያስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ጠቀሜታ አለው ብለው ስለሚገምቱ እንደሆነ ምላሻቸው ያስረዳል::

### 4.1.1.3. የመምህራኑ የንዑስ ቡድን ማስተማር ዝግጅት

መምህራኑ በንዑስ ቡድን ለማስተማር ሲያስቡ ምን አይነት ቅድመ ዝግጅትን እንደሚያደርጉ ለማወቅ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል:: ለጥያቄው (መ1-11፣12) "ሁል ጊዜ አይደለም"፤ በእርግጥ እኔ ገብቼም ቅድመ ዝግጅት ሳላደርግም የምሰጥበት ጊዜ አለ:: ... አንዳንድ ጊዜ ምንድነው የማደርገው፣ በቡድን የሚሰሯቸው ጥያቄዎች አዘጋጃለሁ ዕሬ ... አልፎ አልፎ ነው ሁል ጊዜ አይደለም::..." በማለት ሲያስረዱ፣ (መ3-11) "መጀመሪያ የምሰጠውን ስራ እለያለሁ:: ከዚያ ተማሪዎች ምን ምን ማከናወን እንዳለባቸው እወስናለሁ ..." ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል:: መ2 በበኩላቸው እንዳስረዱት:

> *የቡድን ስራ ከመስጠቴ በፊት፣ በምን በምን ነጥቦች ላይ መወያየት ይችላሉ? የሚለውን መጀመሪያ አዘጋጃለሁ:: የሚወያዩባቸውን ነጥቦች መጀመሪያ ማቀድ አለብኝ:: ተማሪዎቹን ምን ያህል ያወያያል? ምን ያህል ያሳትፋል? በቡድን ያሉ አባላት ሁሉም እኩል ለመካፈል የሚችሉበት አይነት ጥያቄ ነው አይደለም? የተለያየ ሀሳብ ማፍለቅ የሚችሉባቸው ጥያቄዎች መሆናቸውን አረጋግጣለሁ:: ካልሆነ ደግሞ፣ እኔ ተጨማሪ ጥያቄዎችን አዘጋጅቼ እንዲወያዩ አመቺ ሁኔታ እፈጥራለሁ:: (መ2-9)*

እነዚህ የመምህራኑ ምላሾች እንደሚያሳዩት፣ በንዑስ ቡድን ማስተማር ዝግጅት ወቅት ትኩረት የሚሰጡት፣ ለቡድን ስራነት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ወይም ስራዎችን ለመገምገምና ለማዘጋጀት ነው:: ይህንንም ቢሆን አልፎ አልፎ ላያደርጉት እንደሚችሉ መ1 ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል::

### 4.1.1.4. መምህራኑ ቡድኖችንና የመማሪያ ክፍሎችን የሚያደራጁባቸው መንገዶች

#### ሀ. የቡድኖች አደረጃጀት

የቡድን አባላት ብዛት:

መምህራኑ ቡድኖችን በሚያደራጁበት ወቅት በአንድ ቡድን ውስጥ ምን ያህል ተማሪዎችን እንደሚያካትቱ ተጠይቀው "... በአብዛኛው የምጠቀመው ከአምስት እስከ ሰባት ... ነው..."

(መ1-17)። “… በቁጥር አራት አምስት …” (መ3-11) በማለት ሁለቱ መምህራን ሲገልፁ፣ መ2 ቡድኖች የሚያደራጁበትን ቁጥር ከነምክንያታቸው እንደሚከተለው አስረድተዋል።

> *በአንድ ክፍል ውስጥ ከ40 እስከ 50 ተማሪዎች ናቸው የምናገኛቸው ከ5 እስከ 6 ባይበልጥ ጥሩ ነው። ግን እስከ 8 ተማሪዎች ድረስ በቡድን ውስጥ እናደራጃለን። ተማሪው ባለው ሰዓት ለመጠቀም እንዲችል 8፣ 6 እንደዚህ ነው የማደራጃቸው። እና በጣም ሲያጥርም ጥሩ አይደለም፤ ሲበዛም ደግሞ ሀሳባቸውን ለማሰባሰብ ስለሚያስቸግራቸው ከ8 አይበልጥም።…* (መ2-12)

**ለክፍል ውስጥ የቡድን ስራ፣ የቡድን አባላት አመራረጥ**

በክፍል ውስጥ ለሚሰሩ የቡድን ስራዎች በአንድ ቡድን አባልነት የሚደራጁ ተማሪዎች የሚመረጡበትን መስፈርት በተመለከተ መ1 “… አንድ አካባቢ ቁጭ ያሉትን ተማሪዎች ለምሳሌ መጀመሪያ አካባቢ ላይ፣ እዚያው ባሉበት አካባቢ እንዲሰሩ አደርጋለሁ። ከዚያ ቀስ በቀስ ግን የመለዋወጥ ነገር እጠቀማለሁ…” (መ1-17) በማለት ሲገልፁ፣ መ2 በበኩላቸው “…ብዙ ጊዜ፣ ጊዜን ለመቆጠብ እንደተቀመጡበት አደርጋለሁ። ሌላ ጊዜ ደግሞ አልፋቤቲካል ከ1-6፣ ከ7-12 እያልኩ በተራ ቁጥር ራንደምሊ እንጂ ተመራርጠው አይደለም…” (መ2-13) በማለት ገልፀዋል። ከሁለቱ መምህራን በተለየ ሁኔታ መ3 ደግሞ “ቡድኖች የሚደራጁት አብዛኛውን ጊዜ በተማሪዎች ፈቃድ ነው። በቡድን ሆናችሁ ተነጋገሩ ይባላል …” (መ3-14) በማለት መልሰዋል።

**ከክፍል ውጭ ለሚሰሩ የቡድን ስራዎች የቡድን አባላት አመራረጥ**

ከክፍል ውጭ ለሚሰሩ የቡድን ስራዎች የቡድን አባላት የሚመረጡበትን መንገድ በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ፣ መ3 ክፍል ውስጥ ከሚደራጁበት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ (መ3-17) በመግለጽ ቡድኖቹን ተማሪዎች በፍላጎታቸው ተመራርጠው እንደሚመሰርቷቸው ጠቁመዋል። መ2 ግን፣ የተለያዩ የመመደቢያ ስልቶችን እንደሚጠቀሙ “… አንድም በአቀማመጥ፣ አንድም በአልፋቤት፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ አልፎ አልፎ ተመራርጠው የራሳቸውን ቡድን መስርተው እንዲሰሩ አደርጋለሁ…” (መ2-13) ሲሉ ገልፀዋል። መ1 እነዚህ የመ2 መምረጫ መስፈርቶች እንዳሉ ሆነው በተጨማሪ፣ አንዳንድ ጎበዝ ተማሪዎችን በየቡድኑ የሚበትኑበት ጊዜም እንዳለ (መ1-18) አስረድተዋል።

### የአንድ ቡድን አባላት አብሮ ቆይታ

የአንድ ቡድን አባላት አብረው የሚቆዩበትን ጊዜ አስመልክተው፣ መ1 "ብዙ ጊዜ ማድረግ አልወድም እኔ:: ቢበዛ አንዴ ወይም ሁለት ጊዜ ባደርግ ነው እንጂ፣ ከዚያ በላይ አብረው እንዲሆኑ አልፈቅድላቸውም ..." (መ1-22) በማለት ምላሽ ሲሰጡ መ3 በተመሳሳይ "... ቋሚ ቡድን የሚባል ነገር የለም፤ በየጊዜው ይቀያየራል..." (መ3-19) በማለት መልሰዋል:: እንደ መ2 ገለፃ ደግሞ:

> *አሳይመንቱን እስኪሰሩ ድረስ ብቻ ነው:: የተሰጣቸውን የቡድን ስራ ካስረከቡ በኋላ ቡድኑ ይፈርሳል:: በሚቀጥለው ደግሞ ሌላ ቡድን ይኖራል:: በቋሚነት የሚቆይ ቡድንም ሊኖር ይችላል::... አሁን በቋሚነት የሚቆይ ቡድን ሲባል፣ አንዳንድ በተከታታይ የሚሰሩ ስራዎች አሉ:: ለዚያ የተወሰነ ቡድን ይኖራል፤... ፕሮጀክቱ እስኪያልቅ፤ ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ያ ቡድን ይፈርሳል:: (መ2-14፣15)*

ከነዚህ መምህራኑ ስለ ንዑስ ቡድን አደረጃጀታቸው ከሰጧቸው ምላሾች በመነሳት፣ የንዑስ ቡድኖችን ከ4-8 ባለው የተማሪ ቁጥር እንደሚያደራጁ፣ ለክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰሩ የቡድን ስራዎች፣ የቡድን አባላትን በአብዛኛው በተመሳሳይ የመምረጫ መስፈርት (በመቀመጫ ቦታ መቀራረብ፣ በመታወቂያ ቁጥር ቅደም ተከተል፣ በፍላጎት) በመሳሰሉት እንደሚያደራጁ፣ እነዚህ በአንድ ቡድን ውስጥ የተደራጁ ተማሪዎችንም፣ በአብዛኛው ለአጭር ጊዜ ብቻ አብረው እንዲቆዩ እንደሚያደርጉ መገንዘብ ይችላል::

### ለ. የንዑስ ቡድን መማሪያ ክፍል አደረጃጀት

በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በቡድን የሚቀመጡበትን አቀማመጥ በተመለከተ፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚያደራጁት በክባዊ አቀማመጥ መሆኑን "... ያለው ወንበር ለየብቻ የሚቀመጡበት ስለሆነ፣ ክብ ሰርተው እንዲቀመጡ አደርጋለሁ:: ..." (መ3-15) በማለት ከነምክንያቱ ገልፀዋል:: መ1 በተመሳሳይ ሁኔታ "በአብዛኛው እኔ ... ከበው እንዲቀመጡ ነው የማደርገው..." (መ1-19) በማለት ገልፀዋል::

4.1.1.5. የንዑስ ቡድን መማር አላማንና የቡድን ስራን የመግለጽ ሁኔታ

**ሀ. ተማሪዎቹ ስለቡድን ስራ ዓላማ ግንዛቤ እንዲያገኙ የማድረግ ሁኔታ**

ይህንን በተመለከተ ለመምህራኑ በቅድሚያ የቀረበላቸው ጥያቄ፣ "ተማሪዎቹ በሙሉ ስለ ቡድን መማር ዓላማና አሰራር በቂ ግንዛቤ አላቸው ብለው ይገምታሉ?" የሚል ነበር:: ለዚህ ጥያቄ መ3 "የላቸውም ከማለት አላቸው ማለት፣ የሚቀል ይመስለኛል:: ..." (መ3-21) በማለት ምላሽ ሰጥተዋል:: መ1 እና መ2 ግን በተቃራኒው፣ ተማሪዎቹ ስለ ቡድን ስራ ያላቸው ግንዛቤ በጣም አነስተኛ እንደሆነ ገልፀዋል:: እንደሁለቱ መምህራን ገለፃ፣ በዚህ የተነሳም፣ ተማሪዎቹ በቡድን ለመስራት ፍላጎቱ የላቸውም ወይም እንደ መ2 ገለፃ "...ሬዚስት የማድረግ ነገር አለ..." (መ2-17):: በተጨማሪም ተማሪዎቹ የቡድን ስራ ዓላማንና ጠቀሜታን የተገነዘቡ ባለመሆናቸውም ለመምህሩም ሆነ ለማስተማር ዘዴው ያላቸው አመለካከት የተሳሳተ መሆኑንም መ1 በምሬት እንደሚከተለው ይገልፃሉ::

> *ያ ነው ትልቁ ችግር:: እኔ ብዙ ጊዜ በውስጤ የሚሰማኝ ነገር አለ:: እውነቱን ለመናገር የቡድን ስራ ሲባል፣ መምህራን እንዲያው በዚያ ነገር ላይ በቂ የሆነ ነገር ሳይኖረን ቀርቶ፣ እነሱን በዚያ መልክ ጊዜውን እንዲያሳልፉ... አድርገው የሚያስቡ ተማሪዎች አሉ:: ትምህርት በቀልድ እያለፈ እንደሆነ የሚያስቡም አሉ::...*(መ1-25)

ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ለተማሪዎቹ የቡድን መማር ዓለማንና በጋራ ተባብረው እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚያስተዋውቁባቸው መንገዶች ካሉ እንዲያስረዱ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል:: ለዚህም መ3 "ሁል ጊዜም ባይሆን እገልፃለሁ" (መ3-22) በማለት ሲመልሱ፣ መ1 በበኩላቸው "እኔ እንዲያውም መጀመሪያ ኮርስ በምገልፅበት ጊዜ ... መማር ልምድ መለዋወጥ ነው፤ እውቀት መለዋወጥ ነው፤... ብዬ እነግራቸዋለሁ ግን የመቀበሉ ነገር ..." (መ1-26) በማለት ለተማሪዎቹ ስለቡድን መማር ዓላማና ተባብረው እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚያስተዋውቁበትን ሁኔታ አስረድተዋል:: መ2 ደግሞ የራሳቸውን ተሞክሮ፣ "እነግራቸዋለሁ፤ ጠቃሚነቱን እነግራቸዋለሁ:: እንዲያውም በዚህ ሀሳብ ላይ ክርክር እንዲያደርጉ አድርጊያለሁ:: ተማሪ ተኮር ትምህርት ከአስተማሪ መራሽ ትምህርት ይሻላል? አይሻልም? እንዲከራከሩ ሁሉ አድርጊያለሁ ..." (መ2-18) በማለት ብዙ ጥረት ማድረጋቸውን አስረድተዋል:: እነዚህን ጥረቶቻቸውን የሚደግፍ፣ ማለትም ተማሪዎቹ በዘለቄታ በቡድን መማር ሂደት ማድረግ የሌለባቸውንና ያለባቸውን ተግባራትን ለይተው እንዲያውቁና በዚያ መሰረት እንዲሰሩ የሚያደርግ፣ በፅሁፍ የተዘጋጀ የቡድን ስራ መመሪያ አለ ወይ? በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄ

ሶስቱም መምህራን (መ1-27፣ መ2-20፣ መ3-23) በፅሁፍ የተዘጋጀ ምንም አይነት የቡድን መማር መተዳደሪያ ደንብ ወይም መመሪያ እንደሌለ አረጋግጠዋል::

ባጠቃላይ መምህራኑ የሰጧቸው ምላሾች እንደሚያሳዩት፣ ሁለቱ መምህራን ተማሪዎቻቸው ስለ ቡድን መማር አላማና አሰራር ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ እንደሆነና ይህም ለቡድን መማር ማስተማሩ ሂደት እንቅፋት እንደፈጠረ ይስማማሉ:: አንደኛው መምህር ግን እርግጠኛ ሳይሆኑ፣ ግንዛቤ ሳይኖራቸው አይቀርም የሚል ግምቱ ብቻ እንዳላቸው "የላቸው ከማለት አላቸው ማለት፣ የሚቀል ይመስለኛል..." (መ3-21) ሲሉ ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል:: ተማሪዎቹ ስለቡድን ዓላማና ተባብሮ ስለመስራት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ የተጠቀሙባቸው ስልቶችም፣ በትምህርቱ መጀመሪያ ወይም በየመሀሉ በምክር መልክ መንገር ነው:: ከመልሶቻቸው ማየት እንደሚቻለው ግን የሚነግሯቸው ስለ ቡድን መማር ጠቀሜታ እንጂ፣ በቡድን እንዴት መስራት እንደሚችሉ በማስተማር ላይ ያተኮረ አይደለም:: በተጨማሪም፣ ከቃል ባለፈ ምንም አይነት የቡድን ስራ ዓላማንም ሆነ አሰራርን የሚያስገነዝብ ፅሁፋዊ መመሪያ የላቸውም::

ለ. ለቡድን አባላት የየስራ ድርሻን የመግለፅ ሁኔታ

የቡድን ስራ ሲሰጥ በአንድ ቡድን ስር የሚገኙ ተማሪዎች የስራ ድርሻቸውን የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ፣መ3 "ያንን በራሳቸው ስምምነት ነው የሚያደርጉት ..." (መ3-20) በማለት እሳቸው የየስራ ድርሻን እንደማይገልፁ አስረድተዋል:: ከዚሁ የመ3 ምላሽ ጋር በመስማማት (መ2-16) "የየስራ ድርሻ አሁን እገሌ ይሄ ነው፤ ብዬ እኔ አላከፋፍልም:: ግን ሰዓት ተቆጣጣሪ እንዲኖር ያስፈልጋል:: እንደዚሁም ሰብሳቢ፣ ፀሀፊ፣ ፀጥታ አስከባሪ እንደዚህ የስራ ድርሻ እንዲኖራቸው ይጠበቃል:: ሁሉም የራሱን ድርሻ ይወጣል..." በማለት የየስራ ድርሻቸውን የመከፋፈሉ ጉዳይ፣ ለተማሪዎቹ ለራሳቸው የሚተው መሆኑን አስረድተዋል:: መ1 በበኩላቸው:

> *ይህንን ምንድነው የማደርገው፣ መጀመሪያ ኮርሱን ስንጀምር... አልፎ አልፎ የምንጠቀመው የቡድን ስራዎች አሉ የምንወያይባቸው:: ስለዚህ በዚያ ጊዜ ... የቡድን መሪ ይኖራል፤ የምትወያዩበትን ሀሳብ የሚፅፍ ሰው ይኖራል፤ የሚል ነገር እነግራችዋለሁ ... የቡድን ስራ በሚሰሩበት ጊዜ ሁሉም ሲናገሩ ሳይ፣... እዚህ ውስጥ ማነው የሚመራው? ብዬ ስል 'ማንም የለም፤ ዝም ብለን ነው የምንወያየው' የሚሉም አሉ:: የዚያኔ አይ አንድ የሚመራችሁ ሰው አሳይን አድርጉ:: ሌላ ደግሞ የምትወያዩበትን ሀሳብ ጠቅልሎ የሚይዝላችሁ ፀሀፊም ካለ፣ አሳይን አድርጉ:: በዚህ መሰረት ብታደርጉ ... ጥሩ ነው የሚል ነገር አስተያየት እሰጣቸዋለሁ:: በዚያ መሰረት ነው የሚያደርጉት:: (መ1-24)*

ሲሉ የግላቸውን አሰራር አብራርተዋል::

በቡድን ስራ ወቅት ተማሪዎች ስራን ተከፋፍለው መስራት እንዳለባቸው መምህራኑ እንደሚያምኑ መልሶቻቸው ያሳያል:: ይሁን እንጂ፣ በቡድን ስራ ወቅት ስራን መከፋፈል እንደሚያስፈልግ በኮርሱ መጀመሪያ ላይ ከመግለፅ ወይም ጫጫታ ሲፈጠር ስራን ተከፋፍላችሁ ስሩ በማለት አስተያየት ከመስጠት ባለፈ ለተማሪዎች የስራ ድርሻን የመስጠት እንዲሁም በየጊዜው የስራ ድርሻን የማለዋወጥ ተግባር የነሱ ተግባር አድርገው አይቆጥሩም፤ አያከናውኑም:: ይህ ሙሉ ለሙሉ የተተወው ለተማሪዎቹ መሆኑን ከመልሶቻቸው መረዳት ይቻላል::

#### 4.1.1.6. የመምህራኑ የቡድን ስራ ክትትል

##### ሀ. የክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትል

መምህራኑ በቡድን ስራ ወቅት ያላቸውን የክፍል ውስጥ ክትትል ለማወቅ፣ የቡድን ስራዎችን ከሰጡ በኋላ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኑዋቸውን ተግባራት በዝርዝር እንዲያስረዱ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል:: በዚህ መሰረት ሶስቱም መምህራን የሚያከናውኗቸውን ተግባራትን በዝርዝር ገልፀዋል:: (መ2-25) እና (መ3-27) የሰጧቸውን አብዛኞቹን ምላሾች የሚያካትተው የመ1 ምላሽ የሚከተለውን ይመስላል::

> … ተማሪዎች በሚሰሩበት ጊዜ ግራ የሚገባቸው ሀሳብ ካለ … እነዚህን ነገሮች ዞር ዞር እያልኩኝ እያየሁ መንገድ ማሳየት ነው::… አንዳንዴ ወደ ስህተት ከሄዱ … በዚህ ሳይሆን በዚህኛው እዩት እስቲ የሚል አስተያየት እሰጣቸዋለሁ::… መነሻ የሚሆን ነገር ራሱ የሚያጡበት ጊዜ አለ:: መነሻ ሲያጡ ይኼ ማለት እንደዚህ ማለት ነው… ብዬ መንገድ አሳያቸዋለሁ::… እረዳቸዋለሁ:: ከዚያ ውጭ ግን፣ የሰሩትን ሀሳብ… በአንድ ተወካይ አማካኝነት፣ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ፣ ክፍሉ ደግሞ በቀረበው ነገር ላይ … አስተያየት እንዲያቀርብ የራሴን አስተዋፅኦ አደርጋለሁ:: (መ1-30)

ከዚህ በተጨማሪ በሀሳብ ያልተግባቡ ተማሪዎችን፣ ያልተግባቡበትን ምክንያት በመጠየቅ የሚግባቡበት መስመርን እንደሚያሲዙና ያለ ተሳትፎ የተቀመጡ ተማሪዎች ሲያጋጥሟቸው፣ ለምን እንደማይስተፉ፣ የስራ ድርሻቸውስ ምን እንደሆነ ተማሪዎቹን እንደሚጠይቁ (መ2-25) አስረድተዋል::

በአጠቃላይ የሶስቱ መምህራን ምላሾች እንደሚያመለክቱት፣ የክፍል ውስጥ የቡድን ስራን በመከታተል ሂደት መምህራኑ የሚያከናውኗቸው ተግባራት የሚከተሉት ናቸው::

- እየተዘዋወሩ የቡድን ስራዎችን መመልከት
- ግልፅ ያልሆኑ ሀሳቦችን ማብራራት
- የተማሪዎቹ ውይይት ከርዕስ ጉዳዩ እንዳይወጣ ማድረግ
- በውይይቱ ተሳታፊ በመሆንና ሀሳብ በመስጠት ውይይቱን ማገዝ
- የሀሳብ አለመግባባቶችን ማስታረቅ
- የማይሳተፉ ተማሪዎች የማያስተፉበትን ምክንያትና የስራ ድርሻቸውን መጠየቅ
- የውይይት ውጤቶች እንዲደመጡና አስተያየት እንዲሰጥባቸው ማድረግ

## ለ. ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎች ክትትል

ይህን በተመለከተ፣ በቅድሚያ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ላይ ሁሉም ተማሪዎች እኩል ይሳተፋሉ ብለው ይገምቱ እንደሆነ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል:: መ1 "በዚያ ላይ ጥርጣሬ አለኝ..." (መ1-28) በማለት ሲመልሱ በተመሳሳይ መ2 "እርግጠኛ መሆን አልችልም..." (መ2-22) ብለው መልሰዋል:: መ3 በበኩላቸው "በዚህ ላይ ሁሉም እኩል ይሳተፋል የሚል ግምት የለኝም:: ... ከክፍል ውጭ በሚሰሩበት ጊዜ የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ አብዛኛውን ስራ ይሰራሉ:: ሌሎቹ ስማቸውን ብቻ ሰጥተው ምናልባት የማይገኙበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል::... ስለዚህ ሁሉም እኩል ይሳተፋሉ ለማለት አልችልም::" (መ3-24)

በማለት ጥርጣሬ ብቻ ሳይሆን ያለመሳተፍ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ጠቁመዋል:: በማስከተልም፣ ሁሉም ተማሪዎች በቡድን ስራው ላይ መሳተፍ አለመሳተፋቸውን የሚከታተሉበትን ዘዴ እንዲያስረዱ ጥያቄ ቀርቦላቸዋል:: መ1 እና መ2 እንዳስረዱት፣ የመከታተያ ስልታቸው የቡድን ስራው ከተጠናቀቀ በኋላ ከቡድኑ አባላት መካከል ድንገት አንዱ እንዲያቀርብ ወይም ስለ ስራው እንዲያስረዳ ማድረግ ነው:: "... ሁሉም ሀላፊነቱን ተወጥቶ መምጣቱን ለማረጋገጥ፣ የፈለግሁትን ተማሪ ከቡድኑ ውስጥ አቅርብ እላለሁ:: ዛሬ የሚያቀርበው እገሌ ነው ብዬ ነው የምነግራቸው እንጂ፣ ሲዘጋጁ ማን እንደሚያቀርብ አያውቁም::... ስለዚህ በፍርሃት ይዘጋጃሉ" (መ2-22-23):: መ3 ከሁለቱ መምህራን ትንሽ ለየት ባለ መንገድ እንደሚከታተሉ፣ "... በፅሁፍ መልክ የሚቀርብ ከሆነ የያንዳንዱ አስተዋጽኦ እዚያ ላይ ተጠይቆ እንዲገለፅ እጠይቃለሁ:: የኔ የሚለው የራሱን" (መ3-25) በማለት የቡድን ስራው ተጠናቆ በሚቀርብበት ሰዓት እያንዳንዱ የቡድን አባል በስራው ላይ ምን አስተዋጽኦ እንዳደረገ ተማሪው ራሱ ተጠይቆ፣ ተፅፎ እንዲሰጣቸው እንደሚያደርጉ አስረድተዋል::

"በቡድን ስራ ወቅት በቡድን አባላት መካከል አለመግባባቶች የሚፈጠሩባቸው ሁኔታዎች አሉ?" የሚል ጥያቄ ለመምህራኑ ቀርቦላቸው፣ ሶስቱም መምህራን (መ1-31፣ መ2-26፣ መ3-28) አለመግባባቶች እንደሚፈጠሩ በማመን፣ ዋና ዋና ያለመግባባት መንስዔዎች የማን ሀሳብ ይካተት የሚለው፣ ስራን ተከፋፍሎ ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆንና በገንዘብ መዋጮ ላይ አለመስማማት መሆናቸውን አስረድተዋል::

> *... አለመግባባቶች የሚፈጠሩት ከምን አንፃር ነው፣ 'እኔ ላይ ነው ጫና ያለው:: እነሱ ለመስራት ፈቃደኛ አይደሉም:: ... ስለዚህ መስራት አልቻልንም:: ...' አንዳንድ ተማሪዎች ደግሞ... በአንዱ ብቻ የማሰራት ነገር አለ::... የሚሰራው አካል ደግሞ ብር አዋጡ የሚልበት ጊዜ አለ:: ብሩ ደግሞ በዛ ካለ ... እማይስማሙበት ጊዜ አለ:: ... ለማቴሪያል መግዣ ያ ምናምን ተብሎ ነው:: ግን ለማሰሪያም ጭምር ነው:: 'እገሌ ነው የሚሰራው ብር' የሚባልበት ጊዜ አለ:: (መ1-31፣ 32)*

አለመግባባቶቹ መኖራቸውን የሚያውቁትም ተማሪዎቹ መጥተው ሲነግሯቸው ወይም ከሶስተኛ ወገን ከውጭ ሲሰሙ መሆኑን "... ይኼንን ከውጭ ነው የምሰማው ..." *(መ1-35)* በማለት ገልፀዋል::

በተጨማሪም በቡደን አባላት መካከል ግጭቶች መኖሩን ከተረዱ በኋላ፣ ግጭቶቹ እንዲፈቱ የሚወሰዱት እርምጃ ምክር መስጠት መሆኑን መ1 እና መ2 አስረድተዋል:: ለምሳሌ፣ መ1 ሁኔታውን ያስረዱት "ግጭቶቻቸውን እንዲፈቱ ... እንደዚህ አይነት ነገሮች አሉ:: ስለዚህ ከነዚህ ነገሮች እንደትጠነቀቁ፣ የምትሰሩትን ነገር ተስማምታችሁ እንድትሰሩ ... ብዬ ነው ምክር የምሰጣቸው" (መ1-35):: መ3 ግን፣ ግጭት ያጋጠማቸው አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን በመግለፅ፣ ያንን በሁለት ጎበዝ ተማሪዎች መካከል በሀሳብ አለመጣጣም ተፈጠረ ያሉትን ግጭት "ቡድኑ እንዲፈርድ አድርጌ፣ ሁለቱም በተለያዩ ቡድኖች እንደሆኑ አድርጊያለሁ" (መ3-29) በማለት ለግጭቱ መፍትሄ የሰጡበትን ሁኔታ አስረድተዋል::

"ተማሪዎች የቡድን ስራዎችን ለመስሪያ ወይም ስራዎቹን በክፍል ውስጥ ለማቅረቢያ የሚረዱ የዕህፈት መሳሪያዎችን የሚያገኙት ከየት ነው?" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ መ1 እና መ3 ሁልጊዜም ቢሆን ተማሪዎቹ በራሳቸው የሚያመቻቹት እንጂ እነሱ ፈፅሞ እንደማይሰጧቸው "ይህንን ከራሳቸው ነው፤ እኛ አናድልም" (መ2-24):: "የፅህፈት መሳሪያ እኔ አላቀርብም:: ማቅረብ እንዳለብኝም አላውቅም:: በራሳቸው ነው የሚሰሩት" (መ3-26) በማለት ምላሽ

ሰጥተዋል:: መ1 በበኩላቸው ከሁለቱ መምህራን ብዙም ባልተለየ መልኩ "ይኸንን እንኳን እንዲያው የለም ማለት ይቻላል በኔ በኩል:: ካላቸው ከራሳቸው እንዲጠቀሙ ነው የማደርገው ... ግን አልፎ አልፎ ምናልባት በጣም በጣም በጣም እንዲያው የለም በሚባል መልኩ ለመጠቀም የሚቻል ነገር አለ:: ግን እኔ ተጠቅመዋል ብዬ ለመናገር የሚያስችለኝ አይደለም" (መ1-29) በማለት አስረድተዋል::

ከነዚህ ከላይ ከቀረቡት የመምህራኑ ምላሾች መረዳት እንደሚቻለው፣ መምህራኑ ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎች ላይ ተማሪዎቹ ያላቸውን ተሳትፎ የሚከታተሉት፣ ስራዎቹ በሂደት ላይ ሳሉ ሳይሆን ተጠናቀው ከቀረቡ በኋላ ነው:: በስራው ሂደት ላይም የቡድን አባላት የስራ ድርሻን ተከፋፍሎ ሀላፊነት በመወጣት፣ የቡድን ስራውን መስሪያ የፅህፈት መሳሪያ በመግዛትም ሆነ በሌላ ምክንያት ግጭቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ቢገምቱም፣ ግጭቶች መከሰታቸውን ተማሪዎች መጥተው ሪፖርት ካላደረጉ ወይም ከሌላ ከሶስተኛ ወገን ካልሰሙ የሚከታተሉባቸው መንገዶች እንደሌሉ ነው:: በተጨማሪም፣ በማንኛውም የቡድን ስራ ስራውን ለመስራትም ይሁን ስራውን በክፍል ውስጥ ለማቅረብ የሚረዱ የፅህፈት መሳሪያዎችን ተከታትለው ለተማሪዎቹ እንደማያቀርቡ ከመልሶቻቸው ለመረዳት አያዳግትም::

4.1.1.7. የመምህራኑ የቡድን ስራዎች ግምገማና ውጤት አሰጣጥ

*ሀ. የቡድን ስራዎች አገማገም*

ለመምህራኑ ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች አንዱ የቡድን ስራ ግምገማቸውን ለማወቅ የቀረበ ነበር:: መ1 ጥያቄውን "... በጋራ የሰሩትን ነገር ምንድነው የማደርገው ... ርዕስ ጉዳዩን ተከፋፍለው እንዲያቀርቡ አደርጋለሁ:: በሚያቀርቡበት ጊዜ ባላቸው ባቀረቡትና በሌላም ነገር አይቼ ..." (መ1-36) በማለት መልሰዋል:: መ3 ደግሞ "... የራሳቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ በማድረግ ደግሞ በአጠቃላይ ስራውን በአንድነት በመመልከት ነው ..." (መ3-30) በማለት ምላሽ ሰጥተዋል:: መ2 ለጥያቄው ሰፋ ያለ ምላሽን እንደሚከተለው ሰጥተዋል::

> *የቡድን ስራዎችን የምገመግምበት አሰራር ... ተማሪዎቹ የቡድን ስራዎቹን በክፍል ውስጥ ሪፖርት ያደርጋሉ:: ሪፖርት ሲያደርጉ ሩብሪክ (Rubric) አዘጋጃለሁ:: ምን ምን ላይ ማተኮር እንዳብኝ፣ ተማሪው እንዴት ሰዓት ይጠብቃል፣ ድምፁ ለክፍሉ በሙሉ መሰማቱና ስሜት የመሳቡ ሁኔታ፣ ባጠቃላይ የማያቸው ነጥቦች አሉ:: ... መስፈርት እኔ ቀደም ብዬ አዘጋጃለሁ-የመገምገሚያ መስፈርት:: (መ2-27፣28)*

ለ. የቡድን ስራዎች ውጤት አሰጣጥ

ከዚሁ ከቡድን ስራ ግምገማ ጋር በተያያዘ ሌላው ለመምህራኑ የቀረበው ጥያቄ፣ ለቡድን ስራዎቹ ውጤት የሚሰጡበትና በቡድን ስራው ላይ የያንዳንዱን የቡድን አባል ተሳትፎ ለመለካት የሚጠቀሙበትን ስልት እንዲያስረዱ የሚጠይቅ ነበር:: መ2 ለውጤት መስጠቱ መሰረት የሚያደርጉት፣ በግምገማ ወቅት የተጠቀሙበትን መስፈርት እንደሆነ "በዚያ መስፈርት ያሟላ ያላሟላ ኤክስና ራይት እያደረግሁ አልፍና የቡድን ስራቸውን ደግሞ እቀበላለሁ:: ከዚህ በኋላ እዚያ ላይ የፃፉትን ሀሳብ አነባለሁ:: ... ወረቀቱንም አነባለሁ፤ ክፍል ውስጥ እንዴት እንዳቀረቡም ማስታወሻ ይዛለሁ:: ሁለቱንም አንድ አድርጌ ውጤት እሰጣቸዋለሁ" (መ2-28) በማለት አብራርተዋል:: በማስከተል ለኚሁ መምህር በአንድ የቡድን ስራ፣ የቡድኑ አባላት የሚያገኙት ውጤት ይለያያል ወይስ አንድ አይነት ነው የሚል ጥያቄም ቀርቦላቸው "አንድ አይነት ነው" (መ2-29) በማለት መልሰዋል:: በሌላ በኩል መ3 የቡድን ስራዎችን ቢያሰሩም ለአብዛኛዎቹ የቡድን ስራዎች ውጤት እንደማይዙ ቢይዙም አነስተኛ ውጤትን እንደሚይዙ በመግለፅ፣ የሚሰጠው ውጤት ግን "... ለአባላቱ ሁሉ በተመሳሳይ የሚሰጥበት ሁኔታም አለ:: ደግሞም የያንዳንዱ የግል ስራ የሚታይበት መንገድ አለ" (መ3-31) በማለት አስረድተዋል:: ከሁለቱ መምህራን በተለየ ሁኔታ መ1 የቡድን ስራዎችን ቢሰጡም ለስራዎቹ በጭራሽ ውጤት እንደማያስጡ ገልፀዋል:: ቀደም ሲል የቡድን ስራዎችን እየገመገሙ፣ በአንድ የቡድን ስራ ለቡድኑ አባላት በሙሉ ተመሳሳይ ውጤትን ይሰጡ እንደነበረ በማስታወስ፣ አሁን ግን ውጤት መስጠት ያቆሙበትን ምክንያት እንደሚከተለው በሰፊው አስረድተዋል::

> *... ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባለው የአሰራር ለውጥ ለቡድን ስራዎች እኔ በበኩሌ ውጤት መስጠት አቁሚያለሁ:: ... የተወሰኑ ሰዎች ከኮሌጃችን ሄደው ወርክሾፕ ወስደው የተመለሱበት ጉዳይ አለ::... ተማሪዎችን በቡድን ስንገመግማቸው የቡድን ውጤት መስጠቱ ጥሩ እንዳይደለ (መጥተው እንዳስረዱን ማለት ነው) የሰዎችን የየግል ችሎታ የማይመዝን እንደሆነ፣ ውጤት መስጠትም ካለብን መስጠት ያለብን ደረጃዎችን አውጥተን ለምሳሌ እጅግ በጣም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ፣ ጥሩ እያልን ... በዚያ መሰረት ብንከታተላቸው የቡድን ስራዎችን:: ... አንዳንድ ጊዜ ጥሩ በግል የሚሰሩ ተማሪዎች ውጤታቸው ላይ ዝቅተኛ ሊያመጡ ይችላሉ:: ሶ በዚያ ጊዜ ይኼ እጅግ በጣም ጥሩ፣ በጣም ጥሩ እየተባለ የተሰጠውን ነገር ... ልናይላቸው እንደምንችል... (መ1 -35፣37)*

ተማሪዎች የቡድን ስራዎቻቸውን ከሌሎች ቡድኖች ጋር በመለዋወጥ የበጤ እርማት ያካሂዱ እንደሆነ ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ፣ መ1 እና መ2 የቡድን ስራዎቹ በክፍል ሲቀርቡ የሌሎቹ ቡድን ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ ከመጋበዝ ባለፈ፣ የቡድን ስራዎቻቸውን ተቀያይረው

እንዲተራረሙ እንደማያደርጉ ገልፁዋል:: መ3 ግን ከሁለቱ መምህራን በተለየ ሁኔታ “እስ፤ ይህንን ዘዴ በጣም እጠቀማለሁ:: ተማሪዎች በጣም ወደውት ይህንን ስራ ለመስራት ፈቃደኛ ስለሆኑ፣ ያንዱ ስራ ላይ አስተያየት በሚሰጡበት ጊዜ፣ በጣም ደስተኛ ሆነው ለማረም፣ ሀሳባቸውን ለመስጠት ይችኩላሉ” (መ3-32) በማለት ተግባራዊነቱን አስረድተዋል:: በተያያዘ ተማሪዎቹ በቡድን መማር ሂደቱ የሚያደርጉትን የየራሳቸውን ለውጥ በየጊዜው የሚገመግሙበት ሁኔታ እንዳለ ለማወቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ ሶስቱም መምህራን (መ1-40፣ መ2-31፣ መ3-33) እንዲህ እንደማያደርጉ ገልፀዋል::

በአጠቃላይ ከላይ መምህራኑ የቡድን ስራዎችን የሚገመግሙባቸውና ውጤት የሚሰጡባቸው አሰራሮችን በተመለከተ ካቀረቧቸው ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው፣ አብዛኞቹ መምህራን የቡድን ስራን የሚገመግሙት የመገምገሚያ መስፈርትን መሰረት አድርገው አይደለም:: ዋና የመገምገሚያ መንገዳቸውም፣ የቡድን ስራዎቹን በክፍል ውስጥ የማቅረብ ሁኔታን መመልከት ነው:: አብዛኞቹ ከሶስቱ ሁለቱ ለቡድን ስራዎች ፈፅሞ ውጤት እንደማይሰጡ፣ ቢሰጡም አነስተኛ ውጤት እንደሚሰጡ ለመረዳት ተችሏል:: ለአንድ የቡድን ስራ የሚሰጠው ውጤትም፣ በአብዛኛው ለቡድኑ አባላት በሙሉ ተመሳሳይ የሆነ ቡድናዊ ውጤት እንደሆነ ከምላሾቻቸው መረዳት ይቻላል:: ከዚያ በተጨማሪ፣ በአብዛኛው ተማሪዎቹ በቡድን ስራ ላይ የቢጤ ግምገማ እንዲያካሂዱ እንደማያደርጉ፣ ተማሪዎች የግላቸውን የቡድን ስራ ተሳትፎ በየጊዜው እንዲገመግሙ ደግሞ ፈፅሞ እንደማያደርጉ ለመረዳት ይቻላል::

### 4.1.1.8. የንዑስ ቡድን ማስተማር ዕብረቃን የማካሄድ ሁኔታ

መምህራኑ የንዑስ ቡድን ማስተማር አተገባበራቸው ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ወይም ጥንካሬና ድክመቱን የሚገመግሙበት መንገድ ካለቸው እንዲያስረዱ ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ ሁለቱ መምህራን (መ1-44፣ መ3-35) የተማሪዎቹን እንቅስቃሴ በማየት የሚል ምላሽን ሰጥተዋል:: ለምሳሌ:- መ1 መላሻቸውን የሰጡት “እራሴን የማይበት፣ ተማሪዎቹ በሚያቀርቡት አቀራረብ ላይ፣ የምደሰትባቸው ጊዜያት አሉ:: ... ስለዚህ በዚያ ጊዜ የሚሰማኝ ስሜት፣ በቃ ደስ የሚል ነው:: እንኳንም ይህንን ስራ በቡድን አሰራሁ የምልበት ጊዜ አለ ...” (መ1-44) በማለት ነበር::

መ2 በበኩላቸው "የጎላ ችግር ነው ብዬ የማቀርበው ነገር የለም:: ያው እኔ ሳቀርብ ጥያቄውን ሳዘጋጅ ጥሩ አቀራረብ ሳይኖረኝ ሲቀር ውጤታማ የሆነ የቡድን ስራ ላይኖር ይችላል:: ... ጥሩ ዝግጅት ጥሩ ፕሮፖዛል አቅርቤ ተማሪዎች ሰርተው ሲያመጡ ምንም ችግር አላጋጠመኝም" (መ2-31) በማለት መልሰዋል::

በሌላ በኩል ተማሪዎቹ የቡድን መማር ሂደታቸውን እንዲገመግሙ ማድረግን በተመለከተ መ1 እና መ3 ያነሱት ነገር ባይኖርም፣ መ2 ግን:

> *አሁን ይኼንን ያሳያቸዋል ብዬ የማስበው፣ ምንድነው እኔ የሰሩትን ስራ አሰባስባለሁ:: ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ:: አርሜ እራሳቸውን ደግሞ መልሰው እነሱ እንዲያዩ ወረቀቱን መጨረሻ ላይ እመልስና ... የመጀመሪያው ምን ይመስላል? ሁለተኛውና ሶስተኛውስ? ... መጀመሪያ ከነበራችሁበት ኮርሱን ስንጨርስ ያላችሁበት ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚለውን ክፍል ውስጥ እንወያያለን:: (መ2-31)*

በማለት ተማሪዎች በቡድን ስራ ያመጡትን ለውጥ እንዲገመግሙ እንዳሚያደርጉ አስረድተዋል::

ከመምህራኑ ምላሾች መገንዘብ እንደሚቻው፣ የቡድን ማስተማር ሂታቸውን የሚገመግሙት የቡድን ስራዎች ሲቀርቡ ተማሪዎች በሚያሳዩት አቀራረብ ሁኔታ ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ ግን መደበኛ የሆነ፣ በቡድን ስራ ወቅት ተማሪዎቹ ያሉባቸውን ችግሮችም ሆነ አጠቃላይ የቡድን መማር ማስተማር ሂደቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ሊያሳያቸው የሚችል የማስተማር ዕብረቃን እንደማያካሂዱ፣ የሚሰጧቸው በርካታ በግምት ላይ የተመሰረቱ መልሶቻቸው ያስረዳሉ:: የሚከተለው የመ1 ተማሪዎቹ ለቡድን ስራ ተነሳሽነት የሚያጡበትን ሁኔታ አስመልክተው የሰጡት ሀሳብ ጥሩ ማስረጃ ነው::

> *... የቡድን ስራን እንደምንም ሳይቆጥሩ ወይም የረባ ነገር አይመጣም ብለው ያስቡ? ወይም መጨረሻ ላይ የሚነሳ ነገር አለ እንደርሳለን ብለው ይጠብቁ? ብቻ ከሆነ ነገር አንፃር የተማሪዎቹ የመስራት ተነሳሽነት የሚቀንስበት ጊዜ አለ:: ከዚህ አንፃር እኔ አብዛኛውን ጊዜ የቡድን ስራን ለመጠቀም ያለኝ ፍላጎት አናሳ ነው በበኩሌ:: (መ1-42)*

መምህራኑ፣ ተማሪዎቹ ከያንዳንዱ የቡድን ስራ በኋላ የቡድን መማር ሂደታቸውን እንዲገመግሙ የሚያደርጉበት አሰራርም የላቸውም::

#### 4.1.2. ከክፍል ምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የመምህራኑ የክፍል ውስጥ የቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበርን ለማወቅ አምስት ምልከታዎች ተካሂደዋል:: ከነዚህ ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎችም እንደሚከተለው ተተንትነዋል::

##### 4.1.2.1. የቡድኖችና የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት

ሰንጠረዥ ሁለት: ስለ ቡድኖችና ክፍሎች አደረጃጀት ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ምልከታዎች | መምህር | የአባላት ብዛት | የአባላት አመራረጥ | የቡድን አቀማመጥ | የመዘዋወሪያ ክፍተት መኖር | አቀማመጣቸውን የመከታተል ሁኔታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ም1 | መ1 | ከ6-7 | በአቀማመጥ መቀራረብ | ክባዊ | – | – |
| 2 | ም2 | መ1 | 6 | ቁጥር በመጥራት | ክባዊ | – | – |
| 3 | ም3 | መ2 | ከ5-7 | በአቀማመጥ መቀራረብ | ክባዊ | – | – |
| 4 | ም4 | መ1 | ከ5-6 | በአቀማመጥ መቀራረብ | ክባዊ | – | – |
| 5 | ም5 | መ2 | ከ5-7 | በአቀማመጥ መቀራረብ | ክባዊ | + | – |


መፍቻ:- + በምልከታው ወቅት ነበር (ታይቷል)

- በምልከታው ወቅት አልነበረም (አልታየም)

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው መምህራኑ ቡድኖችን ሲያደራጅ በአንድ ቡድን ውስጥ እንዲካተቱ ያደረጓቸው ተማሪዎች ብዛት ከ5-7 ባለው ውስጥ ነበር:: ቡድኖቹ የተመሰረቱትም በአብዛኛው የተማሪዎቹን የአቀማመጥ መቀራረብ መሰረት በማድረግ ሲሆን አቀማመጣቸውም ክብ ቅርፅን በመስራት ነበር:: የሚከተሉት በምልከታ ወቅት የተነሱ ፎቶ ግራፎች ሁኔታውን በይበልጥ ያስረዳሉ::



ሀ



ለ

ከላይ በክብ ሆነው በተቀመጡት በአንዳንድ ቡድኖች መካከል እንደልብ ለመዘዋወር የሚያስችል ክፍተት እንደሌለ በምልከታዎቹ ወቅት ለማየት ተችሏል:: ለምሳሌ ከዚህ በታች በፎቶግራፉ ላይ የሚታዩት ቡድኖች በጣም ተዘራርበው በመቀመጣቸው መምህሩ እንደልብ እየተዘዋወሩ ከነሱ በኋላ ያሉትን ቡድኖች ለመመልከት የማያስችሉ ናቸው::



ሐ

በምልከታው ወቅት እንደታየውና ከላይ የቀረቡት ፎቶ ግራፎችም እንደሚያሳዩት ቡድኖቹ የተደራጁት አነስተኛ ቁጥር ባለቸው ተማሪዎች ነው:: አቀማመጣቸውም ሁሉም አባላት ፊት ለፊት መተያየት የሚችሉባቸውና በቀላሉ መደማመጥ የሚችሉባቸው ሆነው ታይተዋል:: ነገር ግን፣ አብዛኞቹ ቡድኖች የተመሰረቱት በአቀማመጥ መቀራረብ በመሆኑ ከላይ በፎቶ "ሀ" እና "ለ" ሴቶቹ በአንድነት ወንዶቹ ደግሞ በአንድነት ሆነው እንደሚታዩት ያለ ተመሳሳይነትን የሚፈጥር መሆኑን ለማስተዋል ተችሏል:: በአራቱ ምልከታዎች ወቅት እንደታየው አንዳንድ ቡድኖች በጣም ተጠጋግተው ስለተቀመጡ፣ በመሀላቸው እንደልብ ተዘዋውሮ እነሱንም ሆነ ከነሱ በኋላ ያሉ ቡድኖችን ለመከታተል የሚቻልባቸው ሁኔታዎች አልነበሩም:: በመምህራኑ በኩል፣ የተማሪዎቹን የቡድን አቀማመጥ አመቺ መሆን አለመሆን የመከታተልና የማስተካከል ሁኔታ ግን ፈፅሞ አልታየም::

4.1.2.2. የቡድን ስራን ግልፅ የማድረግ ሁኔታ

ሰንጠረዥ ሶስት: የቡድን ስራዎቹን ግልፅ ማድረግን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ምልከታዎች | መምህር | የቡድን ስራን ማስተዋወቅ | ትዕዛዞችን መግለፅ | የስራውን ማጠናቀቂያ ጊዜ በቅድሚያ መግለፅ | ለአባላቱ የየስራ ድርሻን መስጠት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ም1 | መ1 | + | + | + | _ |
| 2 | ም2 | መ1 | + | + | _ | _ |
| 3 | ም3 | መ2 | + | + | + | _ |
| 4 | ም4 | መ1 | + | + | _ | _ |
| 5 | ም5 | መ2 | + | + | _ | _ |

ከሰንጠረዡ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ መምህራኑ የቡድን ስራዎቹን በቅድሚያ ከማስተዋወቅ በተጨማሪ ትዕዛዞቹን ይገልፃሉ:: በአምስቱም ምልከታዎች ትዕዛዞቹ በቃልም በፅሁፍ ተሰጥተዋል:: ስራው የሚፈጀውን ጊዜ በቅድሚያ የመግለፅ ሁኔታ ግን በአብዛኛው አይስተዋልም:: ለምሳሌ በምልከታ 2፣4 እና 5 እንደታየው መምህራኑ ደቂቃውን የገለፁት ተማሪዎቹ ስራውን ጀምረው በሂደት ላይ እያሉ ሳለ ነበር:: ለያንዳንዱ የቡድን አባላት የየስራ ድርሻውን ወይም ሚናውን ለይቶ መስጠት ደግሞ በሁሉም ምልከታዎች አልታየም::

4.1.2.3. የክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትል

ሰንጠረዥ አራት:- ስለ ክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትል ከምልከታ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ምልከታዎች | መምህር | በክፍሉ ውስጥ መዘዋወር | ከቡድኖቹ ጋር መስተጋብር መፍጠር | የያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ መከታተል | የስራ ውጤት እንዲያቀርቡ ማድረግ | ተማሪዎቹን ማበረታታት | ማጠቃለያ መስጠት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ም1 | መ1 | + | + | _ | + | + | + |
| 2 | ም2 | መ1 | + | + | _ | _ | _ | _ |
| 3 | ም3 | መ2 | + | + | _ | + | + | + |
| 4 | ም4 | መ1 | + | + | _ | + | _ | + |
| 5 | ም5 | መ2 | + | + | _ | _ | _ | _ |

ሰንጠረዥ 4 እንደሚያሳየው መምህራኑ የቡድን ስራዎችን ከሰጡ በኋላ በክፍሉ ውስጥ በየቡድኖቹ መሀል ይዘዋወራሉ:: በዚህም ወቅት ከየቡድኖቹ ጋር መስተጋብር በመፍጠር የተማሪዎቹን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፣ በውይይቱም እየተሳተፉ ተማሪዎቹን ይረዳሉ::



መ መምህሯ የቡድን ስራዎችን ሲከታተሉ

የመምህራኑ ክትትል በአብዛኛው ያተኩር የነበረው ግን የቡድኖቹን አጠቃላይ ተሳትፎ በመከታተል ላይ ነበር እንጂ፣ በየቡድኖቹ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን በሙሉ እኩል መሳተፍ አለመሳተፋቸውን በመከታተል ላይ ያተኮረ አልነበረም:: በውይይቱ ወቅቶች አንዳንድ ተማሪዎች የጎላ ተሳትፎ ሲያደርጉ አንዳንዶቹ ግን በአብዛኛው አድማጭ ብቻ ሆነው የታዩባቸው ሁኔታዎች ታይተዋል:: የቡድን ስራዎቹ ከተጠናቀቁ በኋላ፣ በየቡድኖቹ ተወካዮች አማካይነት የስራ ውጤቶቹ እንዲቀርቡ ተደርገዋል:: ከየቡድኖቹ የተመረጡ ተወካዮች የስራዎቻቸውን ውጤቶች፣ ወደፊት ለፊት /ወደ ጥቁር ሰሌዳው/ በመውጣት ወይም ከታች በፎቶግራፉ እንደሚታየው በቡድን በተቀመጡበት ቦታ ሆነው ሲያቀርቡ ለመመልከት ተችሏል::



ሠ

አብዛኛውን ጊዜ ሁሉም ቡድኖች ውጤቶቻቸውን የማቅረብ ዕድሉን ሲያገኙ፣ አንዳንዴ ግን የተወሰኑ ቡድኖች ሳያቀርቡ እንዲሁም መምህሩ ማጠቃለያ ሳይሰጡ የክፍለ ጊዜው ሰዓት የሚያበቃበት ሁኔታ ታይቷል:: በውይይቱ ሆነ፣ የስራ ውጤቶቹ በሚቀርቡበት ወቅት ተማሪዎቹን የማበረታታት ሁኔታ ግን አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል::

### 4.1.3. ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት በተማሪዎቹ የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ በደጋፊ የመረጃ ምንጭነት ማገልገሉ በክፍል ሦስት ተገልጿል:: ከዚህ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችም እንደሚከተለው ተተንትነዋው ቀርበዋል::

#### 4.1.3.1. የቡድኖችና የክፍሎች አደረጃጀትን በተመለከተ ከመጠይቆቹ የተገኘ መረጃ

**ሀ. የቡድን  አደረጃጀት**

**የአባላት ብዛት:-** በቡድን ምስረታ ወቅት በአንድ ቡድን ውስጥ ከስንት እስከ ስንት ተማሪዎች በአባልነት እንደሚታቀፉ፣ በመጠይቁ ክፍል ሶስት ጥያቄ አራት ለቀረበው ጥያቄ፣ መጠይቁን በትክክል ሞልተው ከመለሱት 58 ተማሪዎች መካከል 54ቱ የተለያዩ ቁጥሮችን በመጥቀስ ምላሻቸውን ሰጥተዋል:: ምላሻቸውን ከሰጡት ውስጥ 49ኙ (90.7%)ቱ ያመለከቷቸው ቁጥሮች ሲጠቃለሉ የአባላቱ ቁጥር ከ4-8 መሀል እንደሆነ አሳይተዋል:: ቀሪዎቹ 5 ተማሪዎች (9.3%)ቱ ግን ከ4 በታች እስከ 3 ድረስ ሊሆን እንደሚችል አመልክተዋል::

**የቡድን አባላት አመራረጥ:-** በተለይ ከክፍል ውጭ ለሚሰሩ የቡድን ስራዎች፣ በአንድ ቡድን አባልነት የሚመደቡ ተማሪዎች የሚመረጡበትን መስፈርት እንዲገልፁ በመጠይቁ ክፍል አራት ጥያቄ ሁለት ተጠይቀዋል:: ለጥያቄዎቹም ከ58ቱ ተማሪዎች 57ቱ ምላሽ ሰጥተዋል:: እንደ ተማሪዎቹ ገልፃ ከሆነ በአንድ ቡድን ውስጥ የሚካተቱ ተማሪዎች የሚመረጡባቸው መስፈርቶች **የመታወቂያ ቁጥር ቅደም ተከተል፣ የአቀማመጥ መቀራረብ፣ በፍላጎት እርስ በርስ መመራረጥ፣ ዕጣ (በተለይ ቁጥር መጥራት)፣ ከጎበዝ ተማሪዎች ጋር በማቀናጀት** እና **ወንድና ሴትን በማቀናጀት**  ናቸው:: ከነዚህ ውስጥ በ49 ተማሪዎች (85.9%) በከፍተኛ ድግግሞሽ የተነሳው በመታወቂያ ቁጥር ቅደም ተከተል የሚለው ሲሆን በሁለተኛነት በ22 ተማሪዎች (38.6%) በድግግሞሽ የተነሳው ደግሞ፣ በአቀማመጥ መቀራረብ የሚለው ነው:: ከነዚህ ሌላ 19

ተማሪዎች (33.5%) በዕጣ እንዲሁም 13 ተማሪዎች (22.8%) በፍላጎት በመመራረጥ የሚሉትን የቡድን አባላት መምረጫ መስፈርቶች በድግግሞሽ አንስተዋል::

ይሁን እንጂ፣ ተማሪዎቹ በመጠይቁ ክፍል ሶስት ጥያቄ አምስት፣ በመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ የቡድን መማር ሂደት ጠንካራና ደካማ የሚሏቸውን ነጥቦች እንዲዘረዝሩ ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ አንዳንድ ተማሪዎች ከላይ የተጠቀሱትን የቡድን አባላት የመምረጫ መንገዶች፣ ምክንያቶችን ጭምር እየሰጡ በደካማነት ፈርጀዋቸዋል:: ለምሳሌ፣ ተ35 "በመዝገብ ቁጥር ሲደረድሩ ሁሉም ሰነፍ ከሆነ ሀሳብ ለሀሳብ አለመለዋወጥ ስለሚያስከትል..." በማለት የመምህራኑ የቡድን ማደራጃ ዋነኛ ስልት የሆነውን በመታወቂያ ቁጥር ቅደም ተከተል የማደራጀት ስልት ችግር ገልፃለች:: በአቀማመጥ መቀራረብ ማደራጀታቸውም ቢሆን ችግር እንደሚነፀባረቅበት ተ8 "አንዳንድ ጊዜ ጎበዝ ተማሪ በአንድ ላይ ከተቀመጡ ደካማው ቡደን ጥሩ የመረዳት ሁኔታ አይኖርም:: ምክንያቱም ሁሉም ደካማ ከሆነ idea share አያደርጉም::" በማለት ትገልፃለች:: ተ4 በበኩሏ " በቡድን በምንሆንበት ጊዜ ተማሪዎች ጎበዝን በመምረጥ አንድ ላይ ይሆናሉ:: በትምህርት ደካማ የሆኑ ተማሪዎች ሲጎዱ ይችላሉ::" በማለት በመመራረጥ የሚደረግ የቡድን ምስረታ ያለውን ችግር ታስረዳለች::

### የቡድን አባላት አብሮ ቆይታ

በአንድ ቡድን ውስጥ የታቀፉ ተማሪዎች ለምን ያህል ጊዜ አንድ ላይ እንደሚቆዩ እንዲገልፁ፣ በመጠይቁ ክፍል ሶስት ጥያቄ ሶስት ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ ከ58ቱ ተማሪዎች 57ቱ ምላሾቸውን ሰጥተዋል:: ከነዚህ ምላሻቸውን ከሰጡ 57 ተማሪዎች መካከል 27ቱ (47.4%) አንድ የተሰጠንን የቡድን ስራ ሰርተን እስክናጠናቅቅ ብቻ፣ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል:: 15 ተማሪዎች (26.3%) ደግሞ እንደ ሁኔታው ከአንድ የቡድን ስራ በላይም አብረው ሊቆዩ እንደሚችሉ ገልፀዋል:: 8 ተማሪዎች (14%) ለተከታታይ ሁለትና ሶስት የቡድን ስራዎች አብረው እንደሚቆዩ ሲገልፁ 5 ተማሪዎች (8.8%) ብቻ ለአንድ ሙሉ ሴሚስተር አብረው እንደሚቆዩ አስረድተዋል:: ቀሪዎቹ 2 ተማሪዎች (3.5%) ግን አይታወቅም በማለት መልሰዋል::

በአጠቃላይ የቡድን አደረጃጀቱን በተመለከተ ተማሪዎቹ የሰጧቸው ምላሾች እንደሚያመለክቱት፣ በአንድ ቡድን ውስጥ የሚካተቱ ተማሪዎች ቁጥር ቢያንስ 4 ቢበዛ ደግሞ 8 እንደሆነ ነው:: በአንድ ቡድን የሚካተቱ አባላትን መምረጫ ዋና ዋና መስፈርቶች ደግሞ

የመታወቂያ ቁጥር ቅደም ተከተል፣ የአቀማመጥ መቀራረብ፣ እጣና በፍላጎት መመራረጥ ሲሆኑ በነዚህ አመራረጦች አንዳንድ ተማሪዎች ደስተኛ አለመሆናቸው ታውቋል:: እንደተማሪዎቹ መረጃ፣ የሚመሰረቱት ቡድኖችም በዘላቂነት አባላቱ አብረው የሚቆዩባቸው ሳይሆኑ በአብዛኛው ለተወሰነ ወቅት ብቻ የሚቆዩባቸው ናቸው::

## ለ. የመማሪያ ክፍሎች አደረጃጀት

ሰንጠረዥ አምስት: የቡድን አቀማመጥን በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | | አብዛኛውን ጊዜ 4 | | አንዳንድ ጊዜ 3 | | አልፎ አልፎ 2 | | በጭራሽ 1 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | በክፍል ውስጥ በቡድን በምንቀመጥበት ወቅት፣ የቡድኑ አባላት በሙሉ ፊት ለፊት መተያየት እንችላለን:: | 33 | 56.9 | 19 | 32.8 | 5 | 8.6 | 1 | 1.7 | - | - |
| 4 | በቡድን ስራ ወቅት፣ የቡድን አባላት ተቀራርበን ስለማንቀመጥ ለመደማመጥ እንቸገራለን:: | 3 | 5.2 | 3 | 5.2 | 14 | 24.1 | 16 | 27.6 | 22 | 37.9 |
| 10 | በክፍል ውስጥ በቡድን በቡድን ሆነው በሚቀመጡ ተማሪዎች መካከል፣ እንደልብ መዘዋወር የሚያስችል ክፍተት አለ:: | 15 | 25.9 | 20 | 34.5 | 11 | 18.9 | 6 | 10.3 | 5 | 8.6 |

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድን የሚቀመጡባቸው አቀማመጦች በአብዛኛው የቡድን አባላቱን ፊት ለፊት መተያየት የሚያስችሉ መሆናቸውን፣ ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ለ1ኛው ጥያቄ (56.9%)ቱ ሁልጊዜ እና (32.8%)ቱ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በማለት በድምሩ (89.7%)ቱ የሰጡት ምላሽ ያስረዳል:: በሰንጠረዥ ለ4ኛው ጥያቄ (37.9%)ቱ

በጭራሽ እና (27.6%)ቱ አልፎ አልፎ በድምሩ (65.5%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ በአቀማመጥ መራራቅ የተነሳ ለመደማመጥ እንደማይቸገሩ አሳይተዋል:: በቡድን በቡድን ሆነው በተቀመጡ ተማሪዎች መካከል እንደልብ መዘዋወር የሚያስችል ክፍተት ይኖር እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ በሰንጠረዡ እንደሚታየው (25.9%)ቱ ሁልጊዜ እና (34.5%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ በማለት በድምሩ (60.4%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ መኖሩን አመልክተዋል::

እነዚህ የተማሪዎች ምላሾች እንደሚያሳዩት፣ የመምህራኑ የክፍል አደረጃጀቶች በአብዛኛው የቡድን አባላትን ፊት ለፊት መተያየት የሚያስችሉ ሆነው ተገኝተዋል:: ይሁን እንጂ፣ ፊት ለፊት የመተያየት ሁኔታን የመፍጠራቸውን ያህል በጎላ መልኩ መቀራረብንና ያለ ችግር መደማመጥን የሚፈጥሩ ሆነው አልተገኙም:: በቡድኖቹ መካከል መዘዋወር የሚያስችል ክፍተት የመኖሩ ሁኔታም፣ በአብዛኛው የሚታይ ሆኖ አልተገኘም::

### 4.1.3.2. የቡድን ስራ አላማና የቡድን ስራ ገለፃ

ሰንጠረዥ ስድስት: የቡድን ስራ አላማና የቡድን ስራ ገለፃን በተመለከተ፣ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | | አብዛኛውን ጊዜ 4 | | አንዳንድ ጊዜ 3 | | አልፎ አልፎ 2 | | በጭራሽ 1 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 2 | መምህሩ/ሯ/ በቡድን ተባብሮ መስራት እንዴት እንደሚቻል ትምህርት ይሰጡናል:: | 5 | 8.6 | 9 | 15.5 | 14 | 24.1 | 22 | 37.9 | 8 | 13.8 |
| 5 | መምህሩ/ሯ/ የቡድን ስራ ሲሰጡ ስለ አሰራሩ ማብራሪያ ይሰጣሉ:: | 20 | 34.5 | 22 | 37.5 | 11 | 18.9 | 4 | 6.9 | 1 | 1.7 |
| 7 | በክፍል ውስጥ የሚሰራ የቡድን ስራ ሲሰጥ፣ በምን ያህል ደቂቃ መስራት እንዳለብን በቅድሚያ ይገልፅልናል:: | 11 | 18.9 | 20 | 34.5 | 18 | 31.0 | 8 | 13.8 | 1 | 1.7 |
| 11 | መምህሩ/ሯ/ የቡድን ስራ ሲሰጡ፣ ለያንዳንዱ የቡድን አባል የየስራ ድርሻውን ያከፋፍላሉ:: | 4 | 6.9 | 3 | 5.2 | 13 | 22.4 | 12 | 20.4 | 26 | 44.8 |

በሰንጠረዥ ስድስት ለጥያቄ 2 ተማሪዎቹ በሰጡት መልሽ (13.8%)ቱ በጭራሽ እና (37.9%) አልፎ አልፎ እንዲሁም (24.1%)ቱ አንዳንዴ በማለት በድምሩ (75.8%)ቱ መምህራኑ ተከታታይነት ባለው መልኩ ተባብሮ ለመስራት የሚያስትሏቸውን ማህበራዊ ክሂሎትን በትምህርትነት እንደማይሰጧቸው አመልክተዋል:: መምህራኑ የቡድን ስራዎችን በሚጡበት ጊዜ ሁሉ፣ ለቡድን አባላት የስራ ድርሻቸውን ከፋፍለው እንደማይሰጧቸው (44.8%)ቱ በጭራሽ እና (20.4%)ቱ አልፎ አልፎ እንዲሁም (22.4%)ቱ አንዳንዴ በማለት ባጠቃላይ (87.6%)ቱ የሰጡት ምላሽ ያስረዳል:: ከዚህ በተጨማሪ መምህራኑ የቡድን ስራዎቹን በሰጡ ቁጥር ለስራው የሚያስፈልገውን ጊዜ ከመነሻው የመግለጽ ሁኔታም እንደሌለ (18.9%)ቱ ሁልጊዜ እና (34.5%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ በድምሩ (53.4%)ቱ ብቻ የሰጡት ምላሽ ያሳያል:: በአንፃራዊነት ሲታይ መምህራኑ የቡድን ስራዎችን አሰራር አብራርተው የማቅረብ ሁኔታቸው የተሻለ መሆኑን (34.5%)ቱ ሁልጊዜ እና (37.5%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ በድምሩ (72.0%)ቱ የሰጡት ምላሽ ያሳያል:: ከዚህ በተጨማሪ በርካታ ተማሪዎች ለክፍል ሶስት ጥያቄ አምስት ምላሽ በሰጡት ወቅት፣ መምህራ የቡድን ስራ ሲሰጡ፣ እያንዳንዱ የቡድን አባል በስራው ላይ ያለውን ድርሻ በግልፅ አለማስረዳታቸው፣ በስራው እኩል ለመሳተፍ ችግር እንደጋረጠባቸው ገልፀዋል:: ሁኔታውን ተ33 "የቡድን ስራው የሚሰራው በአንድ ተማሪ ሊሆን ይችላል:: መምህሩ የያንዳንዱን የቡድን አባላት አስተዋፅኦ አይጠይቁም…" በማለት ይገልፃል:: ከዚህ ሌላ ግን፣ መምህራኑ አብዛኛውን ጊዜ የቡድን ስራዎችን አሰራር በማብራራት ስራዎቹን ግልጽ እንደሚያደርጉ በሰንጠረገፑ የቀረበው መረጃ ያሳያል::

### 4.1.3.3. የቡድን ስራ ክትትል

### ሀ. የክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትል

ሰንጠረዥ ሰባት፡ የመምህራኑን የክፍል ውስጥ የቡድን ስራ ክትትልን በተመለከተ የተማሪዎች መጠይቅ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | | አብዛኛውን ጊዜ 4 | | አንዳንድ ጊዜ 3 | | አልፎ አልፎ 2 | | በጭራሽ 1 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 16 | በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የቡድን ስራ ሲሰሩ መምህሩ/ሯ/ እየተዘዋወሩ ይከታተላሉ:: | 28 | 48.3 | 20 | 34.5 | 7 | 12.1 | 3 | 5.2 | - | - |
| 17 | መምህሩ/ሯ/ እየተዘዋወሩ የቡድን ስራዎችን በሚከታተሉበት ወቅት፣ ሁሉም ቡድኖች ጋ ይደርሳሉ:: | 31 | 53.4 | 15 | 25.9 | 6 | 10.3 | 5 | 8.6 | 1 | 1.7 |
| 9 | ስለ ቡድን ስራ አሰራር ተማሪዎች ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መምህሩ/ሯ/ ማብራሪያ ይሰጣሉ:: | 26 | 44.8 | 24 | 41.4 | 7 | 12.1 | 1 | 1.7 | - | - |
| 25 | በቡድን ስራ ወቅት፣ መምህሩ/ሯ/ ተማሪዎችን ያበረታታሉ:: | 6 | 10.3 | 21 | 36.2 | 14 | 24.1 | 14 | 24.1 | 3 | 5.2 |
| 27 | ከቡድን ስራ በኋላ ሁሉም ቡድኖች የስራ ውጤቶቻቸውን የማቅረብ (የማስደመጥ) ዕድል ያገኛሉ:: | 25 | 43.1 | 16 | 27.6 | 14 | 24.1 | 2 | 3.4 | 1 | 1.7 |
| 28 | ከቡድን ስራ በኋላ መምህሩ/ሯ/ ማጠቃለያ ይሰጣሉ:: | 35 | 60.3 | 15 | 25.9 | 4 | 6.9 | 3 | 3.4 | 1 | 1.7 |

መምህራኑ የቡድን ስራዎችን ከሰጡ በኋላ የተማሪዎቹን ስራዎች እየተዘዋወሩ እንደሚከታተሉ በሰንጠረዥ ሰባት ለ16ኛው ጥያቄ (48.3%)ቱ ሁልጊዜ እና (34.5%)ቱ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በድምሩ (82.8%)ቱ የሰጡት ምላሽ ያስረዳል:: በዝውውሩ ወቅት መምህራኑ ሁሉም ቡድኖች ዘንድ በአብዛኛው እንደሚደርሱም (53.4%)ቱ ሁልጊዜ እና (25.9%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ በደምሩ (79.3%)ቱ የሰጡት ምላሽ ያሳያል:: በክትትሉ ወቅት ተማሪዎቹ ስለ ቡድን ስራዎቹ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎችም መምህራኑ አብዛኛውን ጊዜ ምላሽ እንደሚሰጡ፣ በሰንጠረገፑ ለ9ኛው ጥያቄ (44.8%)ቱ ሁልጊዜ እና (41.4%)ቱ አብዛኘውን ጊዜ በማለት በድምሩ (86.2%)ቱ ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ ተችሏል:: በሌላ በኩል በቡድን መማር ሂደቱ የተማሪዎች ተሳትፎን የማበረታታት ሁኔታ አነስተኛ መሆኑን

(10.3%)ቱ ሁልጊዜ እና (36.2%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ በማለት በድምሩ (46.5%)ቱ ብቻ ሲመልሱ ቀሪዎች ከዚህ በተለየ ምላሽ የሰጡበት ሁኔታ ያስረዳል:: የቡድን ስራዎቹ ከተጠናቀቁ በኋላ የስራ ውጤቶቻቸውን የማስደመጥ (የማቅረብ) ዕድሉን በአብዛኛው እንደሚያገኙ (43.1%)ቱ ሁልጊዜ እና (27.6%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ በማለት በድምሩ (70.7%)ቱ ከሰጡት ምላሽ መረዳ ተችሏል:: መምህራኑ ከቡድን ስራዎቹ መጨረሻ ማጠቃለያ መስጠትን እንደሚያዘወትሩም (60.3%)ቱ ሁልጊዜ እና (25.9%)ቱ አብዛኛውን ጊዜ በማለት በድምሩ (86.2%)ቱ የሰጡት ምላሽ አሳይቷል::

### ሰ. ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎች ክትትል

ሰንጠረዥ ስምንት: ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎች ክትትልን በተመለከተ የተማሪዎች መጠይቅ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | | አብዛኛውን ጊዜ 4 | | አንዳንድ ጊዜ 3 | | አልፎ አልፎ 2 | | በጭራሽ 1 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 21 | ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ላይ፣ ጨርሶ የማይሳተፉ ተማሪዎች አሉ:: | 2 | 34 | 6 | 10.3 | 15 | 25.9 | 23 | 39.7 | 12 | 20.7 |
| 24 | ከክፍል ውጭ እንዲሰሩ የሚሰጡ የቡድን ስራዎች የሚሰሩት በጥቂት አባላት ብቻ ነው:: | 2 | 3.4 | 12 | 20.7 | 11 | 18.9 | 18 | 31.0 | 15 | 25.9 |
| 14 | ከክፍል ውጭ የሚሰራ የቡድን ስራን፣ አንድ የቡድን አባል ብቻውን ሰርቶ የሚያቀርብበት ሁኔታ አለ:: | 4 | 6.9 | 10 | 17.2 | 11 | 18.9 | 15 | 25.9 | 18 | 31.0 |
| 19 | ከክፍል ውጭ በሚሩ ስራዎች ላይ ሁሉም ተማሪዎች መሳተፍ አለመሳተፋቸውን መምህሩ/ሯ/ ይከታተላሉ:: | 3 | 5.2 | 12 | 20.7 | 15 | 25.9 | 15 | 25.9 | 13 | 22.4 |
| 29 | መምህሩ/ሯ/ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች፣ ሁሉም ተማሪዎች መሳተፉ አለመሳተፋቸውን በተለያዩ ዘዴዎች ያረጋግጣሉ:: | 2 | 3.4 | 9 | 15.5 | 15 | 25.9 | 18 | 31.0 | 14 | 24.1 |
| 26 | መምህሩ/ሯ/ በቡድን አባላት መካከል መግባባት መኖር አለመኖሩን ይከታተላሉ:: | 4 | 10.3 | 9 | 15.5 | 14 | 24.1 | 14 | 24.1 | 17 | 29.3 |

በሰንጠረዥ ስምንት በተራ ቁጥር 21፣ 24 እና 14 የተሰጡት የተማሪዎች ምላሾች እንደሚያስረዱት ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎች ላይ የማይሳተፉ ተማሪዎች የሚኖሩበት ወይም ስራው በጥቂት አባላት ብቻ የሚሰራበት ወይም አንድ ተማሪ ብቻ ስራውን ሰርቶ የሚያቀርብበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ነው:: መምህራኑ ከክፍል ውጭ የሚሰሩ ስራዎች ላይ ተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ በየጊዜው እንደማይከታተሉ ለሰንጠረዡ ለ19ኛው ጥያቄ (22.4%)ቱ በጭራሽ (25.9%)ቱ አልፎ አልፎ እንዲሁም (25.9%)ቱ አንዳንዴ በማለት በድምሩ (74.2%)ቱ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል:: ስራዎቹ ተሰርተው ከቀረቡም በኋላ እንኳን የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የተሳተፉትንና ያልተሳተፉትን ተማሪዎች የመለየት ሁኔታን መምህራኑ አዘውትረው ተግባራዊ እንደማያደርጉት (24.1%)ቱ በጭራሽ፣ (31.0%)ቱ አልፎ አልፎና (25.9%) አንዳንዴ በማለት በድምሩ (81.0%)ቱ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ይቻላል:: በስራው የተሳተፉና ያልተሳተፉትን መከታተል ብቻም ሳይሆን የቡድን አባላቱ በመግባባት መንፈስ መስራት አለመስራታቸው በየጊዜው የመከታተል ሁኔታም ቢሆን በአብዛኛው ተግባራዊ እንደማይሆን (29.3%)ቱ በጭራሽ፣ (24.1%)ቱ አልፎ አልፎና (24.1%)ቱ ደግሞ አንዳንዴ በማለት በድምሩ (77.5%) ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል::

በመጠይቁ ክፍል ሁለት ከቀረቡትና ከላይ በሰንጠረዥ ከተጠናቀሩት ምላሾች በተጨማሪ፣ በክፍል ሶስት ጥያቄ አምስት ምላሾቻቸውም ከክፍል ውጭ በሚደረጉ የቡድን ስራዎች ላይ የመምህራን ክትትል አነስተኛ እንደሆነ ገልፀዋል:: ለምሳሌ፣ ተ18 "ከክላስ (ከክፍል) ውጭ የሚሰጠውን የቡድን ስራ በደንብ አይከታተሉም::" በማለት ይገልፃል:: ስራዎቹ በሂደት ላይ እያሉ አለመከታተል ብቻ ሳይሆን፣ ተሰርተው ከቀረቡ በኂላም ቢሆን የተሳተፉና ያልተሳተፉ ተማሪዎችን የመለየት ሁኔታ እንደሌለ ተ21 "ተማሪዎች የቡድን ስራ ከሰሩ በኂላ እያንዳንዱ አባል በስራው መሳተፉ አይረጋገጥም::" በማለት ትገልፃለች::

4.1.3.4. የቡድን ስራ ግምገማና ውጤት አሰጣጥ

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- የቡድን ስራ ግምገማና ውጤት አሰጣጥን በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ. ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | | አብዛኛውን ጊዜ 4 | | አንዳንድ ጊዜ 3 | | አልፎ አልፎ 2 | | በጭራሽ 1 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 15 | ውጤት የሚኖረው የቡድን ስራ ሲሰጥ የመገምገሚያ መስፈርቱ በቅድሚያ ይገለፅልናል:: | 3 | 5.2 | 7 | 12.1 | 17 | 29.5 | 20 | 34.5 | 11 | 18.9 |
| 31 | ለአንድ የቡድን ስራ ውጤት ሲሰጥ፣ የቡድኑ አባላት በሙሉ አንድ አይነት ውጤትን ያገኛሉ:: | 20 | 34.5 | 18 | 31.0 | 6 | 10.3 | 6 | 10.3 | 8 | 13.8 |
| 34 | ለአንድ የቡድን ስራ ውጤት ሲሰጥ የቡድን አባላት በስራው ላይ እንዳላቸው ተሳትፎ መጠን የተለያዩ ውጤቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል:: | 6 | 10.3 | 6 | 10.3 | 12 | 20.7 | 9 | 15.5 | 25 | 34.1 |
| 30 | ቡድኖች ስራቸውን በመቀያየር፣ አንድ ቡድን የሌላቸውን ቡድን ስራ እንዲገመግምና አስተያየት እንዲሰጥ ያደረጋል:: | 4 | 6.9 | 15 | 25.9 | 11 | 18.9 | 16 | 27.9 | 12 | 20.9 |

በሰንጠረዥ ዘጠኝ ተማሪዎቹ ለ15ኛው ጥያቄ (18.9%)ቱ በጭራሽ፣ (34.5%)ቱ አልፎ አልፎና (29.5%)ቱ ደግሞ አንዳንዴ በማለት በድምሩ (82.9%)ቱ ከሰጡት ምላሽ

መምህራኑ ውጤት የሚኖረውን የቡድን ስራን በሚሰጡበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ የመገምገሚያ መስፈርቱን በቅድሚያ ለተማሪዎቹ እንደማይገልፁ ለመረዳት ተችሏል:: በሰንጠረዡ ለ31ኛው ጥያቄ (34.5%)ቱ ሁልጊዜ እና (31.0%)ቱ አብዛኛን ጊዜ በድምሩ (65.5%)ቱ እንደገለፁት ለአንድ የቡድን ስራ የሚሰጠው ውጤት ለቡድኑ አባላት በሙሉ በተመሳሳይ እንደሚሰጥ ነው:: ለአንድ የቡድን ስራ ውጤት ሲሰጥ በስራው ላይ እያንዳንዱ ተማሪ ያደረገውን ተሳትፎ በሚለካ መልኩ የተለያየ ውጤት የመስጠት ሁኔታ ግን እንደማይዘወተር (10.3%)ቱ ሁልጊዜ እና (10.3%) አብዛኛውን ጊዜ በድምሩ (20.6%)ቱ ብቻ የሰጡት ምላሽ ያስረዳል:: ከዚህም ሁኔታ መምህራኑ ከግላዊ ግምገማ ይልቅ ቡድናዊ ግምገማ ላይ ማተኮራቸውን መረዳት ተችሏል:: እንዲሁም ለ30ኛው ጥያቄ (20.9%)ቱ በጭራሽ ፣ (27.9%)ቱ አልፎ አልፎና (18.9%)ቱ አንዳንዴ በማለት በደምሩ (67.7%)ቱ እንደመለሱት ቡደኖች በየጊዜው ስራዎቻቸውን እየተለዋወጡ የቢጤ ግምገማን የሚያካሂዱበት ሁኔታ እድሉ የጠበበ መሆኑን ያሳያል::

በተጨማሪም አብዛኞቹ ተማሪዎች ለመጠይቁ ክፍል ሶስት ጥያቄ አራት በሰጡት ምላሽ የቡድን ስራዎች ተገምግመው ተገቢው ውጤት ስለማይሰጣቸው ደስተኞች እንዳልሆኑና የቡድን ስራ የመስራት ፍላጎታቸውም የቀዘቀዘ እንደሆነ ገልፀዋል:: የብዙዎቹን ሀሳብ በሚወክል መልኩ ተ3 "የቡድን ስራ ይሰጥ እንጂ … አስተማሪው የተሰጠንን የቡድን ስራ ወስደው ለተማሪ ማርክ አይሰጡም፤ በጣም ከባድ ጥያቄ ተሰጥቶን ተማሪዎች ሰርተን አምጥተን ካሰኛቸው 5 ማርክ ይይዛሉ:: ካላሰኛቸውም ማርክ አይዙም ይተዋሉ:: ይህ ለምን ይሆናል?" በማለት በምሬት ትገልፃለች:: የተሳትፏቸውን መጠን ባላገናዘበ መልኩ በሚሰጠው የቡድን ውጤትም ቅሬታ እንዳላቸው ተ18 "ለሁሉም ተማሪ እኩል ውጤት ይሰጣሉ:: ይህ ደግሞ የተማሪዎች ጥረትን ይቀንሳል ወይም እንዲሰሩ አያደርጋቸውም" ሲል ይገልፃል:: ብዙዎቹም በዚህ ሀሳብ ይስማማሉ:: ግልፅ የሆነ የመገምገሚያ መስፈርት እንደሌለና መስፈርት ካለም ተማሪዎቹ በሚገባ እንዲረዱት የማድረግ ጥረት እንዳሌለ፣ በዚህም የተነሳ፣ ተማሪዎች ወደ ተሳሳተ አመለካከት መሄዳቸውን ተ37 "የቡድን ስራ ውጤት ሲሰጠን በወረቀት ለተፃፈው አንድ አይነት ውጤት ይሰጥና ለፕሬዜንቴሽን የተለያየ ውጤት ይሰጠናል:: በውጤቱ ደስተኛ አይደለሁም ምክንያቱም ውጤት ሚሰጡት አብዛኛውን ጊዜ በዘርና በሀይማኖት ነው" በማለት ከሰጠችው ምላሽ መገንዘብ ይቻላል::

### 4.1.3.5. የቡድን መማር ዕብረቃ

ሰንጠረዥ አስር:- የቡድን መማር ዕብረቃ ማካሄድን በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | | አብዛኛውን ጊዜ 4 | | አንዳንድ ጊዜ 3 | | አልፎ አልፎ 2 | | በጭራሽ 1 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 32 | ተማሪዎች የቡድን አሰራራቸውን ደካማና ጠንካራ ጎኖች እንደገመግሙ ይደርጋል:: | 7 | 12.1 | 13 | 22.4 | 9 | 15.5 | 8 | 13.8 | 21 | 43.1 |
| 33 | መምህሩ/ሯ/ በቡድን መማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ ይጋብዛሉ:: | 3 | 5.2 | 13 | 22.4 | 7 | 12.1 | 17 | 29.3 | 18 | 31.0 |

ተማሪዎች የቡድን አሰራራቸውን ጥንካሬና ድክመት በየጊዜው እንደማይገመግሙ (56.9%) በጭራሽና አልፎ አልፎ በማለት እንዲሁም (15.5%) አንዳንዴ በማለት በድምሩ (72.4%)ቱ የሰጡት ምላሽ ያሳያል:: የራሳቸውን የቡድን መማር ብቻም ሳይሆን አጠቃላይ የቡድን መማር ማስተማር ሂደቱ ላይ አስተያየት በየጊዜው የመስጠት እድላቸው ዝቅተኛ እንደሆነ (31.0%) በጭራሽ እና (29.3%)ቱ አልፎ አልፎ እንዲሁም (12.1%)ቱ አንዳንዴ በድምሩ (72.4%)ቱ በማለት የሰጡት ምላሽ ያሳያል::

## 4.2. ማብራሪያ (Discussion)

የንዑስ ቡድን ማስተማርን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ በቂ ዝግጅት ማድረግ ከመምህራን እንደሚጠበቅ በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.2.1. ስር የቀረቡት የምሁራን ሀሳቦች አስረድተዋል:: በተለይም Westberg and Jason (1996) እንደገለፁት በዝግጅቱ ወቅት ስለሚመሰረቱት ቡድኖች አባላት ብዛት፣ ስብጥር፣ በቡድን ስራነት ስለሚቀርቡት ጥያቄዎች፣ ለቡድን ስራው ስለሚያስፈልጉ የመርጃ መሳሪያዎች ወዘተ. ትኩረት መስጠት ይገባል:: የመሰረታዊ አማርኛ መምህራኑ ስለ ማስተማር ዝግጅታቸው የሰጧቸው ምላሾች ግን ይህንን የሚያሳዩ ሆነው አልተገኙም:: መምህራኑ እንደገለፁት፣ በዝግጅታቸው ወቅት

ትኩረት የሚሰጡት የቡድን ስራ ጥያቄዎችን ለመምረጥና ለማዘጋጀት ብቻ ነው:: ይህ የመምህራኑ ዝግጅት ምሁራኑ በዝግጅት፣ ወቅት ትኩረት ሊያገኙ ይገባል ከሚሏቸውና በአባሪ አንድ እንደቀረበው Putnam (1997) በትምህርት እቅድ ቅጽ ላይ ጭምር ሊሰፍሩ ይገባቸዋል፣ ከሚሏቸው ዝርዝር ክንውኖች አንፃር ሲታይ አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል::

የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራኑ፣ በቃለ መጠይቁ ወቅት እንደገለፁት፣ የንዑስ ቡድኖችን የሚያደራጁት ከ4-8 ባሉ የተማሪዎች ብዛት ነው:: እንደ መምህራኑ ገለፃ በአንድ ቡድን አባልነት የሚደራጁ ተማሪዎች የሚመረጡባቸው መስፈርቶችም በክፍል ወስጥ ያላቸው የአቀማመጥ መቀራረብ፣ የመታወቂያ ቁጥር ቀደም ተከተል፣ የተማሪዎች ፍላጎት የመሳሰሉት ናቸው:: አባላቱም በአንድ ቡድን አባልነት አብረው የሚቆዩትም በአብዛኛው ለአጭር ጊዜ ብቻ እንደሆነ መምህራኑ አስረድተዋል:: በምልከታዎቹ ወቅት የታዩት የቡድን አባላት ቁጥርና የአባላት አመራረጥ ሁኔታ እንዲሁም፣ ተማሪዎቹ የቡድን አባላት ቁጥር፣ አመራረጥና አብሮ ቆይታን አስመልክቶ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾችም የመምህራኑን ምላሽ የሚያረጋግጡ ሆነው ተገኝተዋል:: ይሁን እንጂ፣ የዚህ አይነቱ የቡድን አደረጃጀት ምሁራኑ በምዕራፍ ሁለት በ2.2.2. ስር ስለ ንዑስ ቡድን አደረጃጀት ከሚያነሷቸው ሀሳቦች ጋር ሲነፃፀሩ፣ ከአባላት ቁጥር በስተቀር አባላቱ የሚመረጡባቸው መስፈርቶችም ሆኑ በአንድ ቡድን አባልነት አብረው እንዲቆዩ የሚደረግበት ጊዜ ተገቢ አሰራርን የተከተሉ ሆነው አልተገኙም::

በምልከታዎቹ ወቅት እንደታየው የተማሪዎቹ የክፍል ውስጥ ቡድናዊ አቀማመጥ አባላቱን ፊት ለፊት መተያየት የሚያስችሉ ሆነው ታይተዋል:: (ፎቶግራፎቹን ይመለከቷል) ከዚህ በተጨማሪ በሰንጠረዥ አምስት ለጥያቄ 1 እና 4 ተማሪዎቹ የሰጧቸው ምላሾችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ ሆነው ተገኝተዋል:: ይህ የተማሪዎች ቡድናዊ አቀማመጥ Johnson and Johnson (1990) መሆን አለበት ከሚሉት ሀሳብና በአባሪ ሁለት ላይ እና Matiru et al (1995) እና Wragg (1999) ካቀረቡት የአቀማመጥ ቅርፅ ጋር የሚመሳሰል ሆኖ ተገኝቷል:: በቡድን በቡድን በተቀመጡ ተማሪዎች መካከል መኖር ስለሚገባው የመዘዋወሪያ ክፍተት፣ በሰንጠረዥ አምስት እንደቀረበው (60.4%)ቱ ሁልጊዜ እና አብዛኛውን ጊዜ በማለት ለመጠይቁ ምላሽ ቢሰጡም፣ ከተደረጉት አምስት ምልከታዎች በአራቱ ተማሪዎቹ እንዳሉት ሆኖ አልተገኘም:: በአራቱ ምልከታዎች ወቅት እንደታየው

የመዘዋወሪያ ክፍተቶቹ ልክ በአባሪ ሶስት ላይ Bruke (2000) እንዳሳዩት፣ በሁሉም ቡድኖች መካከል በተመጣጠነ ሁኔታ ያለ ሆኖ አልተገኘም። በአንዳንድ ቡድኖች መካከል በቂ የመዘዋወሪያ ክፍተት ሲኖር አንዳንድ ቡድኖች ግን በጣም ተጠጋግተው ስለተቀመጡ መምህራኑ በመሀከላቸው እንደልብ እየተዘዋወሩ የቡድኖቹን ስራዎች ለመከታተል የሚያስችሉ አልነበሩም።

በጥናቱ የተካተቱት መምህራን፣ ተማሪዎቻቸው በቡድን ለመስራት የሚያስችሏቸውን የትብብራዊ ክሂሎትን በየጊዜው በትምህርትነት እንደማይሰጧቸው ከምላሾቻቸው መረዳት ተችሏል። (75.8%)ቱ ተማሪዎችም በሰንጠረዥ ስድስት ለ1ኛው ጥያቄ በጭራሽ፣ አልፎ አልፎና አንዳንዴ በማለት የሰጡት ምላሽም ይህንኑ የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ሁኔታ በምዕራፍ ሁለት በ2.2.1. እና በ2.2.3. ስር ከቀረቡት የምሁራን ሀሳቦች በተለይ ደግሞ Johnson and Johnson (1990፣29) "በቡድን ሆኖ እንዴት መስራት እንደሚቻል ትምህርት ካልተሰጣቸው ተማሪዎች፣ በቡድን መስራትን መጠበቅ አይቻልም" በማለት በአጽንኦት ከገለፁት ሀሳብ ጋር አብሮ የሚሄድ ሆኖ አልተገኘም። እነዚሁ በጥናቱ የተካተቱ ሶስት መምህራን የቡድን ስራን ሲሰጡ ለአባላቱ በሙሉ የየስራ ድርሻን ከፋፍለው እንደማይሰጡ ገልፀዋል። ይህንኑ ነጥብ በተመለከተ በመጠይቁ ለቀረበው ጥያቄም (65.2%)ቱ በጭራሽ እና አልፎ አልፎ፣ (22.4%)ቱ ደግሞ አንዳንዴ በድምሩ (87.6%)ቱ የሰጧቸው ምላሾች እንዲሁም በተደረጉት አምስት ምልከታዎች፣ በአንዳቸውም እንኳን ቢሆን ለቡድን አባላት የስራ ድርሻን ከፋፍሎ የመስጠት ሁኔታ አለመታየት ሀሳቡን የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም እንደ Davis (1993) ፣ Kain (2003) ወዘተ. ያሉ ምሁራን ለያንዳንዱ አባል የስራ ድርሻውን መስጠት ይገባል የሚሉት ሀሳብ፣ በመምህራኑ ተግባራዊ እንደማይሆን ለመገንዘብ ተችሏል።

መምህራኑ የቡድን ስራዎቹን ግልፅ አድርገው እንደሚያቀርቡ ግን፣ በተደረጉት ምልከታዎች ለማየት ተችሏል (ሰንጠረዥ ሶስትን ይመለከቷል)። አብዛኞዎቹ ተማሪዎች ይህንን አስመልክቶ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾችም (ሰንጠረዥ ስድስት ጥያቄ 3 ና 5 ይመልከቱ) የምልከታውን ሀሳብ የሚደግፉ ሆነው ተገኝተዋል። ባጠቃላይ፣ በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.2.2. ስር ከተነሱት የምሁራኑ ሀሳቦች አንፃር ሲታይ፣ የመምህራኑ አቀራረብ ለተማሪዎቹ የቡድን መማር አላማዎችንና የእርስ በርስ ግንኙነት ክሂሎትን የማያስተዋውቅና እያንዳንዱ አባል በቡድን ስራው በሀላፊነት ስሜት የድርሻውን

በማበርከት ተሳታፊ እንዲሆኑ የማያደርግ ሆኖ ተገኝቷል:: ግልፅ በሆነ ትዕዛዝ የቡድን ስራን ከመስጠት አኳያ ግን፣ ጥሩ ገጽታ እንዳለው ለመረዳት ተችሏል::

በቃለመጠይቁ ወቅት መምህራኑ ከሰጧቸው ምላሾች፣ በምልከታዎቹ ወቅት ከታዩት ሁኔታዎች (ሰንጠረዥ አራትን ይመልከቱ) እንዲሁም ተማሪዎቹ በሰንጠረዥ ሰባት ላይ ለጥያቄ 16፣ 9 እና 27 ከሰጧቸው ምላሾች፣ መምህራኑ የቡድን ስራዎችን ከሰጡ በኋላ በክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ ስራዎቻቸውን እንደሚከታተሉ፣ ለተማሪዎቹ ጥያቄዎች ምላሾችን እንደሚሰጡና እገዛ እንደሚያደርጉ ለመረዳት ተችሏል:: በስራዎቹ በመጨረሻም፣ በአብዛኛው እያንዳንዱ ቡድን የስራ ውጤቱን እንዲያቀርብ እንደሚያደርጉ ከተደረጉት ምልከታዎችና (70.7%)ቱ ሁልጊዜ እና አብዛኛውን ጊዜ በማለት ከሰጡት ምላሽ ለመገንዘብ ተችሏል:: በሌላ በኩል፣ በተደረጉት ምልከታዎች ማስተዋል እንደተቻለው የመምህራኑ የቡድን ስራ ክትትል በቡድኖች ላይ እንጂ በተናጠል የያንዳንዱን ተማሪ ተሳትፎ በመከታተል ላይ ያነጣጠረ ሆኖ አልታየም:: ተማሪዎቹ በሚወያዩበትም ሆነ መጨረሻ ላይ የስራዎቻቸውን ውጤቶች በሚያቀርቡበት ወቅት፣ ማበረታቻ የመስጠት ሁኔታም ጎልቶ አልታየም:: በሰንጠረዥ ሰባት ለመጠይቁ ጥያቄ 25 የተሰጠው የተማሪዎች ምላሽም ይህንኑ የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል:: ይህ የመምህራ የክፍል ወስጥ የቡድን ስራ ክትትል፣ በምዕራፍ ሁለት እንደ Hougen (1998) ፣ Ur (1996) የመሳሰሉት ምሁራን ካቀረቧቸው ሀሳቦች አንፃር ሲታይ ከማበረታቻ ማነስና የያንዳንዱን አባል ተሳትፎ በተናጠል ካለመከታተል በስተቀር አብዛኞቹን የሚያሟላ ሆኖ ተገኝቷል::

መምህራኑ በቃለ መጠይቅ ወቅት እንደገለፁት ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ሁሉም ተማሪዎች እኩል ይሳተፋሉ የሚል ግምት የላቸውም:: የመምህራኑ ግምት ትክክል እንደሆነም ተማሪዎቹ ለቃለ መጠይቁ 14ኛ፣ 12ኛ እና 24ኛ ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች ያረጋግጣሉ (ሰንጠረዥ ስምንትን ይመለከቷል):: ይሁን እንጂ፣ የመምህራኑ ምላሽ እንደሚያስረዳው የቡድን ስራዎቹ ከመጠናቀቃቸው በፊት፣ ማለትም ስራዎቹ በሂደት ላይ ሳሉ የሚደረግ ምንም አይነት ክትትል የለም:: ተማሪዎቹም ይህንን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ፣ (48.3%) ክትትሉ እንደሌለ፣ ቢኖርም አናሳ እንደሆነ በጭራሽና አልፎ አልፎ ሲሉ፣ እንዲሁም (25.9%) አንዳንዴ በድምሩ (74.2%) ሲሉ የሰጧቸው ምላሾችና ለመጠይቁ ክፍል ሶስት ጥያቄ አምስት የሰጧቸው ምላሾች ያስረዳሉ::

በተጨማሪም መምህራኑ በቡድን አባላት መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ እንደሚችሉ ቢገምቱም ተማሪዎቹ መጥተው ካልነገሯቸው ወይም ከሶስተኛ ወገን ከውጭ ካልሰሙ በስተቀር የመከታተያ ስልቶች እንደሌሏቸው የሰጧቸው ምላሾች ያስረዳሉ:: ተማሪዎቹም፣ መምህራኑ በቡድን አባላት መካከል መግባባት መኖር አለመኖሩን የመከታተል ሁኔታቸው አነስተኛ መሆኑን (53.4%) "በጭራሽ" እና "አልፎ አልፎ" እንዲሁም (24.1%) "አንዳንዴ" በማለት ገልፀዋል:: መምህራኑ ግጭቶች እንዳሉ ከተረዱ በኋላም ተማሪዎቹን ተስማምታችሁ ስሩ ብሎ ከመምከርና ከመገሰፅ ወይም የተጋጩትን ተማሪዎች ወደ ተለያየ ቡድን ከመነጣጠል ውጭ፣ ተማሪዎች ግጭቶቻቸውን የሚፈቱባቸውን መንገዶች በማስተማር ራሳቸው እንደፈቱ የሚያደርጉባቸው ሁኔታዎች የሉም:: ለቡድን ስራ መስሪያ ወይም ማቅረቢያ የሚሆን ምንም አይነት የፅህፈት መሳሪያዎችን ለተማሪዎቹ እንደማያሰጡም መምህራኑ ገልፀዋል:: ተማሪዎቹም ይህንን በተመለከተ በመጠየቁ ክፍል ሁለት ጥያቄ 23 ለቀረበው ጥያቄም (91.3%) "በጭራሽ"ና "አልፎ አልፎ" የሚል ምላሽ በመስጠት አረጋግጠዋል:: ይህ ሁኔታ በምዕራፍ ሁለት በቁጥር 2.2.4. ስር ምሁራን ካቀረቧቸው ሀሳቦች አንፃር ሲታይ መምህራኑ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ላይ ያላቸው ክትትል፣ በተለይም Davis (1993) የጊዜ ሰሌዳ አውጥተው በየጊዜው ሂደቱን መከታተል አለባቸው ከሚሉት አንፃር፣ የለም በሚባል ደረጃ የሚገኝ ነው::

መምህራኑ ስለ ቡድን ስራ ግምገማና ውጤት አሰጣጣቸው በቃለ መጠይቁ ወቅት ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት እንደተቻለው፣ አብዛኞቹ የቡድን ስራዎች ላይ ግምገማ አያካሂዱም፤ ውጤትም አይዙም:: ለአንዳንዶቹ የቡድን ስራዎች ውጤት ቢይዙም እንኳን አነስተኛ ውጤትን ብቻ ይሰጣሉ:: ተማሪዎቹ በመጠይቁ ክፍል ሶስት ጥያቄ አምስት የሰጧቸው ምላሾችም የቡድን ስራ አገማገሙ መምህራኑ በገለፁት መሰረት እንደሚካሄድ የሚያረጋግጥ ሆኖ ተገኝተዋል:: ይሁን እንጂ፣ ይህ የቡድን ስራን ሰጥቶ አለመገምገምም ሆነ፣ ለቡድን ስራ ጥቂት ውጤትን ብቻ የመስጠት ሁኔታ ብዙዎቹን ተማሪዎች ቅር እንዳሰኘና ለቡድን ስራ ያላቸው ፍላጎት እንዲቀዘቅዝ እንዳደረገ ከምላሾቻቸው ለመረዳት ተችሏል:: Putnam (1997) በቡድን የሚማሩ ተማሪዎች ከያንዳንዱ የቡድን ስራ በኋላ ወይም እንዳመቺነቱ ስራዎቻቸው ሊገመገሙ ይገባል ሲሉ ካቀረቡት ሀሳብ ጋርም የሚስማማ ሆኖ አልተገኘም::

አብዛኞቹን የቡድን ስራዎች አለመገምገምና ወጤት አለመስጠት ብቻም ሳይሆን፣ የሚገመገሙት ጥቂቶቹ የቡድን ስራዎችንም ቢሆኑ የሚገመግሙትና ውጤቶችን

የሚሰጡት በአብዛኛው በመስፈርቶች ላይ ተመስርተው አለመሆኑን ከመምህራኑ ምላሾች ለመገንዘብ ተችሏል። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የመገምገሚያ መስፈርትን መሰረት አድርጎ ስራዎቹን ለመገምገም ሙከራ ቢኖርም፣ መስፈርቱ ግን በቅድሚያ ለተማሪዎቹ እንደማይገለፅ ተማሪዎቹ ለመጠይቁ ክፍል ሶስት ጥያቄ 4 ከሰጧቸው ምላሾችና በሰንጠረዥ ዘጠኝ ለጥያቄ 15 ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል። ይህ የመምህራኑ አሰራር Stone (1994) የቡድን ስራ ግምገማ መስፈርትን መሰረት ያደረገና መስፈርቱም በቅድሚያ ለተማሪዎቹ ተገልፆላቸው የሚካሄድ መሆን አለበት ከሚሉት ጋር የሚጣጣም ሆኖ አልተገኘም።

በሌላ በኩል፣ ከመምህራኑ የቃል መጠይቅ ምላሾች እንዲሁም በሰንጠረዥ ዘጠኝ ተማረዎቹ ለመጠይቁ 31ኛ እና 34ኛ ጥያቄዎች ከሰጧቸው ምላሾች የመምህራ የቡድን ስራ ግምገማና ውጤት አሰጣጥ፣ የአንድ ቡድንን ድክመትና ጥንካሬን እንጂ በቡድኑ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ድክመትና ጥንካሬ በመለካት ላይ ያተኮረ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህ፣ የመምህራኑ የቡድን ሰራ አገማገም Dolmans et al (2003) በቡድን ስራ ግምገማ ወቅት ከቡድናዊ ግምገማ ይልቅ ግላዊ ግምገማ በገዘፉ መታየት አለበት ሲሉ ካቀረቡት ሀሳብ አንፃር ሲታይ በተቃራኒው የሚካሄድ ሆኖ ተገኝቷል። ከዚህ ሌላ ከመምህራኑ ምላሾችና (67.7%) ተማሪዎች ለመጠይቁ 30ኛ ጥያቄ በጭራሽ፣ አልፎ አልፎና አንዳንዴ በማለት ከሰጡት ምላሽ፣ የቡድን ስራ ላይ የቢጤ ግምገማ በተጠናከረ መልኩ እንደሚያካሄድ ለመረዳት ተችሏል። ሶስቱም መምህር በተመሳሳይ መልኩ እንደገለፁት ደግሞ፣ ተማሪዎች በቡድን መማር ሂደት ያሳዩትን ለውጥ ለማወቅ እንዲችሉ የራስ ግምገማን በየጊዜው እንዲያካሂዱ እንዳማይደረግ ለመገንዘብ ተችሏል። በአጠቃላይ ሲታይ የመምህራኑ የቡድን ስራ ግምገማና ውጤት አሰጣጥ ምሁራኑ መሆን አለባቸው ብለው ካቀረቧቸው አሰራሮች ጋር የተራራቀ ሆኖ ታይቷል።

የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራኑ፣ ከያንዳንዱ የቡድን ማስተማር በኋላ በማስተማር ሂደቱ የነበሩትን ደካማና ጠንካራ ጎኖች ለመገምገም የማስተማር ዕብረቃን እንደማያካሂዱ የሰጧቸው ምላሾች ያስረዳሉ። በመሆኑም (Jaques 1998 ፣ Botes 1994 ፣ Larrive 2005) እንደ ማንኛውም የማስተማር ሂደት፣ የንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደት የሚጠይቀው አንዱ ተግባር የማስተማር ዕብረቃ ማካሄድ ነው ሲሉ ያስገነዘቡት ሀሳብ ተፈፃሚ ሆኖ አልተገኘም። ተማሪዎቹም ቢሆኑ ከያንዳንዱ የቡድን መማር ሂደታቸው ትምህርት

ማግኘት እንዲችሉ፣ ዕብረታን እንዲያካሂዱ መምህራኑ እንደማይረዷቸው ለመጠይቁ 32ኛ ጥያቄ (72.4%)ቱ በጭራሽ፣ አልፎ አልፎና አንዳንዴ በማለት የሰጡት ምላሽ አሳይቷል:: በየጊዜው የቡድን መማር ማስተማር ሂደቱን እንዲገመግሙ ዕድሉ እንደማይሰጣቸውም፣ ለመጠይቁ 33ኛ ጥያቄ (72.4%)ቱ በጭራሽ፣ አልፎ አልፎና አንዳንዴ በማለት ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል:: ይህ ሁኔታ በምዕራፍ ሁለት ላይ እነ (Putnam 1997፣ Davis 1993፣ Jaques 1989፣ Dolmans et al 2003) ተማሪዎች በራሳቸው የቡድን መማር ሂደት ላይም ሆነ በቡድን መማር ማስተማር ሂደቱ ላይ በየጊዜው ዕብረታ ማካሂድ አለባቸው በማለት ያቀረቡት ሀሳብን፣ መምህራኑ ተግባራዊ እንደማያደርጉ አስረድቷል::

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል::

### 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራንን የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር ማጥናት ነው:: ይህንንም ማድረግ ያስችላሉ በሚል ጥናቱ ሊመልሳቸው ያነሳቸው ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ::

1. መምህራኑ በንዑስ ቡድን ለማስተማር ምን አይነት ቅድመ ዝግጅትን ያደርጋሉ?
2. የንዑስ ቡድኖችንና ክፍሎችን እንዴት ያደራጃሉ?
3. የቡድን ስራ አላማንና የቡድን ስራዎችን ለተማሪዎቻቸው ያስረዳሉ?
4. የንዑስ ቡድኖች ስራዎች ክትትላቸው ምን ይመስላል?
5. የንዑስ ቡድን ስራዎችንና የንዑስ ቡድን መማር ሂደትን በሚገባ ይገመግማሉ?

ጥያቄዎቹን ለመመለስም በኮሌጁ ያሉትንና በዚህ አመት (2000ዓ.ም) የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስን ያስተማሩ ሶስት የአማርኛ መምህራን በሙሉ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል:: የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ሲያደርጉ የክፍል ምልከታ በማካሄድ፣ለመምህራ ቃለ መጠይቅ በማድረግና በእጣ ንሞና የተመረጡ ተማሪዎች መጠይቅ እንዲሞሉ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል:: መረጃዎቹ ከተሰበሰቡና ከተደራጁ በኋላ በተናጠል ተተንትነዋል:: እነዚህ በተናጠል የተተነተኑት መረጃዎች እርስ በርስ ያላቸውን መደጋገፍ ወይም ልዩነት፣ እንዲሁም በክለሳ ድርሳናት ከተነሱት ሀሳቦች ጋር ያላቸው ዝምድና በማብራሪያው ንዑስ ክፍል ቀርቧል:: በተደረገው ትንተናና ማብራሪያም የሚከተሉት ማጠቃለያዎች ላይ ለመድረስ ተችሏል::

- መምህራኑ ለንዑስ ቡድን ማስተማር ዝግጅት በሚያደርጉበት ወቅት ትኩረት የሚሰጡት፣ ለንዑስ ቡድን ስራነት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመምረጥና ለማዘጋጀት ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ በያንዳንዱ የንዑስ ቡድን ማስተማር ሂደቶች ምን አይነት ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ፣ ከወዲሁ በመገመት እነሱም ሆኑ ተማሪዎቹ ሊያከናውናቸው

የሚገቡ ተግባራትን በዝርዝር የማቀድ ሁኔታ አልታየም:: ስለዚህ ለንዑስ ቡድን ማስተማር የሚያደርጉት ዝግጅት የተሟላ ሆኖ አልተገኘም::

- የሚያደራጇቸው የንዑስ ቡድኖች፣ ከአባላት ቁጥር አንፃር ተገቢ ቢሆኑም ተፈላጊውን የአባላት ቅይጥነትና ውሁድነት ከመፍጠር አኳያ ግን ተገቢነት ያላቸው ሆነው አልተገኙም:: የንዑስ ቡድኖች አባላት አመራረጣቸው፣ በቅድሚያ ዝርዝር የሆነ የተማሪዎችን ዳራ (ሃይማኖት፣ ብሄረሰብ፣ የትምህርት ችሎታ ወዘተ) መዝግቦ በመያዝ በዚያ ላይ ተመስረቶ የሚደረግ ሳይሆን፣ እንደ መታወቂያ ቁጥር ቅደም ተከተል፣ የአቀማመጥ መቀራረብ፣ በፍላጎት መመራረጥ የመሳሰሉትን መስፈርቶች መሰረት ያደረገ ነው:: ይህ ደግሞ ተገቢ የሆነና የተመጣጠነ ቅይጥነትን ለመፍጠር ካለማስቻሉም በተጨማሪ፣ በተቃራኒው ተመሳሳይነትን ብቻ ሊፈጥርም የሚችል ነው:: መምህራኑ፣ የቡድን አባላት ለረዥም ጊዜ አብረው በአንድነት እንዲቆዩ ስለማያደርጉም፣ አሰራራቸው ተፈላጊውን የአባላት ውሁድነት ለመፍጠር የሚያስችል አይደለም:: በመሆኑም የንዑስ ቡድኖችን የሚያደራጁበት ሁኔታ ባመዛኙ ችግሮች የሚንፀባረቁበት ሆኖ ታይቷል:: በሌላ በኩል፣ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ፣ በቡድን በቡድን ሆነው የሚቀመጡባቸው አቀማመጦች የቡድን አባላት መቀራረብንና እርስ በርስ መተያየትን የሚፈጥሩ በመሆናቸው የክፍል ውስጥ አደረጃጀቱ በአብዛኛው አዎንታዊ ሁኔታ የሚንፀባረቅበት ሆኖ ተገኝቷል::

- መምህራኑ ቡድኖችን ከማደራጀትና የቡድን ስራዎችን ከመስጠት ውጭ፣ ስለቡድን ስራ ዓላማም ሆነ ስለ ትብብራዊ ክሂሎት ተማሪዎቻቸውን የሚያስተምሩባቸው ሁኔታዎች የሉም ለማለት ይቻላል:: በአንፃራዊነት ሲታይ የቡድን ስራዎቹን አሰራር የመግለጽና የማብራራት ሁኔታ የተሻለ ሆኖ ቢገኝም፣ እያንዳንዱ የቡድን አባል በስራው ላይ ያለውን ድርሻ በግልፅ የማሳወቅ ሁኔታ ግን አይታይም:: የቡድን ስራው ሲሰጥም ከመነሻው፣ ስራው የሚፈጀውን ጊዜና የመገምገሚያ መስፈርትን የማሳወቅ ሁኔታ ጎልቶ አይታይም:: ስለዚህ፣ መምህራኑ የቡድን ስራ ዓላማንም ሆነ የቡድን ስራዎችን ለተማሪዎቹ በሚገባ ያስረዳሉ ማለት አይቻልም::

- የተገኙት መረጃዎች እንደሚያስረዱት መምህራኑ የተሟላ ነው ባይባልም፣ በአንፃራዊነት ሲታይ የክፍል ውስጥ የቡድን ስራዎችን፣ በተሻለ ሁኔታ ይከታተላሉ

ማለት ይቻላል:: ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራዎችን ሂደቶች ማለትም፣ ሁሉም አባላት መሳተፍ አለመሳተፋቸውን፣ በመግባባት መንፈስ መስራት አለመስራታቸውን፣ ወዘተ የመከታተልና ችግሮች ስያጋጥሙም በተገቢው ሁኔታ እንደፈቱ የማድረግ ጥረት ግን ፈፅሞ የለም ለማለት ይቻላል::

- መምህራኑ አብዛኞቹን የቡድን ስራዎችንም የሚገመግሙ ሆነው አልተገኙም:: አልፎ አልፎ ለሚገመግሟቸው የቡድን ስራዎችም ቢሆኑ የሚሰጧቸው ውጤቶች አነስተኛ ከመሆናቸውም በተጨማሪ፣ የመገምገሚያ መስፈርቶቹ በቅድሚያ ለተማሪዎቹ የማይገለፁባቸው ሆነው ተገኝተዋል:: በተጨማሪም፣ በግምገማው የሚሰጡት ውጤቶች፣ ግላዊ ተሳትፎን በመለካት ላይ ያተኩሩ መሆን ሲገባቸው በተቃራኒው ቡድናዊ ብቃትን በመለካት ላይ ያተኩሩ ሆነው ተገኝተዋል:: ተማሪዎቹም ቢሆኑ በቡድን መማር ያላቸውን ለውጥ ለማወቅ፣ የራስ ግምገማንም ሆነ የቢጤ ግምገማን የሚያደርጉበት ሁኔታ የለም ለማለት ይቻለል:: ስለዚህ፣ መምህራኑ ተገቢ የቡድን ስራ ግምገማና ውጤት አሰጣጥን ያካሂዳሉ ለማለት አይቻልም::

- መምህራኑ ከያንዳንዱ የንዑስ ቡድን ማስተማር በኋላ የቡድን ማስተማር አተገባበራቸው ውጤታማ መሆን አለመሆኑን በዕብረቃ የሚፈትሹበት፣ ተማሪዎቹም በቡድን መማር ማስተማር ሂደቱ ላይ አስተያየት የሚሰጡበት እንዲሁም፣ የቡደን ማስተማር ዘዴያቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚገመግሙበት አሰራር ያላቸው ሆነው አልተገኘም:: ስለዚህ የቡደን ማስተማር ዘዴ አተገባበራቸው ያለ ዕብረቃ የሚካሄድ፣ በሂደቱ ያሉ ጥንካሬዎችንም ሆኑ ችግሮችን ለመለየት የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል::

## 5.2. አስተያየት

መምህራኑ በንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር የሚታዩባቸውን አንደንድ ችግሮች በማስተካከል፣ ለወደፊቱ በተሻለ ሁኔታ የቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ፣ አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶች ያቀርባል::

- መምህራኑ የሚገኙበት የትምህርት ክፍልም ሆነ የኮሌጁን ትምህርታዊ ጉዳዮች የሚመሩ አካላት የመምህራኑን ጥረት ሊያግዙ የሚችሉ፣ የቡድን ማስተማር አተገባበር ግንዛቤ ማዳበሪያ መድረኮች የሚመቻቹባቸውን ሁኔታዎች ቢፈጥሩ፤

- መምህራኑ የግላቸውን ጥረት በማድረግ ስለንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ ምንነትም ሆነ አተገባበር፣ ግንዛቤያቸውን ይበልጥ ሊያዳብሩላቸው የሚችሉ ጥናታዊ ፅሁፎችን፣ መፅሀፎችን፣ የድረ-ገጽ መረጃዎችን ወዘተ በማንበብ እውቀታቸውን ቢያዳብሩ፤

- በኮሌጁ ከሚገኙ ሌሎች መምህራን ጋር ስለ ጉዳዩ ቢወያዩ፣ አንዳቸው የሌላቸውን የቡድን ማስተማር አተገባበር ምልከታ በማድረግ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በማንሳት የሚማማሩበት ሁኔታን ቢያመቻቹ፤

- ከያንዳንዱ የቡድን ማስተማር ሂደት በኋላ፣ የቡደን ማስተማራቸው ምን ይመስል እንደነበር ዕብረታ በማካሄድ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ የቡድን ማስተማር አተገባበራቸውን እያሻሻሉ ለመሄድ ጥረት ቢያደርጉ፤

- ለተማሪዎቻቸው አስተያየት ታላቅ ግምት በመስጠት፣ የቡድን ማስተማር ሂደቱ ላይ በየጊዜው ተማሪዎቹ ግልፅ አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ፣ ከተማሪዎቻቸው በሚገኙ አስተያየቶች የቡድን ማስተማር አተገባበራቸውን እየገመገሙ የመሄድ ልምድን ቢያዳብሩ፤

# ዋቢ መፅሐፍት


ሙሉጌታ ይታየው (1996) "የተማሪ ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በሰርተፍኬት መርሃ ትምህርት እንደታየው::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)::

ኤልያስ አድማሱ (1997) "በኦሮሚያ መምህራን ኮሌጅ ውስጥ መሰረታዊ አማርኛን የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪ ተኮር አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት ለኤም.ኤ.ዲግሪ መሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)::

ያለው እንዳወቀ (2006). <u>የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር</u>:: አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚች::

Antil, R.L. et al (1998). "Cooperative Learning: Prevalence, Conceptualizations, and the Relation Between Research and Practice." <u>American Educational Research Journal.</u> Vol.35, No.3, PP.419-454. <<u>http://www.jstor.org</u>>

Atkins, J. et al. (1996). <u>Skills Development Methodology.</u> Addis Ababa: AAU Printing Press.

Beebe, A. and Masterson, T. (1986). <u>Communicating Small Groups: Principles and Practices.</u> London: Foresman and Company.

Bejarano, Y. (1987). "A Cooperative Small-group Methodology in the Language Classroom." <u>TESOL Quarterly</u>, Vol. 21. No. 3 <<u>http://www.jstor.org</u>>

Berhanu Bogale (2000). "Verbal Participation in Group Work: A Case Study of First Year Students at Addis Ababa University." Addis Ababa University, Graduate Programe PhD Thesis (unpublished).

Billson, M.J. (1986). "The College Classroom as a small Group: some Implication for Teaching and Learning." <u>Teaching Sociology,</u> Vol. 14. No.3 pp.143-151 <<u>http://www.jstor.org</u>>

Birhanu G/Michael (2000) "A Study of the Paractice of Co-operative Learning in Grade 11: Group Work Organization in Focus." Addis Ababa University, Graduate Programe MA Thesis (unpublished).

Bligh, A.D. et al.(1980). Methods and Techniques in Post secondary Education. Paris: Unesco.

Blumenfeld, et. al. (1996) "Learning with Peers: From Small Group Cooperation to Collborative Communities." Educational researcher. Vol. 25, No.8, pp.37-40. <http://www.jstor.org>

Bostes, M. (1994) "Reflection in Teaching." In Kiani, E. (Eds). Journal for Educational Reform in Namibia. Vol. 1, No.1, PP. 23-24.

Bruke, K. (2000). What to Do with the Kid who ... Developing, Self-Discipline, and Responsibility in the Classromm. 2nd ed. Illinois: Skylight Training and Publishing Inc.

Brumfit, C. (1984). Communicative Methodology in Language Teaching: The Roles of Fluency and Accuracy. Cambridge: Cambridge University Press.

Burden, R. P. (2003). Classroom Management: Creating A Successful Learning Community. 2nd ed. New York: John Wiley & Sons, Inc.

Campbell, L. et al (2004). Teaching and Learning Through Multiple Intelligences. Boston: Pearson Education, Inc.

Chilver, P. (1990) "The Role of the Teacher in Small Group Learning." In Brubecher, M. et al (Eds) Perspective on Small Group Learning (pp 141-153). Ontario: Rubicon Publishing Inc.

Cowie, H. et al (1994). Cooperation in the Multi- Ethinic Classroom: the Impact of Co-operative Group Work on Social Relationships in Middle Schools. London: David Fulton Publishers.

Cuthbert, P. (1994). "Self-development Groups on a Diploma in Management Studies Course" In Thorley, L. and Gregory, R. (EdS). Using Groups-Based Learning in Higher Education. (pp 89-99) London: Kogan Page Limited.

Davis, G.B. (1993). "Collaborative Learning: Group Work and study Teams" <http://www. Teaching. Berkelay. edu/ bgd/ collaborative/ html>

Dolmans, M. et al. (2003) "Development of an Instrument to Evaluate the Effectiveness of Teachers in guiding Small Groups" Higher Education. Vol. 46, No. 4., pp 431-446 <http://www. jstor.org>

Exley, K. and Dennick, R.(2004) Small Group Teaching. London: Routledge Falmer.

Garfield, J. (1993). "Teaching Statistics Using Small Group Cooperative Learning." Journal of Statistics Education V.1 n.1 <http://www. amstat.org/ puplication/ jse/ vini/ Garfield. Html.>

Gauteng Department of Education (1999) "Facilitation Skills and Participative Teaching and Learning: Participants' Manual." Johannesburg: GED.

Girma Gezahegn (2003) "In-Service English Language Teachers Perceptions of the Factors that Influence the Implementation of Group Work Activities in ELT Classes." The Ethiopian Journal of Education, Vol. XXIII No. 2 pp103-126.

Graan, M. (1999). "Learner- Centered education: Equal to Group Work? Findings from Namibian Classrooms." In Teresa, M. and Mariana, V.G. (Eds). Education Reform and Innovation in Namibia: How Best Can Changes in Classroom Practice be Implemented and Supported? (pp 52-60). Cape Town: CTP Book Printers Ltd.

Gregory, R. and Torley, L. (1994). "Present Challenges" In Thorley, L. and Gregory, R. (Eds). Using Group-based Learning in Higher Education. (pp 179-186) London: Kogan page Limited.

Harmer, J. (2006). The Practice of English Language Teaching 3rd ed. Edinburg: Pearson Education Limited.

Hokugen, L. (1998) "Suggestions for Leading Small- Group Discussions. <http://www.celt.iastate.edu/teaching/smallgroup.html>

Jacobs, G. (1988) "Cooperative goal structure: a Way to Improve Group Activities." ELT Journal. Vol.42, No.2, PP.97-101.

Jaques, D. (1989). "Small Group Teaching." <http://www.vobedu/ Uasom,ume/edm/small.htm>

Johnson, W.D. and Johnson, T.R. (1990) "Cooperative Classrooms." In Brubacher, et al (Eds). Perspective on Small Group Learning. (PP. 119-129). Ontario Rubicon Publishing Inc.

Jones, V. and Jones, L. (2004). Comprehensive Classroom Management: Creating Communities of Support and Solving Problems. 7th ed. Boston: Pearson Education, Inc.

Kain, L. D. (2003). Problem-Based Learning For Teachers, Grades K-8. Boston: Pearson Education, Inc.

Larrivee, B. (2005) Authentic Classroom Management: Creating a Learning Community and Building Reflective Practice. 2nd eds. Boston: Pearson Education, Inc.

Livingstone, G. et al. (2002) "The Quality and Effectiveness of Teacher Education in Ethiopia: A Report of the Study Findings with Recommendations for Action." Ministry of Education (unpublished).

Long, M.H. and Porter, P.A. (1985) "Group Work, Inter Language Talk, and Second Language Acquisition." TESOL Quarterly. Vol. 19, No.2 pp. 207-212.

Lou, V. et al (1996). "Within- Class Grouping: A Meta Analysis" In Frank, B. et al Eds Review of Educational Research. Vol. 66, No. 4, (pp 423-458).

Luft, J. (1984). Group Processes: An Introduction To Group Dynamics. 3rd eds. San Francisco: Mayfield Publishing Company.

Mckeachie J.W. (1998)"Active Learning" <http://www.corses, science.fau.edu./ rjordam/ activelearning.htm>

Matiru, B. et al (Eds) (1995). Teach Your Best. Bonn: Germen Foundation for International Development.

Mills, B (1998) "Managing and Motivating!-Distance Learning Group Activities." <http://www:tltgroup.org/gilbert/millis.htm>

Ministry of Education (2003) "A National Curriculum Guideline for Pre-Service Teacher Education Programmes". Addis Ababa (unpublished)

Nunan, D. (1992). Collaborative Language Learning and Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Petty, G. (2004) Teaching Today. 3rd eds. London: Nelson Thornes Ltd.

Putnam, J. (1997). Cooperative Learning In Diverse Classroom. New Jersey: Prentice- Hall, Inc.

Richards, C.J. and Rodgers, S. T. (2001). Approaches and Methods in Language Teaching. 2nd ed. Cambridge: Cambridge University Press.

Rose, S(2005) "The Art of Discussion Leadership: Managing the Quiet or Dominant Participant." <http://www.ddw.org/user-assets/ documents/ PDF/ session handouts /2005/ 051805/>

"SEAL Classroom Observation Checklist." <http://www.edu.dudley. gov.uk>

Sharan, S. (1990). "The Group Investigation Approach to Cooperative Learning: Theoretical Foundations." In Brubacher, et al (Eds). Perspective on Small Group Learning. (pp.29- 39) Ontario: Rubicon Publishing Inc.

Stone, B. (1994) "The Academic Management of Group Projects." In Thorey, L. and Gregory, R. (Eds). Using Group- based Learning In Higher Education. (pp.59-63). London: Kogan Page Limited.

Thorley, L. and Gregory, R. (eds) (1994) Using Group Based Learning In Higher Educaiton. Lon: Kogan Page Liimted.

Tribe, R.M.D. (1994). "An Overview from Higher Educaiton." In Thorley, L. and Gregory, R. (Eds). Using Group- Based Learning in Higher Education. (pp 25-31) London: Kongan page Limited.

UNICEF (2000) "Managing the Active Classroom." <http://www.unicef.org/ teachers/ teachers/Manage.htm>

Ur, P. (1996). A course in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Westberg, J. and Jason, H. (1996). Fostering Learning in Small Groups: A Practical Guide. New York: Springer Publishing Company, Inc.

Wragg, C.E. (1999). An Introduction to Classroom Observation. 2nd ed. New York: Routledge Falmer.

Yunfeng, Z. (n.d.) "Task Type and Teacher's Role: Two Important Factors In Effective Group Learning." <http://ct-net.net/tc-sample-6-3>

Zeleke Theshome (2006) "A Study on How Teachers of EFL Manage Group Work: Grade 10 in focus." Addis Ababa University, Graduate program MA Thesis (unpublished).

# አባሪዎች

*FIGURE 3.9*
*Cooperative Lesson Plan Form*

**Cooperative Lesson Plan Form**

**Grade Level:** ______________ **Subject Area:** ______________

**Step 1. Select a lesson** ______________

**Step 2. Make decisions**

a. Group size: ______________

b. Assignment to groups: ______________

c. Room arrangement: ______________

d. Materials needed for each group: ______________

e. Assigning roles: ______________

Step 3. Set the lesson. State, in language your students understand:

a. Task: ______________

b. Positive interdependence: ______________

c. Individual accountability: ______________

d. Criteria for success: ______________

e. Specific behaviors expected: ______________

Adapted from Johnson, Johnson, & Holubec (1990)

*FIGURE 3.9*
*continued*

Step 4. Monitor and process

a. Evidence of expected behaviors (appropriate actions): ______________

b. Observation form: ______________
Observer(s): ______________

c. Plans for processing (feedback): ______________

Step 5. Evaluate outcomes

a. Task achievement: ______________

b. Group functioning: ______________

c. Notes on individuals: ______________

d. Suggestions for next time: ______________

Step 6. Determine needed adaptations for students with special needs

______________



*Figure 5.24 Students participating in a lively small group discussion*






Figure 4.3 Working in groups – is it a positive experience?

አባሪ 3


Possible Room Arrangement
Teacher Desk
Blackboard
Screen
Supplies


Blackboard
Teacher

## የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህራንን ለመጠየቅ የተዘጋጁ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

**ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ መረጃ**

1. የትምህርት ደረጃዎን ቢገልፁልኝ?
2. ለምን ያህል ጊዜ በምህርነት አገልግለዋል?
3. የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራምን ተከታትለዋል?

**ክፍል ሁለት፡- የቡድን ማስተማርን የሚመለከቱ ጥያቄዎች**

1. በእርስዎ አስተያየት ተማሪዎችን በቡድን እንዲማሩ የማድረግ ዓላማ ምንድ ነው ይላሉ? ለተማሪዎቹ ምን ጠቀሜታ አለው ይላሉ? ( በተለይ ከቋንቋ ትምህርት አንፃር)
2. ለተማሪዎች የቡድን ስራዎችን ለመስጠት ሲያስቡ ምን አይነት ቅድመ ዝግጅት ያደርጋሉ?
3. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድን የሚሰሯቸው የቡድን ስራዎች ምን ምን ናቸው? ከክፍል ውጭ የሚሰሯቸው የቡድን ስራዎችስ ምን አይነት ናቸው?
4. በክፍል ውስጥ ለሚሰሩ የቡድን ስራዎች ቡድኖች የሚራጁት እንዴት ነው? ( የአባላተ ብዛት፣ አመዳደብ ወዘተ).
5. ከክፍል ውጭ ለሚሰሩ የቡድን ስራዎች ቡድኖች የሚራጁት እንዴት ነው? ( የአባላት ብዛት፣ አመዳደብ፣ ማንነው ምርጫውን የሚያካሂደው ለምንስ ያህል ጊዜ በአንድ ቡድን አባልነት አብረው ይቆያሉ?)
6. በእርስዎ ግምት ተማሪዎቹ ስለ ቡድን መማር አላማና አስራር በቂ ግንዛቤ አላቸው ይላሉ? እርሰዎስ ለተማሪዎቹ የቡድን መማር ዓላማንና አሰራርን የሚያስተዋውቁባቸው መንገዶች አሉ?
7. ተማሪዎች በንዑስ ቡድን በሚሰሩበት ወቅት ማድረግ ስላለባቸውና ማድረግ ስለሌለባቸው ነገሮች የሚገልፅ መመሪያ ወይም ደንብ አለ?
8. በክፍል ውስጥ የተማሪዎች የቡድን አቀማመጥ ምን ይመስላል?
9. በተለይ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ሁሉም የቡድኑ አባላት እኩል ተሳትፎን የሚያደርጉ ይመስለዎታል? ሁሉም በስራው ላይ መሳተፋቸውን እንዴት ነው የሚከታተሉት?

10. ተማሪዎች የቡድን ስራዎችን ለመስራያ ወይም ስራዎቹን በክፍል ውስጥ ለማቅረቢያ፣ የሚረዱ የጽህፈት መሳሪያዎችን የሚያገኙት ከየት ነው?
11. ለተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የቡድን ስራዎችን ሲሰጡ እርስዎ በክፍለ ጊዜው፣ ከመጀመሪያ እስከ ማብቂያው ባለው ሂደት ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑ ቢዘረዝሩልኝ?
12. በቡድን አባላት መካከል አለመግባባቶች የሚፈጠሩበት ሁኔታ አለ? አለመግባባት የሚፈጠር ከሆነ ላለመግባባቱ ምክንያት ናቸው የሚሏቸውን፣ እንዲሁም መፍትሄ ናቸው የሚሏቸውን ሃሳቦች ቢገልፁልኝ?
13. የቡድን ስራዎች የሚገመገሙት ( ውጤት የሚሰጣቸው) እንዴት ነው?
14. ተማሪዎች የቡድን ስራዎቻቸውን በመለዋወጥ የቢጤ እርማት የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ? የራሳቸውን የቡድን መማር ሂደት እንዲፈትሹ የሚደረግበት ሁኔታስ አለ?
15. የቡድን መማር ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ መሆኑን አለመሆኑን የሚገመግሙበት ስልት ካለ ቢያስረዱኝ
16. በመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ፣ የቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት ያጋጠመዎት ችግሮች ካሉ ዘርዘር አድርገው ቢገልፁልኝ?

# አባሪ 5

**በሆሳህና መም/ት/ኮሌጅ የመሠረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህር 1፣ ለቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች**

1. አ፡ በቅድሚያ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ስላደረጉልኝ፣ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ለመነሻ እንዲሆነን የትምህርት ደረጃዎን ቢገልፁልኝ?
   መ.1፡ የትምህርት ደረጃዬ -ኧ- ባችለር ኦፍ ኢዱኬሽን በአማርኛ
2. አ፡ እሺ. ለምን ያህል ጊዜ በመምህርነት አገልግለዋል፡፡
   መ1. ፡ እኔ ከ92 ዓ.ም ጀምሮ ነው መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም እንዲሁም፣ በ98 እዚህ ኮሌጅ ውስጥ ከ98 ዓ.ም ጀምሮ እየሰራሁ ነው ያለሁት፡፡ወደ 9 ዓመት ሆኖኛል በመምህርነት ሙያ፡፡
3. አ፡ በኮሌጅ የሚሰጠውን የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም ተከታትለዋል?
   መ1፡ አዎን ተከታትያለሁ፡፡
4. አ፡ እስቲ ስለ ቡድን ማስተማር አተገባበር አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅ፡፡ ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲማሩ ያደርጋሉ?
   መ1፡ ሁልጊዜም ባይሆን አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ፡፡
5. አ፡ -ኧ- ለምሳሌ ምንያህል ጊዜ አዘውትረው ያስተምሩበታል?
   መ1፡ የቡድን ስራ ለመጠቀም የማስተምረው ርዕስ ጉዳዮች ይወስናሉ፡፡ ርዕስ ጉዳዩ ለቡድን ስራ የሚጋብዝ ከሆነ የቡድን ስራን ለመጠቀም ወስኜ ያንን ክፍል ውስጥ ተግባራዊ አደርጋለሁ ፡፡ ከዚህ ውጭ ግን ሌሎች የማስተማሪያ ስልቶችን ነው የምጠቀመው ክፍል ውስጥ፡፡
6. አ፡ እሺ. በርሶ አስተያየት ተማሪዎች በቡድን እንዲማሩ የማድግ ዓላማ ምንድነው?
   መ1፡ እኔ እንግዲህ ብዙ ጊዜ እኔ እንደራሴ እንደ ሌሎቹ መምህራን ሳይሆን እንደኔ ግላዊ አመለካከቴ፣ የቡድን ስራ ነው ብዬ የምሰጣቸው -ኧ- በአብዛኛው ርዕስ ጉዳዮቹ እራሳቸው ተማሪዎቹ ከዚህ ቀደም -ኧ- የተወሰነ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ዕውቀት አላቸው ብዬ ሳስብ፣-ኧ- ሌላው የተወሰኑም ቢሆኑ እዚያ ቡድን በመሰረቱበት ጊዜ የተወሰኑ ተማሪዎችን እውቀት አላቸው፣ በዚያ ዙሪያ ትንሽ ኤክስፒሪያንስ ሼር፣ ልምዳቸውን ሊያካፍሉ ይችላሉ ብዬ ሳስብ ነው ወደ ቡድን ስራ የምገባው፡፡ ግን በአጠቃላይ ርዕሰ ጉዳዩ፣ የሚነሳው ርዕስ ጉዳይ በጣም አዲስነት ካለው በራሴ በኩል በሌክቸር ሜተድ በመጠቀም ነው ለማስተማር ጥረት የማደርገው፡፡
7. አ፡ እሺ. ለተማሪዎቹ የሚኖረው ጠቀሜታ፣ የቡድን ስራ ለተማሪዎቹ ምን አይነት ጠቀሜታ ያስገኝላቸዋል ይላሉ?
   መ1፡ እኔ እንግዲህ እስከዛሬ ካለኝ ልምድ፣ የቡድን ስራ ብዙ ጥቅሞች ይሰጣል በኔ በኩል እንዳየሁት፡፡ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ -ኧ-የመናገር ነገር -ኧ- የማፈር ነገር ያላቸው ተማሪዎች አሉ፡፡ ሲናገሩ እና ይኼ የእፍረት ነገር ለምሳሌ መምህሩ ሲጠይቅ ለመመለስ ወይም ሀሳባቸውን ለመግለፅ የሚያፍሩ፣ የሚፈሩ ተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ከራሳቸው ጓደኞች ጋር ሲሆኑ ሃሳባቸውን፣ ያው የሚገባውን ሃሳብ አውጥተው ተነጋግረው፣ ያው ጥሩ የሆነውን ነገር ደግሞ በቡድኑ አማካይነት በክፍል ውስጥ የሚቀርብበት ጊዜም አለ፡፡ ከዚህ ባለፈ ተማሪዎቹ ራሳቸው እዚያው የመማር ተግባር እርስ በራሳቸው ማካሄዳቸው፣ ተማሪዎች ልምዳቸውን (ኤክስፒሪያንሳቸውን) ሲያካፍሉ -ኧ-ጥሩ ነገር ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ወይም ጓደኞቻቸው ከዚህ ባለፈ ይኼ በቡድን ሰርተው ዕበረታ ያካሂዳሉ፤ የሰሩትን ሃሳብ፡፡ ስለዚህ ክፍል ውስጥ በሚቀርብበት ጊዜ፣ ይኼ ፕሬዘንት የሚደረገው ነገር የቋንቋ ችሎታቸውን ያዳብርላቸዋል፣ ፕላስ ከተለያዩ ቡድኖች የሚመጣው አይዲያ ብዙ ሀሳቦችን የያዘ ነገር፣ አዳዲስ ነገሮች ሊመጡበት የሚችሉበት አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ስለዚህ ነው እንግዲህ፣ የሚሰጠው ጥቅም እነዚህን የመሰለ ነው በኔ በኩል፡፡
8. አ፡ አዎ ምናልባት ከቋንቋ አንፃር ያሉት አሁን ጀመር አድርገውታል፣ ከቋንቋ አንፃር ምን ምን ጥቅሞች አሉት?በቡድን መስራት ለቋንቋ ትምህርት?
   መ1፡ እኔ በቡድን መስራት ለቋንቋ ትምህርት ብዙ ጠቀሜታ ይሰጣል ብዬ ነው የማስበው፡፡ይኼ የመናገር ጉዳይ አለ፣ ተማሪዎቹ ቅድም እንዳልኩት በቡድን በሚሆኑበት ጊዜ ለንግግር፣ ለመናገር ዕድሉ ይሰፋል፡፡ መምህሩ ሚናገርበት ጊዜ ያው የማዳመጡ ነገር ነው በአብዛኛው የሚኖረው፡፡ ነገር ግን በቡድን ሲሆኑ አንደኛው ሲናገር ሌላኛው ያዳምጣል፡፡ ሌላኛውም ተራው ሲደርስ ይናገራል፡፡ ስለዚህ ይኼ የንግግር ክሂላቸውንም በዚያው እግረ መንገዳቸውን እንዲያሻሽሉ አስተዋፅኦ ያደርጋል ብዬ ነው የማስበው እንደ እኔ፡፡

9. አ፡ የቡድን ማስተማር ዘዴን በተመለከተ የወሰዷቸው ስልጠናዎች አሉ?

መ1፡ እኔ ከዚህ በፊትም በምማረው ትምህርት በእርግጥ የመጀመሪያ ዲግሪዬን በምሰራበት ወቅት፣ ከዚህ ውጭ ዲፕሎማዬንም ስርቻለሁ:: እዚያ ላይ የተማርኳቸው ነገሮች አሉ:: መምህራን ስልጠና ላይ በተለይ የቴሶ ፕሮግራም ከመጣም ወዲህ፣ ከዚያም በፊት የቡድን ስራዎችን በተመለከተ አንዳንድ ስልጠናዎችን ወስጃለሁ::

10. አ፡ እሺ. የ ሀየር ዲፕሎማ ፕሮግራም ወስጃለ ብለዋል:: ከዚያ አንፃር ለቡድን ስራ ወይም የቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር የረዳዎት ነገር ምናልት ካለ?

መ1፡ ይኼን ከፍተኛ ዲፕሎማ መማር የቡድን ስራዎችን እኔ አሁን ለመሳሌ፣ ከዚህ በፊት አውቅ የነበረው ሀየር ዲፕሎማ ከመማሬ በፊት አውቅ የነበረው፣ የቡድን ስራዎች ተማሪ፣ የተወሰነ ተማሪ አንድ ላይ ማድረግ ከዚያ በኋላ የተዋያዩትን ሀሳብ በህብረት እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ እነዚህን ነበር የማውቀው::ነገር ግን፣ለምሳሌ በአንድ ቡድን የሚሰሩትን ይኼ ክሮስ አ ቨር የሚባል ሜተድ አለ::ከአንደኛው ቡድን ወደ ሌላኛው ቡድን ሄደው የሰሩትን ስራ ልምድ መለዋወጥ መቻል:: በተለያዩ ቡድኖች እየሄዱ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ የማድረግ ነገር አለ:: ብዙ የቡድን ስራ ሜተዶች አሉ:: ይኼ በክብ ሰርቶ መሀል ላይ የሆነ ሆት የሆነ ኢሹ ላይ መወያየት መከራከር ነገር አለ ::ብዙ አይነት የቡድን ስራዎችን አይነት ከዚያ ወዲህ ተምሬያለሁ::

11. አ፡ ለተማሪዎች የቡድን ስራዎችን ለመስጠት ሲያስቡ ምን አይነት ቅድመ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ?

መ1፡ ሁልጊዜ አይደለም፤ በእርግጥ እኔ ገብቼም ቅድመ ዝግጅት ሳላደርግም የምሰጥበት ጊዜ አለ:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ምን አደርጋለሁ፣ የዕለቱን ትምህርት ከጨረስኩ በኋላ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ እስቲ መዕሐፎችን አንብባችሁ፣ እንደዚህ ተዘጋጅታችሁ የምታዩትን ነገር ሁሉ፣ የምትጠይቁት ሰው ካለም ጠይቃችሁ ኑ ብዬ እንዲሁ በደፈናው ሰጥቻቸው አሔዳለሁ:: ስመለስ ዕርስ ጉዳዩን አዕፍና እስኪ ይህንን ሀሳብ ቡድኖችን ሰርታችሁ ተወያዩባቸው የሚል ነገር ደረጃ ላይ የምመጣበት ጊዜ አለ::ግን ይኼንን ሁልጊዜ አላደርገውም::

12. አ፡ የትምህርት ዝግጅትዎ፣ ለምሳሌ በቡድን ለማስተማር ሲዘጋጁ ማለትም በሚቀጥለው ጊዜ የቡድን ስራን እሰራለሁ ብለው ሲነሱ፣የሚዘጋጁባቸው ነገሮች አሉ? ማለትም የትምህርት ዝግጅትዎ ምን ይመስላል?

መ1፡ እኬ ያንን በተመለከተ አንዳንድ ጊዜ አልፎ አልፎ ነው የማደርገው፣ አንዳንድ ጊዜ ምንድድነው የማደርገው በቡድን የሚሰሯቸውን ጥያቄዎች አዘጋጃለሁ ዕሬ:: ከዚያ በኋላ ደግሞ ክፍል ውስጥ ለየቡድኑ የምሰጥበት ሁኔታ አለ:: አልፎ አልፎ ነው ሁልጊዜ አይደልም:: ከዚያ ውጭ ግን እኔ እራሴ ያዘጋጀሁትን የራሴን የትምህርት ዝግጅት ይገቨ ገባና ለተማሪዎቹ እሰጣቸዋለሁ:: ከዚያ በኋላ ሁሉንም ስራ ሳይሆን፣ ለየቡድኑ የምሰጣቸውን ስራዎች ከፋፍዬ እሰጣቸዋለሁ::

13. አ፡ -ኧ- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰሯቸው የቡድን ስራዎች ምን ምን አይነት ናቸው?

መ1፡ እ በአብዛኛው የሚያደርጉት የመወያየት ጉዳይ ነው:: ርዕስ ጉዳዩ ይሰጣዋችል:: ያንን በተመለከተ ሲወያዩ እና እኔ የሚጠይቁት ሀሳብ ካለ፣እዚያ ጋ ሄጄ በዚህ መንገድ በዚህ መንገድ ብትወያዩ ይኼንን ብታዩስ? እያልኩ እስተያየት እሰጣቸዋለሁ:: የሚነግሩኝ ነገር ይኖራል:: ይኼስ እንዴት ተረሳ?ይኼንንስ ማንሳት አትችሉም ነበር ወይ? እያልኩኝ ሌላ ሌላ መንገድ እየከፈትኩ እሰጣቸዋለሁ::በዚያ መንገድ እየገቡ ይወያያሉ:: አብዛኛው ውይይት ነው የሚሰሩት::

14. አ፡ እሺ ከክፍል ውጭ የሚሰሯቸው የቡድን ስራዎችስ አሉ?

መ1፡ ከክፍል ው... ጪ፣ እኔ በዚህ ሁለት ዓመት ውስጥ እንግዲህ ከክፍል ውጪ የሚሰሩትን፣ በእርግጥ እሰጣቸዋለሁ የቡድን ስራዎችን::እነዚያን የሠጠኋቸውን የቡድን ሥራዎች ወደ ውጤት አለውጣቸውም እንጂ::

15. አ፡ ምናልበት ይህንን ጉዳይ ወደ በኋላ እንመጣበታለን:: ለአሁኑ አለ ወይ የቡድን ስራዎቹ?

መ1፡ አዎ አለ አለ::

16. አ፡ ምን አይነት ስራ ለምሳሌ?

መ1፡ -ኧ- ለምሳሌ አሁን እኔ ባለፈው ሲሚስተር ላይ የልቦለድ ግምገማ ስራ ሰጥቻቸዋለሁ::ረጅም ልቦለድ ከአላባዊያንና ከቴክኒኮች አንፃር ገምግመው እንዲያቀርቡ ያደረግሁበት ሁኔታ አለ:: በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ያደረኩበት ሁኔታ አለ::

17. አ፡ እሺ በክፍል ውስጥ ለሚሰሩት ስራዎች ቡድኖች የሚራደራጁት እንዴት ነው? የሚደራጁት ስል፣ የአበላት ብዛታቸውን በአንድ ንኡስ ቡድን ውስጥ? አመራረጣቸው እንዴት እንዴት እንደሆነ፣ እና አቀማመጣቸው?

መ1: በእርግጥ የተማሪዎች ቁጥር ወሳኝ፤ነው በአንድ ክፍል የሚኖረው። እኔ በአብዛኛው የምጠቀመው ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርስ አባል ያለው ቡድን መመስረትን ነው። በአብዛኛው የምጠቀመው። እና የአባላቱን ብዛት እኔ በዚያ መልኩ ነው እያደረኩ ያለሁት። ከዚያ ውጭ ግን፣የቡድን ስራዎች በሚሰሩበትት ጊዜ፣ተማሪዎችን በአብዛኛው የመለዋወጥ ነገር እጠቀማለሁ። አንድ አካባቢ ቁጭ ያሉትን ተማሪዎች፣ ለምሳሌ በመጀመሪያዎቹ አካባቢ ላይ እዚያው ባሉበት አካባቢ እንዲሰሩ አደርጋለሁ። ከዚያ ቀስ በቀስ ግን የመለወጥ ነገር እጠቀማለሁ።-እ- ግን አብዛኞቹ ተማሪዎች ለምሳሌ -እ-ካላቸው እንትን አንፃር አንድንዴ አስፈላጊ ሆኖ ይኼ ተማሪዎቹ ከሚኖሩበት አካባቢዎች ጋር እንደዚህ፣ ለመስራት ይርቀኛል እንደዚህ ምናምን የሚሉ አሉ። በመስራት ሂደት ውስጥ። ሶ በዚያን ጊዜ በአካባቢ መቀራረብ የማድረግበት ጊዜ አለ። -እ- ክፍል ውስጥ የማውቃቸው ጥሩ ጥሩ ልጆች አሉ። እነዚያን ተማሪዎች አንዳንዴ ወደየቡድኑ የምበትንባቸው ጊዜያት አሉ እንደ ሁኔታው።

18. አ፡ ከትምህርት ችሎታቸው አንፃር ነው?

መ1: አዎ ከችሎታቸው አንፃር፤ እኔም ስለማውቃቸው ውጤታቸውን የማውቃቸው ልጆች አሉ ። እነዚህን ወደየቡድኑ ዲስትሪቢዩት አርድጌ ፤በውጤት ብቻም ሳይሆን ክፍል ውስጥ ሁልጊዜ ፕሬዘንት ሲያደርጉ የማያቸውን ልጆች አሉ፡እነዚህ ልጆች ለሌሎቹ ድልድል እንዲኖር ወደ ተለያዩ ቡድኖች እንዲዳረሱ የማደርግበት ሁኔታ አለ። የተለያዩ ነገሮች ነው የምጠቀመው።

19. አ፡ እሺ አቀማመጣቸውስ እንዴት ነው?

መ1: በአብዛኛው እኔ ክብ ሆነው ነው፣ ከበው እንዲቀመጡ ነው የማደርገው -እ-በዚህ መልኩ ነው የምጠቀመው።

20. አ፡ እሺ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። ከክፍል ውጭ ለሚሰሩ የቡድን ስራዎች ቡድኖች በዚሁ መልኩ ነው የሚያደራጁት?

መ1: ከክፍል ውጭ እንዲያውም ቀድም ባልኩት መልኩ ነው ።ምንድነው የመቀራረብ እከሌ ከእከሌ ይሁን፣ እኔ ይርቅብኛል እዚህ መጥቼ ለመስራት፣ማታ ስንሰራ፣ የሚሉት ነገር አለ። እና ከዚህ አንፃር አንዳንዴ የምመድብበት አለ። አንዳንዴ ደግሞ ገፍቼ ሄጄ፣ ያንን ትቼ እንደፈለጋችሁ አድርጋችሁም ስሩ ግን በዚህ ID ነምበር መሰረት እኔ አደራጃለሁ፣ በዚህ ስሩ የምልበት አለ። ለዚህ መነሻዬ ምንድን ነው፣ እሮሮዎች ይመጣሉ አንዳንዴ።እኛ ላይ ነው ጫና እየበዛ ያለው፤ በዚህ ምክንያት ነው እኛ በውጤት የተጎዳነው የሚሉ ትንሽ የሚሞክሩ ተማሪዎች አሉ። ከነሱ የሚመጣ እሮሮ አለ። ስለዚህ፣ እንደዚህ አይነት ነገሮች ሲመጡ እንዳመጣጡ ለማስተንከል እሞክራለሁ።

21. አ፡ የአባላት አመራረጡስ በርሶዎ ነው የሚመረጠው? ወይስ በተማሪዎች?

መ1: ተማሪዎቹም የሚያነሱትን ነገር አንዳንዴ እቀበላለሁ። ይኼ የመቀራረቡን ቀድም ያልኩህን ጉዳይ ፤በአካባቢ የመቀራረብ ጉዳይ ማታ ስለምንሰራ እንደዚህ፣ ከዚህ አንፃር አንዳንዴ የማይሉቸው ጉዳይ አለ። ሁልጊዜ ግን አይደለም። አልፎ አልፎ ነው።

22. አ፡ በአንድ ቡድን ውስጥ በአባልነት የታቀፉ ተማሪዎች፣ በአንድ ቡድን አባልነት ለምን ያህል ጊዜ አብረው ይቆያሉ?

መ1: ብዙ ጊዜ ማድረግ አልወድም እኔ። ቢበዛ አንዴ ወይም ሁለት ጊዜ ባደርግ ነው እንጂ፣ ከዚያ በላይ አብረው እንዲሆኑ አልፈቅድላቸውም። ወዲያው እቀይራለሁ። በሚቀጥለው ስመጣ በዚህ መልኩ ሳይሆን በሌላ መልኩ እንዲሰሩ የማድግ ነገር አለ።

23. አ፡ ማለዋወጥ?

መ1: አዎ ማለዋወጥ

24. አ፡ -እ- አንድ የቡድን ስራ ለመስራት፣ የቡድን አባላቱ የየስራ ድርሻቸውን የሚከፋፈሉት እንዴት ነው?

መ1: ይህንን ምንድነው የማረገው፣ መጀመሪያ ኮርሱን ስጀምር የማስታውቀው ነገር አለ። የኮርሱን አላማ ማስተዋወቅ አለ። ይዘቱን ማስተዋወቅ አለ። ከዚያ በኋላ የመማር ማስተማሩ ስልት ምንድነው? የሚለው ላይ ምንድነው የማደርገው የቡድን ስራ እንዳለ አልፎ አልፎ የምንጠቀመው፣የቡድን ስራዎች አሉ የምንወያይባቸው፣ ስለዚህ በዚህ ጊዜ የቡድን ስራ ሲኖር የቡድን መሪ ይኖራል፤እዚያ ውስጥ የምትወያዩትን ሀሳብ የሚፅፍ ሰው ይኖራል፤ የሚል ነገር እንግራቸዋለሁ።ስለዚህ የቡድን ስራ ሲባል መረበሽ ሳይሆን፣ ስርዓት

ባለው መልኩ አንድ የምትወያዩትን ነገር ዕድ የሚይዝላችሁና የሚመራችሁ ሰው ያስፈልጋል፤ መሪ በሌለበት ቦታ ዝም ብሎ መንጫጫት ስለሚሆን በዚህ መልኩ ነው የምታደርጉት ብዬ መጀመሪያ ላይ እነግራቸዋለሁ::ከዚያ ውጭ ግን አንዳንዴ አዲስ የሚመጡ ተማሪዎች፣ ይኼ ግር የሚላቸው ጊዜ አለ:: እንደዚህ በዚህ መልኩ ነው የምታደርጉት ሲባሉ ካልተዋወቁ የሚቸግራቸው ጊዜ አለ:: ከዚያ ውጭ እየተከታተልኩ፣ የቡድን ሥራ በሚሰሩበት ጊዜ፣ ሁሉም ሲናገሩ ሳይ፣ማነው የሚመራችሁ? እዚህ ውስጥ ማነው የሚመራው? ብዬ ስል፣ ማንም የለም፤ ዝም ብለን ነው የምንወያየው የሚሉም አሉ:: የዚያኑ አይ አንድ የሚመራችሁ ሰው አሳይን አድርጉ:: ሌላ ደግሞ የምትወያዩትን ሀሳብ ጠቅልሎ የሚይዝላችሁ ፀሐፊም ካለ አሳይን አድርጉ:: በዚህ መሠረት ብታደርጉ ማስታወሻ የሚይዝላችሁ ሰው ቢኖር ጥሩ ነው፤ የሚል ነገር አስተያየት እሰጣቸዋለሁ:: በዚያ መሠረት ነው የሚያደርጉት::

25. አ: ተማሪዎቹ በሙሉ ስለ ቡድን መማር አላማና አሰራር በቂ ግንዛቤ አላቸው ይላሉ?

መ1: ያ ነው ትልቁ ችግር:: እኔ ብዙ ጊዜ በውስጤ የሚሰማኝ ነገር አለ:: እውነቱን ለመናገር፣-ኧ- የቡድን ስራ ሲባል መምህሩን እንዲያው በዚያ ነገር ላይ በቂ የሆነ ነገር ሳይኖረን ቀርቶ እነሱ በዚያ መልኩ ጊዜውን እንዲያሳልፉ አሁን -ኧ-አድርገው የሚያስቡ አሉ:: እና ትምህርት በቀልድ እያለፈ እንደሆነም የሚያስቡም አሉ::እና በአጠቃላይ በቡድን ስራ ላይ ያላቸውን አመለካከት እንዲያው ተማሪው ቢሆንለት የሚመርጠው ምንድነው፣ ሁል ጊዜ መምህሩ ገብቶ ብቻ የሆነ ነገር እንዲናገር እና ኖት እንዲሰጣቸው ከዚህ ጋር ብቻ ነው ያላቸው ፍላጎት:: እንጂ ይኼ በቡድን ተወያይቶ ሀሳብ ማቅረብ እ... የሚለው ነገር ላይ ብዙ ፍላጎቱ የላቸውም:: እንደውም በጫና የሚካሄድ ነው የሚመስለኝ አንዳንዴ:: የቡድን ሥራ ላይ እንደዚያ ነው እኔ ግን አሁን ርዕሰ ጉዳዩ ስለሚገፋፋኝ ነው ወደዚያ የምሄደው እንጂ ፣እኔም ከዚያ የተነሳ ተማሪዎቹ ከሚሰጡኝ ፊድባክ የተነሳ፣ከማየው ስሜት የተነሳ፣ በአብዛኛው እንደዚያው ገብቼ የማስተማሩን ነገር እኔም አሁን እየመረጥኩ የመጣሁበት ሁኔታ አለ:: እና ተማሪዎቹ ለቡድን ስራ ያላቸው ባጠቃላይ ፍላጎት ጥሩ አይደለም:: እንዲያውም የቡድን ስራ ሰርተው ካቀረቡ በኋላ የሚሰጣቸው ፊድባክ አለ:: በሰሩት ስራ ላይ አስተያየት እሰጣቸዋለሁ:: መሆን ያለበት በዚህ መልኩ ነበር:: እያልኩ ስትሄድ እንደ ማስተማር ነው እኔ አሁን ለራሴ የምቆጥረው:: እነሱ ግን ያንን ነገር እንደዋዛ ነው የሚያልፉት ::ስ መጨረሻ ላይ ምንድነው የሚጠብቁት ከኔ፣እንዳስተምራቸው ነው ያን ነገር እንደ አዲስ እንዳስተምራቸው ይጠብቃሉ:: ስ ይኼም እራሱ እንደ አንድ ችግር እኔ ያየሁበት ሁኔታ አለ::

26. አ: የቡድን ስራ ዓላማውንና አሰራሩን ለተማሪዎቹ ለማስተዋወቅ በርሶ በኩል ያደርጉት ጥረት ካለ?

መ1: እኔ እንዲያውም መጀመሪያ ቀደም ኮርስ በምንገልፅበት ጊዜ የምጠቀመው የመማር ማስተማር ዘዴ ላይ ያልኩት መማር በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚሆን ነገር አይደለም፤ መማር በሁሉም አቅጣጫ የሚሆን ነገር ነው፤ ልምድን መለዋወጥ ነው፤ ዕውቀትን መለዋወጥ ነው፤ እናንተም ጋ የሆነ ነገር ይኖራል:: ከናንተ ጋ ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል ነገር ሊኖር ይችላል፤ከእኔ ወደ እናንተ ጋ የሚሄድ ነገር ሊኖር ይችላል:: ከናንተ ከጓደኞቻችሁ ወደ አንዳችሁ እንደዚህ የምትለዋወጧቸው ብዙ ነገሮች አሉ:: ስለዚህ መማርን ከአንድ አቅጣጫ አንጠብቅም እዚህ ክፍል ውስጥ:: ስለዚህ ይኼ የልምድ መለዋወጥ ነው::የምናውቀውን ነገር መለዋወጥ ነው:: ስለዚህ፣ በዚህ መልኩ ነው ውይይትም የሚሆነው በዚህ መልኩ ነው:: ሀሳብ የመቀያየር ነገር ነው:: እና መማር ማለት ደግሞ በዚህ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን፣በሁሉም አቅጣጫ ሊሆን የሚገባው ነገር ነው ብዬ እነግራቸዋለሁ ግን፣የመቀበሉ ነገር አሁንም... የመቀበሉ ነገር ነው ተማሪዎቹ ላይ እንደው ጊዜ ማሳለፊያ አድርጎ የመቁጠር ነገር... አዎ መምህሩን በእርግጥ እንደዚያ የሚያደርጉ መምህራን ሊኖሩ ይችላሉ ከዚያ ባለፈ ግን፣ጊዜ ማሳለፊያ አድርገው መምህሩን ይጠቀማሉ የሚል ነገር፣ወይም ርዕሰ ጉዳዩ የሚከብድ ሆኖ ያንን ለማሳለፍ ይጠቀማሉ የሚል ነገር እንደዚህ አይነት ነገሮች አሉ::

27. አ: ተማሪዎች በቡድን ስራ ወቅት ማድረግ ያለባቸውና ማድረግ የሌለባቸውን ነገሮች ለማስረዳት የተዘጋጀ መመሪያ አለ?

መ1: እንደዚያ አይነት ነገር የለም:: በመመሪያ ደረጃ እኔ እስካሁን ድረስ እንዲያው ከትምህርት ባገኘሁት፣ ስማር ካገኘሁት ነገር የቡድን ስራ በምትሰሩበት ጊዜ እንደዚህ እንደዚህ ማድረግ አለባችሁ የሚል ነገር፣ ያገኘሁት ከውጭ እንጂ፣ እንደዚህ በኮሌጅ የተቀመጠ መመሪያ ነገር የለም::

28. አ፡ እሺ. በተለይ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ሁሉም የቡድን አባላት እኩል ተሳትፎ የሚያደርጉ ይመስሎታል?

መ1: በዚህ ላይ ጥርጣሬ አለኝ፡፡ -ኧ- ምክንቱም አብዛኞቹ ስራዎች ተሰርተው ሲመጡ አያቸዋለሁ፡፡ያ የቡድን ስራ በእርግጥ የዚያ ቡድን ስራ ነው ወይ? ብዬ የማስብበት ጊዜ አለ፡፡ የልጆቹን የክፍል ውስጥ ስራቸውንና ሰርተው ያመጡትን ነገር ሳይ አንዳንዴ የሚለያዩበት ጊዜ አለ፡፡ በዚህ አኳያ የምጠራጠርበት ጊዜ አለ፡፡ ያንን ግን ለማረጋገጥ የምጠቀምባቸው ነገሮች አሉ፡፡ በተለይ በዕብረቃ ጊዜ ላይ ድንገት አንድ ሰው ሆን ብዬ አስነስቼ እስኪ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ አንተ አቅርብ፣ የምልበት ጊዜ አለ፡፡ በዚያ መንገድ ለማረጋገጥ የምሞክርበት ሁኔታ አለ፡፡ ግን የቡድን ስራ፣በተለይ ውጭ ተሰርቶ በሚመጣው ላይ ብዙ አመኔታ የለኝም እኔ፡፡

29. አ፡ ተማሪዎች የቡድን ስራዎችን ለመስራያ ወይም ስራዎቹን በክፍል ውስጥ ለማቅቢያ የሚረዱ የዕህፈት መሳሪያዎችን የሚያገኙት ከየት ነው?

መ1: -ኧ- ይሔንን እንኳን እንዲያው የለም ማለት ይቻላል በኔ በኩል፡፡ ተማሪዎች ይሄንን የሚጠቀሙበት አጋጣሚ የለም፡፡ ሁልጊዜ ይህንን እኔ ሳድርግብዬ ብጠይቅም፣ የሚያደርግ አካል ያለ አይመስለኝም፡፡ ግን ካላቸው ከራሳቸው እንዲጠቀሙ ነው የሚደረገው እንጂ በኮሌጁ በኩል ይህንን አስመልክቶ የሚሰጥ ነገር የለም፡፡ ግን አልፎ አልፎ ምናልባት በጣም በጣም በጣም እንዲያው የለም በሚባል መልኩ ለመጠቀም የሚቻል ነገር አለ፡፡ግን ያን እኔ ተጠቅመዋል ብዬ ለመናገር የሚያስችለኝ አይደለም፡፡

30. አ፡ ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰሩትን የቡድን ስራዎች ከሰጡ በኋላ፣ እርስዎ በክፍሉ ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ቢዘረዝሩልኝ?

መ1: የኔ ስራ ምንድነው ቀደም ሲል ገልጬው ነበር፡፡ ተማሪዎች በሚሰሩበት ጊዜ፣ግራ የሚገባቸው ሀሳብ ካለ አንዳንዴ ይህንን እንዴት አድርገን ነው የምንሰራው የሚሉት ነገር አለ፡፡ ወይም ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ የሚሄዱበት ጊዜ አለ፡፡ እነዚህ ነገሮች ዞር ዞር እያልኩኝ እያየሁ መንገድ ማሳየት ነው ይኼንን ተውት እላለሁ አንዳንዴ ወደ ስህተት ከሔዱ፡፡ ወይም እኔ ወደማልፈልገው አቅጣጫ ከሔዱ ወይም የትምህርቱ ዓላማ ወዳልሆነ ነገር የሚሔዱበት ጊዜ አለ፡፡ በዚህ ሳይሆን በዚህኛው እዩት እስቲ የሚል ነገር አስተያየት እሰጣቸዋለሁ፡፡ይኼ ማለት ደግሞ እንደዚህ ነው፣ ለምሳሌ መነሻ የሚሆን ነገር ራሱ የሚያጡበት ጊዜ አለ፡፡ መነሻ ሲያጡ ይህ ማለት እንደዚህ ማለት ነው፡፡ስለዚህ እዚህ ውስጥ እናንተ ማየት የምትችሉት ነገር ብዬ መንገድ አሳያቸዋለሁ፡፡ ከዚያ አንዣ ረዳቸዋለሁ ፡፡ከዚያ ውጭ ግን የሰሩትን ሀሳብ ጥቅል በሆነ መልኩ በአንድ ተወካይ አማካይነት ለክፍሉ እንዲያቀርቡ፣ ክፍሉ ደግሞ በቀረበው ነገር ላይ እንከኖች ወይም ደግሞ ገንቢ የሆነ አስተያየት እንዲያቀርብ የራሴን የበኩሌን አስተዋጽኦ አደርጋለሁ፡፡

31. አ፡ በቡድን አባላት መካከል አለመግባባቶች የሚፈጠሩባቸው ሁኔታዎች አሉ?

መ1: በጣም ይፈጠራሉ ማለት ይቻላል፡፡ በተለይ ውጭ በሚሰሩ ስራዎች ላይ አለመግባባቶች ይፈጠራሉ፡፡ አለመግባባቶች የሚፈጠሩት ከምን አንፃር ነው፣ እኔ ላይ ነው ጫናው ያለው እነሱ ለመስራት ፍቃደኛ አይደሉም፡፡ በተለይ ከሰዓት አኳያ አይመቸኝም የሚል ነገር አለ፡፡ ሶ ያለመጣጣም ነገር አለ፡፡ በዚህ ሰዓት ና ሲባል አልመጣም፤ ስለዚህ መስራት አልቻልንም የሚል ነገር ብዙ ጊዜ የሚቀርብበት ነገር አለ፡፡ ከዚህ ውጭ አንዳንድ ተማሪዎች ደግሞ (ፈገግታ) ቅድም የተባለውን በአንዱ ብቻ የማሰራት ነገር አለ፡፡ የሚሰራው አካል ደግሞ ብር አዋጡ የሚልበትም ጊዜ አለ፡፡ ብሩ ደግሞ በዛ ካለ እነዚያ ደግሞ እማይስማሙበት ጊዜ አለ፡፡

32. አ፡ ብሩ የሚዋጣው ለምንድን ነው?

መ1: ለማሰሪያ ተብሎ፣ለማቴሪያል መግዣ ምናምን ተብሎ ነው፡፡ ግን ለማሰሪያም ጭምር ነው፡፡ እገሌ ነው የሚሰራው ብር የሚባልበት ጊዜ አለ፡፡ ሶ ቅድም እጠረጥራለሁ ያልኩትም ከዚህ የተነሳ ነው፡፡ የቡድን ስራ ውጭ የሚሰራው በተለይ በትክክል ልጆቹ ተሳትፈው ሰርተውታል የሚልውን ነገር እጠረጥራለሁ የምለው መነሻው ይኼ ነው፡፡ እና እነዚህን አይነት ነገሮች የሚነሱበት ጊዜ አለ፣ እኔም ጋር የመጡበት ጊዜ አለ፡፡

33. አ፡ ግጭቶች?

መ1፡ አዎ

34. እንደዚህ ግጭቶቹ ሲፈጠሩ የሚፈቱት በምን ዓይነት መንገድ ነው?

መ1፡ እኔ እንዲያውም ምንድነው፡፡ የምለው ሁላችሁም መስራት ይኖርባችኋል፤ መሳተፍ ይኖርባችኋል፤ ይኼንን ደግሞ ለራሴ የማረጋግጥበት መንገድ አለኝ ነው፡፡ለምሳሌ የተሰራውን ስራ አጥንተው የሚመጡ አሉ ለዕብረቃ፡፡ ግን ከዚያ ያለፈ ነገር እጠይቃቸዋለሁ፤ ክሮስ ቼክ አደርጋለሁኝ፡፡ ሽ በትክክል ያንን ስራ መስራት አለመስራታቸውን፣ ጥያቄዎችን እየጠየኳቸው፣ ምን ያህል ሰርተዋል አልሰሩም እንዲያውም ብዙ ጊዜ በቃ አልሰራሁም እስከ ማለት የሚያደርሱ ተማሪዎችም የሚያጋጥሙኝ ጊዜ አለ፡፡

35. አ፡ ግጭታቸውን እንዲፈቱና ተስማምተው እንዲሰሩስ?

መ1፡ ግጭታቸውን እንደፈቱ፣ በዚህ መልኩ የሚመጡ ተማሪዎች ግጭታቸውን እንዲፈቱ የማደርገው በእርግጥ እኔ ጋ እንደዚህ ጎልቶ የደረሰ ግጭት የለም፡፡ ይኼንን ከውጭ ነው የምሰማው፡፡ ከውጭ ሰምቼ ግን ክፍል ውስጥ ይኼንን ነገር እናገራለሁ፡፡ እንደዚህ አይነት ነገሮችም አሉ፣ስለዚህ ከነዚህ ነገሮች እንድትጠነቀቁ፣የምትሰሩትን ነገር ተስማምታችሁ እንድትሰሩ፣ ሁሉም ሰው ሀሳቡን ያምጣ፣ያንን አቀናጅታችሁ አንድ ጥሩ የሆነ ነገር ሰርታችሁ ኑ፤ ብዬ ነው ምክር የምሰጣቸው፡፡

36. አ፡ የቡድን ስራዎች የሚገመገሙትና ውጤት የሚሰጣቸው እንዴት ነው?

መ1፡ በእርግጥ ውጤት ለመስጠት ከዚህ ቀደም እኔ ባለኝ ልምድ፣ አንድ የቡድን ስራ ተሰርቶ ይመጣል፤ የቡድን ስራው ያገኘውን አንድ ዓይነት ውጤት ነው የምሰጠው፡፡ ለምሳሌ ከአምስት ማርክ ከሆነ የምይዘው አምስት ማርክ ለአምስት ተማሪ ከሆነ አምስት አምስት ነው የምሰጣቸው ተመሳሳይ ውጤት፡፡ቅድም እንዳልኩህ ግን ከቅርብ ጊዜ በኋላ ባለው የአሰራር ለውጥ ለቡድን ስራዎች እኔ በበኩሌ ውጤት መስጠት አቁሚያለሁ፡፡ በዚህ በጋራ በሚሰሩት ነገር በጋራ ውጤት መስጠት አቁሚያለሁ፡፡ ባይሆን በጋራ የሰሩትን ነገር ፣ምንድንነው የማደርገው በሚሰሩት ስራ ተሳትፈው ለምሳሌ፣ ርዕስ ጉዳዮችን ተከፋፍለው እንዲያቀርቡ አደርጋለሁ፡፡ ከዚያ በሚያቀርቡበት ጊዜ ፣ ባላቸው ባቀረቡትና በሌላም ነገር አይቼ የተወሰኑ ውጤቶችን ነው ለመስጠት ሙከራ የማደርገው፡፡ ከዚያ ውጭ ግን ለግል ስራ ነው እንጂ ውጤት የምሰጠው ለቡድን ስራ ውጤት መስጠት አሁን አሁን አቁሚያለሁ፡፡

37. አ፡ የአሰራር ለውጥ ያለበት ምንድን ነው?

መ1፡ ከዚህ ቀደም የነበረው ነገር፣ የቡድን ስራ እናሰራለን፤ በአብዛኛው ኮሌጅም ተቋምም በነበርኩበት ጊዜ የቡድን ስራ እናሰራና ለምሳሌ አንድ የፕሮጀክት ስራ፣ ለምሳሌ የማስተማሪያ መሳሪያን በቡድን ሆናችሁ አዘጋጁ የሚል የምንሰጣቸው ጊዜ አለ በቡድን ያንን ነገር ይዘው ይመጣሉ፡፡ አየውና አሥራ አምስት የምሰጠው ከሆነ ለዚያ የማስተማሪያ መሳሪያ ሁሉም አሥራ አምስት እንዲያገኙ ነው የማደርገው ማለት ነው፡፡ እና በዚያ መልኩ ነው እንዲያገኙ የማደርገው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን አሁን ቅርብ ጊዜ ምናልባት የተወሰኑ ሰዎች ከኮሌጃችን ሄደው ወርክሾፕ ወስደው የተመለሱበት ጉዳይ አለ በዚህ ጉዳይ ላይ፡፡ ያም ምንድነው፣ ተማሪዎችን፣ በቡድን ስንገመግም የቡድን ውጤት መስጠቱ ጥሩ እንዳይደለም መጥተው እንዳስረዱን ማለት ነው፡፡ የሰዎችን የግል ችሎታ የማይመዝን እንደሆነ፣ ውጤት መስጠትም ካለብን መስጠት ያለብን ደረጃዎችን አውጥተን ለምሳሌ እጅግ በጣም ጥሩ፣በጣም ጥሩ፣ ጥሩ እያለ ደረጃዎችን አውጥተን ሰጥተን፣ በዚህ መሠረት ብንከታተላቸው የቡድን ስራዎችን፡፡ -ኧ- በግል የሚሰሩ ስራዎች ላይ ግን ውጤት መስጠት እንደሚቻል ነው፡፡ ይህንን፣ አንዳንድ ጊዜ ጥሩ በግል የሚሰሩ ተማሪዎች ውጤታቸው ላይ ዝቅተኛ ሊያመጡ ይችላሉ፡፡ ሶ በዚያን ጊዜ ይኼ እጅግ በጣም ጥሩ ፣በጣም ጥሩ፣ እያተባለ የተሰጠው ነገር፤ኋላ ላይ ይኸንንም ልናይላቸው እንደምንችል፣ የሚል ነገር ትሬኒንግ ተሰጥቶን ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ ነው እኔ እንዲውም ያቆምኩት ማለት ይቻላል ለቡድን ውጤት መስጠት ከዚያ በፊት በደንብ እሰጥ ነበር የቡድን ስራ አሰርቼ ተመሳሳይ ውጤት ነበር እሰጥ የነበረው፡፡ ከዚያ በኋላ እነዚህን ነገሮች ተገንዝቤ ትቼዋለሁ፡፡

38. አ፡ ተማሪዎቹ የቡድን ስራዎችን በመለዋወጥ የቢጤ እርማት የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ?

መ1፡ -ኧ- በዚህ መልኩ የሚገማገሙበት ጊዜ አለ፡፡ ክፍል ውስጥ የምንሰራቸው ስራዎችለምሳሌ አሁን የቢጤ እርማት ሲባል ያው እርስ በርስ የሚገማገሙበት ሁኔታ ይመስለኛል?

39. አ፡ አዎን

መ1: ከዚያ አንፃር የቡድን ስራዎች በሚቀርቡበት ጊዜ፣ በተላይ የቡድኑ ስራ በዕብረታል መልክ ይቀርባል:: እና መጨረሻ ላይ ምንድነው የማደርገው እኔ፤ እያንዳንዱ ስራ እየቀረበ እስቲ በቀረበው ሀሳብ ላይ እስቲ ሀሳባችሁን ስጡ:: ምንድን ነው የምትጠይቋቸው ጥያቄ አለ ወይ? ወይስ እናንተ የምታቁት ቀረ የሚባል ነገር አለ ወይ? ወይስ ስራቸው ራሱ አካሄዳቸው ችግር አለው ወይ? እስኪ አስተያየቶችን ስጡ እላለሁ:: እነዚህን ነገሮች አደርጋለሁ::

40. አ: የየራሳችሁን የቡድን መማር ሂደት እንዲገመግሙ፣ እያንዳንዳቸው የራሳቸውን የቡድን ተሳትፎ እንዲፈትሹ የሚደረግበት ሁኔታስ አለ?

መ1: -ኧ- በዛ በኩል እኔ በበኩሌ እስከአሁን ድረስ ያደረኩት ነገር የለም የራሳቸውን የቡድን ተሳትፎ በተመለከተ የጠየቅኳቸው ነገር በእርግጥ የለም::

41. አ: የቡድን መማር ማስተማር ሂደቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚገመግሙት እንዴት ነው?

መ1: ለራሴ? ለግሌ?

42. አ: አዎ::

መ1: ለግሌ ጠንካራ ብዬ የማስባቸው፣አንዳንዴ በቡድን ሲሰሩ ይችላሉ ብዬ የምሰጣቸው ርዕሰ ጉዳዮች አሉ:: እነዚያን ነገሮች ተማሪዎች ላይ ላዩን ሲሄዱ የማስተውልበት ጊዜ አለ:: እነዚህ ነገሮች ደግሞ አንዳንዴ፣ እኔን ጥሩ ስሜት እንዳይሰማኝ ያደርገኛል:: እና የቡድን ስራ በጣም ተማሪዎቹ አውቀው የሚገለገሉበት ከሆነ የሚጠቀሙበት ከሆነ ጥሩ ነው::ግን አንዳንዴ የሚያሸሩም አሉ:: ሶ ከዚያ አንፃር ሲታይ፣ የሚያሸሩትም ለምንድነው መጨረሻ ላይ ከመምህሩ የሚጠብቁት ነገር ይኖራል:: የሆነ ማጠቃለያ ሀሳብ እንደዚህ የሚባል ነገር አለ:: ስለዚህ ያቺን ጊዜ ብቻ የሚጠብቁ ተማሪዎች አሉ:: የቡድን ስራን እንደ ምንም ሳይቆጥሩ ወይም የረባ ነገር አይመጣም ብለው ያስቡ? ወይም መጨረሻ ላይ የሚነሳ ነገር አለ እንደርሳለን ብለው ይጠብቁት? ብቻ ከሆነ ነገር አንፃር የተማሪዎቹ የመስራት ተነሳሽነት የሚቀንስበት ጊዜ አለ:: ከዚህ አንፃር እኔ አብዛኛውን ጊዜ የቡድን ስራን ለመጠቀም ያለኝ ፍላጎት አናሳ ነው በበኩሌ::

43. አ: የቡድን ማስተማር ሂደትቱ ውጤታማ ነው፤ ውጤታማ አይደለም ብለው እንዲያው የማስተማር ሂደቱን ራሱን፣ የሚገመግሙበት ሁኔታ አለ?

መ1: ሙሉ በሙሉ ለኔ ውጤታማ ነው ብዬ አላቀርብም:: በተወሰነ መጠን ግን ውጤታማ የሆንኩባቸው ጊዜያት አሉ::

44. አ: አዎ እሱን በምንድነው የሚገመግሙት ማለቴ ነው?

መ1: እ እራሴን የማይበት ተማሪዎቹ በሚያቀርቡት አቀራረብ ላይ የምደሰትባቸው ጊዜያት አሉ:: እኔ ያላየኋቸውን ነገሮች ተማሪዎች የሚያቀርቡበት ጊዜ አለ:: ስለዚህ በዚያ ጊዜ የሚሰማኝ ስሜት በቃ ደስ የሚል ነው:: እንኳንም ይህንን ስራ በቡድን አሰራሁ የምልበት ጊዜ አለ:: ከዚህ ውጭ ግን፣ ቅድም ያልኳቸውን ነገሮች ተማሪዎች ሲያደርጉ ሳይ፣ ከዚያ በተቃራኒው ይሆናል::

45. አ: በመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ፣የቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት፣ ያጋጠሙዎት ችግሮች ካሉ ዘርዘር አድርገው ቢገልጹልኝ?

መ1. አኬ አንዳንዴ የማቴሪያል ችግሮች፣ ለምሳሌ በተለይ ውጭ በሚሰሩበት ጊዜ እነዚህን መፅሐፎች ካገኛችሁ፣ አስሳችሁ ሥሩ ብዬ እሰጣቸዋለሁ:: ነገር ግን፣ ወዲያውኑ እነዚህን መፅሐፎች አጥተናል:: ምንም አይነት ሶርስ ልናገኝ አልቻልንም ብለው እኔ ጋ የሚመጡበት ጊዜ አለ:: ሶ ከዚህ አንፃር እራሱ ለማስተማር በጣም አስቸጋሪ ነው:: ሞጁሎቹ ተባዝተው በበቂ ሁኔታ በቤተ መፅሐፍ አይቀመጡም:: ሌሎች በቡድን ሥራ ጊዜ የተማሪዎች ዝግጁ አለመሆን:: እነዚህ በቡድን ሥራ ላይ ተፅዕኖ አድርገውብኛል:: ከዚያ ውጭ መሰረታዊ የአማርኛ ኮርሱ፣ የመቀነጫጨብ ችግር ነው ያለበት:: አሁን ለምሳሌ ስነፅሑፍ ያነሰና ከዳር ሳያደርስ ሰዋስው ይገባል:: ሰዋስውንም የሆነ ነገር አንስቶ ከዳር ሳያደርስ የሆነ ነገር ላይ፣ እና ተማሪዎች ገባ ብለው እንዲወያዩ፣ ሃሳብ እንዲሰዋጡ ለማድረግ ያለው የይዘቱ፣ የራሱ ቁጥብነት ራሱ ብዙም ገባ ብለን እንዳናይ፣ የቡድን ስራዎችን እንዳናሰራ የሚያደርግበት ሁኔታ ያጋጠመኝ ጊዜ አለ::

46. አ: ባጠቃላይ ስለ ቡድን ማስተማር ዘዴ ያልዎት አስተያየት ምንድነው?

መ1: እኔ ጥቅል የሆነው ሃሳብ ያለኝ፣ የቡድን ስራ ያው እንደሚታወቀው አንዱ የማስተማሪያ ዘዴ ነው:: ግን ብቸኛው አይደለም:: ሌሎች የማስተማሪያ ዘዴዎችንም በአግባቡ መጠቀም ተገቢ ይመስለኛል:: ነገር ግን በተለይ የተማሪዎችን የመናገር እና የውይይትንም ባህል የማዳበር ነገር አለ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ለተማሪዎቹ በጣም ይጠቅማል::አ-አንዱ የማያውቀውን ሌላው የሚያውቅበት ሁኔታም ስላል ልምዶችን እንዲለማመዱ የሚሰጠው

ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው።ስለዚህ ይሄ የቡድን ስራ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ነው። ግን ሁልጊዜ ያንን የቡድን ስራ መጠቀም አግባብነት ያለው አይመስለኝም። እና ግን ጥሩ ነው። ጥሩ የማስተማሪያ ዘዴ አድርጌ ነው የምወስደው።

47. አ፡ ስላደረጉልኝ ትብብር እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።

መ1፡ እሺ. እኔም አመሰግናለሁ።

ክፍል ማለትም ከ40 በታች ያለበት ከሆነ፣ ስድስት እንዲሆኑ አደርጋለሁ:: ከ40 እስከ 50 የሚደርሱ ከሆነ ከ6-8 እንደሁኔታው አደራጃለሁ::

13. አ: በምን መስፈርት ነው ተማሪዎች ለአንድ ቡድን አባልነት የሚመረጡት?

መ2: ለቡድን የሚመረጡት ብዙ ጊዜ፣ ጊዜን ለመቆጠብ እንደተቀመጡበት አደርጋለሁ:: ሌላ ጊዜ ደግሞ፣አልፋቤቲካል ከ1-6፣ 7-12 እያልኩ በተራ ቁጥር ራንደምሊ እንዲ ተመራርጠው እይደለም:: የውጪ የቡድን ስራዎች በማሰራበት ጊዜ ተማሪዎቹ የመመራረጥ ሁኔታ አለ፣ ምክንያቱም አብሮ ለመስራት፣ አብሮ ለመገናኘት ፣የቡድን ሪፖርቱን ለማጠናቀር የሚቀራረቡ ይፈላለጋሉ:: ይህንን ዕድል ሁል ጊዜ አልሰጥም:: ምክንያቱም፣ የሚተዋወቁ ሲሆኑ አንደኛው ብቻ ሀላፊነቱን እንዲወስድ ያደርጉና ሌሎቹ ድርሻ አይኖራቸውም:: ያ እንዳይሆን ብዙ እንትን የማይላቸው ሲሆን አፈቅድላቸዋለሁ:: ከዚህ ውጭ ግን በራሴ እንትን ነው፣ ወይ እዚያው እንደተቀመጡ ስድስቱን በአንድ ላይ እንዲሰሩ አደርጋለሁ:: የማይተዋወቁም ቢሆኑ ዕውቀታቸውን አንድ ላይ እንትን እንዲሉ፣ ይጠቅማቸዋል፤ይሰራሉ:: የሚተዋወቁ ሲመራረጡ፣ ይህን ያህል ትኩረት አይሰጡም፤ አይፈራሩም:: እንዱ ሌላውን ደግሞ እንትን እንዳይል ለተወሰነው ብቻ እንዲሰራ ይሰጥና ሌላኛው ነፃ ይሆንና ከውይይቱ ይወጣል:: ያ እንዳይሆን አንድም በአቀማመጥ፣ አንድም በአልፋቤት፣ሌላ ጊዜ ደግሞ አልፎ አልፎ፣ተመራርጠው የራሳቸውን ቡድን መስርተው እንዲሰሩ አደርጋለሁ:: የተወሰነ መስፈርት የለውም::

14. አ: አባላቱ በአንድ ቡድን አባልነት ምን ያህል ጊዜ አብረው ያቆያሉ?

መ2: አሳይመንቱን እስኪሰሩ ድረስ ብቻ ነው:: የተሰጣቸውን የቡድን ስራ ካስረከቡ በኋላ፣ቡድኑ ይፈርሳል:: በሚቀጥለው ደግሞ ሌላ ቡድን ይኖራል:: በቋሚነት የሚቆይ ቡድንም ሊኖር ይችላል::

15. አ: እሀ እንዴት?

መ2: አሁን በቋሚነት የሚቆይ ቡድን ሲባል፣ አንዳንድ በተከታታይ የሚሰሩ ስራዎች አሉ:: ለዚያ የተወሰነ ቡድን ይኖራል:: ግን አንድ ፕሮጀክት ተቀርጾ የሚሰጠው በዚያ በፕሮጀክቱ ጊዜ በተሰጠው ቡድን ነው፤ፕሮጀክቱ እስኪያልቅ:: ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ቡድኑ ይፈርሳል::

16. አ: አንድ ቡድን ስራን ለመስራት፣ የቡድን አባላት የየሥራ ድርሻውን የሚከፋፈሉት እንዴት ነው?

መ2: የየስራ ድርሻ አሁን እገሌ ይሄ ነው ብዬ አላከፋፍልም::ግን ሰዓት ተቆጣጣሪ እንዲኖር ያስፈልጋ:: እንዲሁም ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ፣ፀጥታ አስከባሪ እንደዚህ የስራ ድርሻ እንዲኖራቸው ይጠበቃል:: ሁሉም የራሱን ድርሻ ይወጣል:: አሁን የቡድኑ ሪፖርት አቅራቢ ሰዓቱን ያልጠበቀ ከሆነ፣ የቡድኑ ሰዓት ጠባቂ፣ ምልክት ሊሰጠው ይገባል::እኔ ሳልሆን እሱ ይቆጣጠራል:: ምክንያቱም ሰዓት አለመጠበቅ የቡድን ስራዉን ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ስለሆነ ይጠበቃል:: እነሱም በሚሰሩበት ጊዜ በጊዜ መጠቀም እንዲችሉ፣እሱ የራሱን ድርሻ ይወጣል:: ለዚህ ነው የሚከፋፈሉት::

17. አ: ተማሪዎቹ በሙሉ ስለ ቡድን መማር አላማና አሰራር በቂ ግንዛቤ አላቸው ይላሉ?

መ2: እንግዲህ እንደተማሪው መረዳት ነው? የሚጠቅም ነው ብለው የሚያስቡ አሉ:: በአብዛኛው ተማሪ ሰርቶ ማግኘት እንዳለበት የሚያምኑ አሉ:: አንዳንዶቹ ግን ሥራ ይበዛል ቢዚ ያደርገናል ከሚል ያለመቀበል ነገር አለ:: ሁሉም ተቀብለውታል ለማለት አልችልም::ሁሉም መምህር ደግሞ ተማሪ ለመቀበል በሚችል ዓይነት አያቀርብም፤የተወሰኑ መምህራም ሌክቸር ሜተድ እንደሚሻል አድርገው ስለሚገምቱ፣ ተማሪም ደግሞ ሌክቸር ሜተዱን ነው የሚፈልገው:: ምክንያቱም ከክፍል ውጭ ብዙ አይደክምም::ደብተሩን ያጠናል:: የቡድን ስራ ከሆነ ግን ከክፍል ውጭ ቢዚ ያደርገዋል:: ስለዚህ ብዙዎቹ ጠቃሚ መሆኑን ቢያምኑም ሬዚዝት የማድረግ ነገር አለ:: የኔ ስራ ነው፤ በዚህ አይነት መማር አለብኝ ብለው ተቀብለዋል ለማለት ያስቸግራል::

18. አ: እርስዎም ተማሪዎቹ የቡድን መማር ዓላማን እንዲያውቁ ያስተምሯቸዋል?

መ2: እነግራቸዋለሁ፤ ጠቃሚነቱን እነግራቸዋለሁ:: እንዲያውም በዚህ ሀሳብ ላይ ክርክር እንዲያደርጉ አድርጊያለሁ:: ተማሪ ተኮር ትምህርት ከአስተማሪ መራሽ ትምህርት ይሻላል? አይሻልም? እንዲከራከሩ ሁሉ አድርጊያለሁ::አሁን ተማሪ ትምህርቱ እንደሚጠቅም ዕውቃል:: ግን መሠረታዊ የሆነ ከታች ይዞት የመጣው ነገር ስለሌለ፣ አቅም ስለሚያንሰው ነው ሬዚስት የሚያደርገው :: ሲከራከሩ የሚያቀርቧቸው ሀሳቦች እንደሚጠቅሙት:: ለምን ለተሻለ ዘዴ መሆኑን ካለው ልምድ እራሳቸው ደግሞ ክፍል ወስጥ በመናገራቸው ውጭ ሲወጡ የመናገር ችሎታቸው እንዳበረ፣ አምና ከነበራችሁበት

አሁን ምን ይመስላል? የራሳችሁን አቅም ስትገምቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ አሁን እናንተ ቆማችሁ አንድ ነገር አቅርባችሁ፣ ማለት ሪፖርት አቅርባችሁ የተሳሳታችሁትን ነገር አርማለሁ፣ ለምን ለሚቀጥለው ጊዜ ይህንን አትሳሳቱም:: ስለዚህ ለውጥ ይመጣል:: ወዲያው ለውጥ ማምጣት የምትችሉበት ነገር አይደለም ወይ? ካለው ተጨባጭ ሁኔታ በማስረዳት፣ተማሪው ይቀበላል:: እንደሚጠቀመውም እያመነ:: ነው ከዚያ ለውጥ አያለሁ::በራሳቸው ፍላጎታቸው እየጨመረ እንደሚሄድ ነው የማየው:: ስጀምር መጀመሪያ ፣ትምህርቱን ማስተማር ስጀምር በአንደኛ ሲሚስተር በመጀመሪያ ሁለት ወር ያለውና ወደ መጨረሻው ያለው ለውጥ ያለው ነው::

19. ለ: ማለት ተሳትፏቸው ነው?

መ2: አዎ ተሳትፏቸውም እየጨመረ ይሔዳል፤ እየተበረታቱም ይሄዳሉ:: ስለዚህ በአብዛኛው እየተቀበሉት ነው ማለት ያቻላል::ግን ሬዚስት የሚያደርግ የለም ማለት አይደለም::

20. ለ: ተማሪዎች በቡድን ስራ ወቅት ምን ማድረግ እንዳለባቸውና ምንስ ማድረግ እንደሌለባቸው የሚያስገነዝብ የተዘጋጀ መመሪያ አለ?

መ2: በፅሁፍ የተዘጋጀ መመሪያ የለም:: ያው እኔ በማስተማር ልምድ ባገኘሁት፣ እና ሀየር ዲፕሎማ ላይ ካለው ልምድ ተነስቼ ይኼ ይኼ ነው ከምለው በስተቀር በፅሁፍ የተዘጋጀ ነገር የለም:: ቢኖር ጥሩ ነበር ፣ ሁሉም መምህር በተመሳሳይ መልክ እንዲመራ ቢደረግ ጥሩ ነበር:: ይመረጣል ግን የለም::

21. ለ: ሀየር ዲፕሎማ የሚለው ስላነሱ ነው? ሀየር ዲፕሎማ ፕሮግራም መከታተዎ ፣ የቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ ምን ያህል ረድቷዎታል?

መ2: ይጠቅማል ይጠቅማል:: ከሀየር ዲፕሎማ ውጭ ለዚህ የቡድን ስራ ልምድ ያገኘሁበት ሌላ ማንበቢያ ነገር የለም በእርግጥ በዩንቨርስቲ ቆይታዬ በቡድን ስራዎች አንዳንድ ወረቀቶችን ሰርተናል::ያም ቢሆን ይኼኛው የሀየር ዲፕሎማው እራሳችን ሰርተንበት ያለፍንበት ስለሆነ፣ በተግባር የምትሰራበት ስለሆነ የበለጠ የጠቀመኝ ሀየር ዲፕሎማ ነው ብዬ ነው የማስበው::

22. ለ: በተለይ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ሁሉም የቡድን አባላት እኩል ተሳትፎ የሚያደርጉ ይመስሎታል?

መ2: እርግጠኛ መሆን አልችልም::ምክንያቱም እኔ የቡድን ስራ እንዲያቀርቡ ሳደርግ ፣ እነሱ መርጠው አይደለም የቡድን ስራ አቅራቢውን እኔትን የሚሉት፤ቡድኑን አደራጅና፣ሁሉም አላፊነቱን ተወጥቶ መምጣቱን ለማረጋገጥ፣የፈለገውን ተማሪ ከቡድኑ ውስጥ አቅርብ እላለሁ:: ዛሬ የሚያቀርበው እከሌ ነው ብዬ ነው የምነግራቸው እንጂ፣ ሲዘጋጁ ማን እንደሚያቀርብ አያውቁም::

23. ለ:ድንገት ነው እንዲያቀርቡ የሚጠይቋቸው?

መ2: አዎ ድንገት ፤ ክፍል ውስጥ እነሱ ተዘጋጅተው ከመጡ በኋላ፣ እኔ ነኝ አቅራቢውን የምመርጠው:: ስለዚህ በፍርሃት ይዘጋጃሉ::ቢዘጋጁም አሁን እነሱ መርጠው የሚያቀርቡት ተማሪ እና እኔ መርጬ የማቀርበው ተማሪ፣እኩል አይደለም ዝግጅታቸው ፣ስለዚህ ሁሉም እኩል ተሳትፏል ብሎ መናገር ይከብዳል:: የሚዘጋጁ ቡድኖች አሉ:: እንደ ተማሪዎቹ ጠንካራ ተማሪዎች ይዘጋጃሉ፣ ደከም የሚሉትና ፍርሀት የሚሰማቸው አቅሙ የሌላቸው በተለይ፣ እራሳቸውን ለማጋለጥ አይፈልጉም፣ የቡድኑ አባልት ሆነው ነው የሚቀመጡት፣አንድ ላይ ሲሰሩ፣አንዱ የሌላውን አቅም ጨርሶ ለማወቅ ስለማይፈልጉ:: ይኼ የኔ ግምት ነው መስለው ይቀመጣሉ፣ግን ተሳትፎአቸው እኩል ነው ለማለት አይቻልም::

24. ለ: ተማሪዎች የቡድን ሥራዎችን ለመስረያ ወይም ስራዎቹን በክፍል ውስጥ ለማቅረቢያ የሚረዱ የዕሕፈት መሳሪያዎችን የሚያገኙት ከየት ነው?

መ2: ይህንን ከራሳቸው ነው :: እኛ አናድልም::

25. ለ: ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰሩ ስራዎችን ከሰጡ በኃላ እርስዎ በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ቢዘርዝሩልኝ?

መ2: እኔ በየቡድኑ እዞራለሁ፤ ጥያቄዎች ካሏቸው አሁን ሲጨቃጨቁ የማገኛቸው ቡድኖች አሉ:: በምን ጉዳይ ነው የትጨቃጨቁት? ያልተግባባችሁት በምን ሀሳብ ነው? ብዬ እጠይቃቸዋለሁ:: ይነግሩኛል:: እሱ እንዲህ ኢያለ ነው፤ እኔ እንዲህ እያልኩ ነው እና መግባባት አልቻልንም ይላሉ: መግባባት የሚችሉበትን መስመር አስይዛለሁ:: ሳይሰሩ ደግሞ ዝም ብለው ሁለትና ሦስቱ ብቻ እየተናገሩ፣ ሌሎቹ ዝም ብለው የሚቀመጡበትን አገኛለሁ :: የማይሳተፉበት ምክንያት ምንድን ነው ? ያንተ የሥራ ድርሻ ምንድን ነው ? የሥራ ድርሻ አልተከፋፈላችሁ ወይ? በሥራ ድርሻ እየሰሩ እንደሆነ፣ በምን አይነት

ፀሐፊው እየፃፈ እንደሆን ስብሳቢው ደግሞ በምን አይነት ሁሉንም ተማሪ እያስተፈ እንሆን እከታተላለሁ ::

26. አ: በክፍል ውስጥ አለመግባባቶች እንደሚከሰቱ ጠቁመዋል፣ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎችስ አለመግባባቶች የሚከሰቱበት ሁኔታ አለ?

መ2: እንግዲህ አለመግባባቶች ስንል በሁለት አቅጣጫ ነው:: በሳብጀክቱ በትምህርት አይነቱ በሚሰጡት ሀሳብ ያለመግባባት ነገር ሊኖር ይችላል:: አንደኛው ይሄ በዚህ ነው የሚተረጎመው ይላል እና ሌላኛው ይኼ በዚህ ነው የሚተረጎመው ይላል:: የዚህ አይነት አለመግባባት ሊኖር ይችላል:: ሌላው ደግሞ ለምሳሌ ገንዘብ አዋጥተው በሚሰሩበት ስራም ያለመግባባት ይኖራል:: አንዳንዴ ገንዘብ አዋጥተው በጥሩ የማስተማሪያ ዘዴ፣የትምህርት ዝግጅታቸውን ለማቅረብ ለሪፖርታቸው የትምህርት መርጃዎችን አዘጋጅተው ለማቅረብ ወጪ ይጠይቃል:: በዚያ ወጪ የሚባሉ ይኖራሉ:: አሁን ፣ በጥሩ ወረቀት በከለር፣ እንደዚህ ዕሬን እናቅርብ ብለው ሀሳብ የሚያቀርቡ፤ ክፍሎች ይኖራሉ፤አይ እኛ አንችልም ዝም ብለን በወረቀት እንዳለ እናቅርብ፤ በእስክሪቢቷችን ዕሬን የሚሉ አሉ:: በዚህም ያለመግባባት እንደሚኖር እገምታለሁ:: ምክንያቱም ብዙ ጊዜ እንደዚህ አይነት ነገር ይቀርባል:: ሰሩ ያለ የቡድን ስራ በሚሰጥበት ጊዜ ይነግሩኛል:: ቲቸር እንደዚህ ባናቀርብስ? የቡድን መሪያችን እንደዚህ አይነት ይሁን ብሎናል:: እኛ ገንዘብ የለንም ብለው ያላሉ:: አይ አትገደዱም ነእንደዚህ ብታቀርቡ ጥሩ ነው ልምዱ ለናንተ፤ ግን አቅሙ ከሌላችሁ አትገደዱም:: እንዲህ ይሁን ብሎ ወደ ማስገደዱ የሄደውንም ጠርቼ፣ በዚህ በዚህ መልኩ ማቃለል ትችላላችሁ ብዙ ከሮ አይሔድም ብቻ:: አለመግባባቱ ከሮ የሚሔድ ሳይሆን በሚያቀርቡት ነገር ዙሪያ የተወሰነ ያህል ሊኖር ይችላል:: አዎ እና አጋጥሞኛ ልም:: እነዚህን በቀላሉ ደግሞ መፍታት ይቻላል::

27. አ: የቡድን ሥራዎች የሚገመገሙትና ውጤት የሚሰጣቸው እንዴት ነው?

መ2: የቡድን ስራዎችን የምገመግምበት አሰራር አንድ ተማሪዎቹ የቡድን ሥራዎቹን በክፍል ውስጥ ሪፖርት ያደርጋሉ:: ሪፖርት ሲያደርጉ ሩብሪክ አዘጋጃለሁ:: ምን ምን ላይ ማተኮር እንዳለብኝ ማሪው እንዴት ሰዓት ይጠብቃል፣ ድምጹ ለክፍሉ በሙሉ መሰማቱና ስሜት የመሳቡ ሁኔታ፣ባጠቃላይ የማያቸው ነጥቦች አሉ::

28. አ: መስፈርት?

መ2: አዎ መስፈርት እኔ ቀደም ብዬ አዘጋጃለሁ:: የመገምገምያ መስፈርት፣ በዚያ መስፈርት ያሟላ ያለሟላ ቼክሊስ ራይት እያደረግሁ አልፍና የቡድን ሥራቸውን ደግሞ እቀበላለሁ:: ከዚያ በኋላ እዚያ ላይ የጻፉትን ሀሳብ አነባለሁ:: ሁሉቱንም እንትን ካልኩ በኋላ ነው ነጥብ የምሰጣቸው:: ወረቀቱንም አነባለሁ ክፍል ውስጥ እንዴት እንዳቀረቡም ማስታወሻ እይዛለሁ:: ሁሉቱንም አንድ አድርጌ ውጤት እሰጣቸዋለሁ::

29. አ: የቡድን አባላት በአንድ ቡድን ሥራ ውጤታቸው ይለያያል ወይስ አንዳይነት ነው?

መ2: አንዳይነት ነው::

30. አ: ተማሪዎች የቡድን ሥራዎችን በመለዋወጥ የቢጤ እርማት የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ?

መ2: እንግዲህ እስካሁን ባስተማርኩት ቡድን አያሳትፍም፣ ለምሳሌ የድርሰት ሥራ ሲሆን እንደዚያ ማድረግ ይቻላል:: እሳካሁን ባስተማርኩት ቡድን አላደረግኩም:: በርግጥ አሁን እርስ በርስ የሚተራረሙበት ሁኔታ አለ፤ ክፍል ውስጥ አንዳንድ ጊዜ የክፍል ሥራ ከሰሩ በኋላ፣ በግል ከሰሩ በኋላ ደብተራቸውን ተለዋውጠው አንዱ የሌላኛውን እንዲያርም የማድረግ ልምድ አለ:: ግን የቡድን ሥራን በቡድን እንዲያርሙ አድርጌ አላውቅም:: እስካሁን ባስተማርኩት ኮርስ እንደዚህ አይነት ሥራ የሚያሰራም አልገጠመኝም::

31. አ: የራሳቸውን የቡድን መማር እንዲያዩ ወይም እንዲገመግሙ የሚደረግበት ሁኔታ አለ?

መ2: አሁን ይኼን ያሳያቸዋል ብዬ የማስበው ምንድነው፣ እኔ የሰሩትን ሥራ አሰባስባለሁ:: ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ ድረስ፣ሰብስቤ፣ እርሚ እራሳቸው ደግሞ መልሰው እንዲያዩ ወረቀቱን መጨረሻ ላይ እመልስና ያረምኩትን የመጀመርያችሁ ምን ይመስላል? ሁለተኛ ሦስተኛ ወረቀታችሁ ምን ይመስላል? ሦስተኛ አራተኛ ወረቀታችሁ ምን ይመስላል? አሁን ያላችሁበት መጀመርያ ከነበራችሁበት ኮርሱን ስንጀምር ከነበራችሁበት ስንጨርስ ያለችሁበት ሁኔታ ምን ይመስላል? በሚል ክፍል ውስጥ እንወያያለን:: አዲስ ነገር ምንድነው ያገኛችሁበት? ያሳያችሁት ለውጥ ምንድነው የሚለውን ነገር ውይይት እናደርጋለን::

32. አ: የቡድን መማር ማስተማር ሂደቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ማለትም ውጤታማ ነገር? ወይስ ውጤታማ አልነበረም የሚለውን እንዴት ነው የሚገመግሙት?

መ2: በቡድን ማስተማር ጠንካራ ጎን አለው:: ተማሪ አሳታፊ ነው ያነግራል፣ ያጽፋል ክሂሎችን ለማዳበር ጠቃሚ ነው እውቀትም ደግሞ ይካፈላሉ:: አንዱ ከሌላው ቡድን የሚያጠራው ነገር አለ:: በጣም ጠቃሚ ነው እውቀት ያገኙበታል:: ያስተሳሰብ ለውጥ በቀላሉ ያገኙበታል:: ችግሩ ምንድነው የጊዜ እጥረት ነው:: 40 ደቂቃ ነው:: በ40 ደቂቃ ክፍል ውስጥ የተሰሩትን ሥራ የተሰጠውን የቡድን ሥራ እዚያው ክፍል ሰርቶ እዚያው ማቅረብ አይችሉም:: ግዜው አይበቃም አሁን እንደሰሩ እንስጣለን አስር ደቂቃ ወይም አስራ አምስት ደቂቃ፣ በአሥር ደቂቃ ብዙ ነገር አያስቡም:: ብዙ ነገር መስራት አይችሉም:: ከአስር ደቂቃ በኋላ እንዲያቀርቡ እንጠይቃለን በሚያቀርቡበት ጊዜ አሁን ፣እኔ ኖርማል አንድ አይነት ጥያቄ አልሰጣቸውም፣ የተለያየ ጥያቄ ነው የምሰጠው ምክንያቱም አንደኛው ቡድን ካቀረበ ሌላኛው ቡድን ካቀረበ ሌላኛው ቡድን የዚያን ግልባጭ ነው የሚያቀርበው:: ስለዚህ ብዙ አይጣጣሩም:: የተለያዩ ጥያቄዎችን ለየቡድኑ እሰጥና አንዱ ከሌላው የተለየ ስለሆነ ሁሉም አዲስ ነገር መማር ይችላሉ:: ሁሉም አዲስ ነገር ያቀርባል:: ስለዚህ የሁሉም ማዳመጥ ደግሞ ይችላሉ:: ይህንን ለማድረግ 40 ደቂቃ፣ 50 ደቂቃ አይበቃም:: ደግሞ ወንበሩም አመቺ አይደለም፣ እና ወንበሩን ስበው ሌላ አስተማሪ ሲመጣ ወንበር ማስተካከል ጊዜ የሚጠይቅ ነው:: ስለዚህ ችግሩ እዚያ ላይ ነው:: እዚህ ላይ ችግር አለ 97/96 አም ከአሁን በፊት በነበረው ሁለት ተከታታይ ፔሬድ ይሰጠን ነበር:: ያ ጥሩ ነበር:: ሁለት ተከታታይ ፔሬድ ሲሆን የመስሪያ ጊዜ አለ የማቅረቢያ ጊዜ አለ በክፍል ውስጥ ለሚሰጥ የቡድን ስራ ተከታይ ክፍለ ጊዜ አንድላይ ሲሆን የተሻለ ነው ውጤታማም ነው:: ለመምህሩም ለተማሪውም:: ግን በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ የምናሰራው የቡድን ሥራ ብዙም ለውጥን የሚያስከትል አይደለም:: ወደ ውጭ ስናወጣው የማይሰሩ ሊበዙ ነው:: ክፍል ውስጥ ሲሆን ግን ሁሉም ይሳተፋሉ አስተመሪ እየተከታተለ ስለሆነ፣ ችግሩን ደግሞ ሁሉም ማቅረብ አይችልም:: ወደቤት መሄዱ አይቀርም:: ወደቤት እንደሚሄድ ስለሚያውቁ፣ ክፍል ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ አያርጉም:: ቅድሚያ የቀረበው ቡድን የተወሰነ ነገር ይሰጣል፣ ከሱ ያገኙትን ልምድ ይወስዱና ትንሽ ነገር ተዘጋጅተው ይመጣሉ::

33. አ: የማስተማር ሂደቱን ማለትም የዛሬው ክፍለ ጊዜ ጥሩ ነበር አልነበረም የሚለውን የመገምገም ሥራ አለ?

መ2: ጠንካራ ነው ማለት ይቻላል:: ድክመት ይኖራል አንዳንድ ድክመት ይኖራል:: አስተማሪ መራሽ ትምህርት ተማሪ መራሽ ትምህርት በቡድን መሰራቱ ጠንካራ ጎን አለው እላለሁ::

34. አ: መሰረታዊ አማርኛ ኮርስ፣ የቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት፣ ያጋጠመዎት ችግር ካለ ዘርዘር አድርገው ቢገልጹልኝ?

መ2: የጎላ ችግር ነው ብዬ የማቀርበው ነገር የለም:: ያው እኔ ሳቀርብ፣ ጥያቄውን ሳዘጋጅ ጥሩ አቀራረብ ሳይኖረኝ ሲቀር ውጤታማ የሆነ የቡድን ሥራ ላይኖር ይችላል:: ጥሩ ዝግጅት ጥሩ ፕሮፖዛል አቅርቤ ተማሪዎቹ ሰርተው ሲያመጡ ምንም ችግር አላጋጠመኝም::

35. አ: በአጠቃላይ ስለቡድን ማስተማር ዘዴ ያለዎት አስተያየት ምንድነው?

መ2: የቡድን ማስተማር ዘዴን የበለጠ የተሻለ የሚያደርገው ሁሉም መምህር፣ መምህራን እራሳቸው በዚህ አይነት ተምረው ያለፉ አይደሉም:: እነሱ የተማሩትን ዘዴ ተከትለው ነው የሚያስተምሩት:: ያ ነው ሪፍሌክት እየሆነ ያለው:: ያንን እንዲተዉ ለመምህራን ጥሩ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል:: በማስተማር ላይ ላሉ መምህራን ደግሞ አንድ አይነት የቡድን አሰራር እንዲኖር ሁሉም ለዚህ ሥራ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ፣ የተዘጋጀ መመሪያ ቢኖር፣ ምንድነው አንድ መምህር የቡድን ስራ በሚያሰራበት ጊዜ፣ መከተል አለበት የሚለውን ነገር የሚመራ ነገር ቢኖር፣ ሌላው ደግሞ የመጻሕፍ ዝግጅት ነው:: ሲዘጋጁ መጻሕፍቱ፣ ለቡድን ሥራ የሚመቹ ጥያቄዎችን ይዘው የሚዘጋጁ ቢሆን የተሻለ ነው የሚሆነው:: መምህሩ በዚያ ላይ ተማሪ የለውን ያዳበርና የተሻለ ውጤት ይገኛል:: እና እንደዚህ አይነት ነገሮች ቢኖሩ ሂደቱን የበለጠ ውጤታማ ያደርገዋል ብዬ አስባለሁ::

36. አ: እሺ ስላደረጉልኝ ትብብር በጣም አመሰግናለሁ::

መ2: እሺ ምንም አይደል::

# አባሪ 7

በሆሳህና መም/ት/ኮሌጅ የመሠረታዊ አማርኛ ኮርስ መምህር 3፣ ለቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች

1. አ፡ - በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ምላሽ ለመስጠት ትብብር ስላደረጉብኝ አመሰግናለሁ ለመነሻ ያህል የትምህርት ደረጃዎን ቢገልፁልኝ?

   መ3: አማርኛ በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ አለኝ::
2. አ፡ ለምን ያህ ጊዜ በመምህርነት አገልግለዋል?
   መ3: ለ5 ዓመት ያህል ::
3. አ፡ በኮሌጅ መምህርነትስ ለምን ያህል ጊዜ አገልግለዋል?
   መ3: አይ አምስቱንም በኮልጅ መምህነት ነው:: ከዚህ ውጪ ግን አንድ ሁለት አመት በሀይስኩል መምህነት ሰርቻለሁ:: በአጠቃላይ 7 አመት ማለት ነው::
4. አ፡- የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራምን ተከታትለዋል?
   መ3: አዎ
5. አ፡ ተማሪዎች በቡድን ሆነው እንዲማሩ ያደርጋሉ?
   መ3: አዎ እንደየ ፖርሽኑ ይዘት በቡድን የማደርግበት ሁኔታ አለ::
6. አ፡ በመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ የቡድን ማስተማር ዘዴን ምን ያህል አዘውትረው ይሰሩበታል ?

   መ3: በዘህ ኮርስ የተለያዩ ንዑሳን ምዕራፎች አሉ:: ተማሪዎች በየንዑስ ምዕራፎቹ እንደ ኮርሱ ባህሪ በቡድን የሚሰሩበት አጋጣሚ ስላለ በዚህ ጊዜ ነው በወር ወይም በሳምንት ብዬ ለክቼ መናገር ባልችልም ግን የሚሰሩበት አጋጣሚዎች አሉ::
7. አ፡- በእርስዎ አስተያየት ተማሪዎች ቡድን ሆነው እንዲሰሩ የማድርግ አላማ ምንድነው?
   መ3. እንግዲህ በኔ ግምት : በቡድን በሚሆኑበት ጊዜ ምናልባት ለመምህሩ መነገር ወይም ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: ሀሳቸውን ለጓደኞቻቸው ደግሞ በቀላሉ ሊናገሩ ስለሚችሉ እነዚያ ተማሪዎች ዕድል እንዲገኙ ያደርጋል:: ሌላው ከጓደኞቻቸው እንዲማሩ እና የራሳቸውን ዕውቀት እንዲያሻሽሉ ዕድል ይሰጣል:: ለመማሪያም ለማስተማሪያም የሚጠቅም ዘዴ ስለሆነ::
8. አ፡- በተለይ ከቋንቋ ትምህርት አንፃር ፣ ለቋንቋ ትምህርትስ ምን ያህል ጠቀሜታ አለው ?
   መ3: የቡድን ትምህርት በተለይ በቡድን አድርጎ ማስተማሩ በተለይ ለቋንቋ በጣም ጠቃሚ ነው ብዬ አስባለሁ:: ለምን ከጓደኞቻቸው ጋር በቀላሉ ሊናገሩ ሊያዳምጥ ይችላሉ:: እግረ መንገዳቸውን የቋንቋ ችሎታቸውን ሊያዳብሩ ይችላሉ::
9. አ፡ የቡድን ማስተማር ዘዴን በተመለከተ የወሰዷቸው ስልጠናዎች አሉ?
   መ3: በዚህ ላይ በእርግጥ የሀየር ዲፕሎማ ፕሮግራም ውጪ በቡድን ስለማስተማር የተለየ ስልጠና መውሰዴን አላስታውስም::
10. አ፡- ይኼ የሀየር ዲፕሎማ ፕሮግራም የቡድን ማስተማርን ተግባራዊ ለማድረግ ምን ያህል ረድትዎታል?
    መ3:- በጣም ብዙ ጥቅሞች አሉት:: እዚያ የሚቀርቡት ተግባራት በሙሉ፣ ከዚህ ጋር፣ በቡድን ከማስተማር ጋር፣ በተለይም ትምህርቱን ተማሪ ተኮር አድርጎ ከማቅረብ ጋር በቀጥታ የሚገናኙ ስለሆኑ፣ ያ ስልጠና በቀጥታ ግንኙነት አለው ብዬ አስባለሁ::
11. አ፡- ለተማሪዎች የቡድን ሥራዎችን ለመስጠት ሲያስቡ ምን አይነት ቅድመ ዝግጅትን ያደርጋሉ?
    መ3. መጀመሪያ የምሰጠውን ሥራ እለያለሁ:: ከዚያ ተማሪዎች ምን ምን ማከናወን እንዳለባቸው እወስናለሁ:: ተማሪዎች ደግሞ በቁጥር አራት አምስት እየሆኑ እንዲወያዩ አደርጋለሁ:: እነዚህ ናቸው ቅደም ተከተሎቹ::
12. አ፡- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድን የሚሰሯቸው ሥራዎች ምን አይነት ናቸው ?
    መ3:- ለምሳሌ በአንድ ርዕስ ዙሪያ ተነጋግረው፣ የራሳቸውን ሀሳብ ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ የሚጠየቁ ነገሮች ይኖራሉ? ተወያይተው ሀሳባቸውን በሪፖርት መልክ እንዲሰጡ ይደረጋል:: እነዚህ እነዚህ ናቸው::
13. አ፡- ከክፍል ውጭ የሚሰሯቸው የቡድን ሥራዎች ምን አይነት ናቸው?
    መ3:- እነዚያ በቡድን ሥራዎች በአሳይመንት መልክ የሚሰሩ ሥራዎች ናቸው:: አንዳንድ ጊዜ ወደ ከተማም ሄደው ሌሎች መምህራንን በመጠየቅ ከቤተ መጻህፍትም በጋራ

በመሆን መረጃዎችን እንዲያሰባስቡ፣ መልሰው ደግሞ በክፍል ውስጥ ያንን እንዲያቀርቡ የሚደረግበት ሁኔታ አለ ::

14. አ:- በክፍል ውስጥ ለሚሰሩ ስራዎች ቡድኖች የሚደራጁት እንዴት ነው ?

መ3:- ቡድኖች የሚደራጁት አብዛኛውን ጊዜ በተማሪዎች ፈቃድ ነው:: በቡድን ሆናችሁ ተነጋገሩ ይባላል:: ግን አንዳንድ አካሄዶች አሉ:: ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ በተለመደው ቡድን ብቻ እንዳይሆኑ፣ አዳዲስ ተማሪዎች ጋር እያቀናጀሁ፣ አንዳንድ ጊዜ ጠንከር ያለ ተማሪን ደግሞ ደከም ካለ ተማሪ ጋር እያቀናጀሁ የሚሰሩበት ሁኔታ አለ::

15. አ:- አቀማመጣቸውስ ?

መ3:-አቀማመጣቸው፣ ያለው ወንበር ለየብቻ የሚቀመጡበት ስለሆነ፣ ክብ ሰርተው እንዲቀመጡ አደርጋለሁ :: በእርግጥ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ 40፣ 50፣55 ትም የሚሆኑበት አጋጣሚ ስላለ ያስቸግራል ::

16. አ:- በአንድ ቡድን ምን ያህል ተማሪዎች ናቸው የሚደራጁት ?

መ3:- በጣም ቢበዛ እስከ አምስት ተማሪ ነው::

17. አ:- ከክፍል ውጭ ለሚሰሩ የቡድን ሥራዎች፣ ቡድኖቹ የሚደራጁት እንዴት ነው?

መ3:- ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው ::

18. አ:- እርስዎ ነዎት የሚያደራጁት ወይስ ተማሪዎች በፍላጎት?

መ3:- እኔም የማደራጅበት ጊዜ አለ፤ ደግሞ ተማሪዎች በምርጫቸው በፍላጎታቸው የሚሰሩበትም ሁኔታም ደግሞ አለ ::

19. አ:- ተማሪዎች በአንድ ቡድን አባልነት ለምን ያህል ጊዜ አብረው ይቆያሉ ?

መ3:- አይ በየጊዜው የሚቀያየር ቡድን ነው የሚሆነው ምክንያቱም እዚህ ቋሚ የሆነ ቡድን የለም እስካሁን ድረስ:: ቋሚ ቡድን የሚባል ነገር የለም:: በየጊዜው ይቀያየራል:: በአንድ ጊዜ ሌላ ቡድን ፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ ቡድን ነው የሚሆነው::

20. አ:- አንድ የቡድን ስራን ለመስራት የቡድን አባላቱ የሥራ ድርሻቸውን የሚከፋፈሉት እንዴት ነው ?

መ3:- ያንን በራሳቸው ስምምነት ነው የሚያደርጉት:: አብዛኛውን ጊዜ በእኔ በኩል የማደረገው ምንድን ነው ፣ ምናልባት ሪፖርቱን ለክፍሉ የሚያቀርበው ተማሪ አንድ መሆን የለበትም ፣ሁልጊዜ አንድ አይነት ሰው ማቅረብ የለበትም:: ዛሬ አቅራቢው አንዱ ከሆነ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላው ያቀርባል:: መረጃ የሚይዝ ይኖራል ፤ የሚያቀርብ ይኖራል:: የሚያወያየው ደግሞ ይኖራል::

21. አ:- ተማሪዎቹ በሙሉ ስለ ቡድን መማር አላማና አሰራር በቂ ግንዛቤ አላቸው ይላሉ?

መ3:- የላቸውም ከማለት አላቸው ማለት የሚቀል ይመስለኛል:: ምክንያቱም አንድ የመማር ማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነ የተረዱ ይመስለኛል::

22. አ:- እርስዎስ ለተማሪዎቹ የቡድን መማር አላማንና በጋራ እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚያስተዋውቁባቸው መንገዶች አሉ ?

መ3:- አዎ ሁልጊዜም ባይሆን እገልፃለሁ::

23. አ:- ተማሪዎች በበድን ስራ ወቅት ማድረግ ያለባቸውና ማድረግ የሌለባቸው ነገሮችን ለማስረዳት የተዘጋጀ መመሪያ አለ?

መ3:- መመሪያ ነገር አንዳንድ ጊዜ ... የተዘጋጀ መመሪያ ነገር አላየሁም:: ግን በቃል ይነገራቸዋል::

24. አ:- በተለይ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ሁሉም የቡድን አባላት እኩል ተሳትፎ የሚያደርጉ ይመስልዎታል?

መ3:- በዚህ ላይ ሁሉም እኩል ይሳተፋል የሚል ግምት የለኝም:: ብዙውን ጊዜ ከዚህ የነሳ ምናልባት ለቡድን ስራዎች የሚሰጥ፣ በተለይ ከማርክ ጋር በተያያዘ የሚሰጠው ነጥብ አናሳ ነው የሚሆነው:: ምክንያቱም፣ ከክፍል ውጭ በሚሰሩበት ጊዜ የተወሰኑት ተማሪዎች ብቻ አብዛኛውን ስራ ይሰራሉ:: ሌሎች ስማቸውን ብቻ ሰጥተው ምናልባት የማይገኙበት ሁኔታም ሊኖር ይችላል በተለይ ከክፍል ውጭ ሲሆን:: ስለዚህ፣ ሁሉም እኩል ይሳተፋሉ ማለት አይቻልም::

25. አ:- ሁሉም በስራው ላይ መሳተፍ አለመሳተፋቸውን የሚከታተሉት እንዴት ነው? መ3:- ያ ምናልባት የቡድን ስራዎች ላይ፣ በፅሁፍ መልክ የሚያቀርቡ ከሆነ፤ የያንዳንዱ አስተዋጽኦ እዚያ ላይ ተጠይቶ እንዲገለፅ እጠይቃለሁ:: የኔ የሚለው የራሱን::

26. አ፡- ተማሪዎች የቡድን ስራዎችን ለመማሪያ ወይም ስራዎቹን በክፍል ውስጥ ለማቅረቢያ፣ የሚረዱ፣ የጽህፈት መሳሪያዎችን የሚያገኙት ከየት ነው?

መ3:- የፅህፈት መሳሪያ እኔ አላቀርብም:: ማቅረብ እንዳለብኝም አላውቅም:: በራሳቸው ነው የሚሰሩት::

27. አ፡- ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰሯቸውን የቡድን ስራዎች ከሰጡ በኋላ፣ እርስዎ በክፍሉ ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ቢዘረዝሩልኝ?

መ3:- በዚያን ጊዜ እየዞርኩ አያለሁ፤ እመለከታለሁ:: እንደሚሳተፉ፣ ምን ምን ተግባራትን እንደሚያከናውኑ፣ አንዳንድ ጊዜ ጥያቄው ወይም የቀረበው ሃሳብ ግልፅ ላይሆን ይችላል:: ግልፅ ካልሆነ ቀርቤ እጠይቅና፣ ማብራሪያ እሰጣለሁ::

28. አ፡- በቡድን አባላት መካከል አለመግባባቶች የሚፈሩባቸው ሁኔታዎች አሉ?

መ3:- እንደዚህ አይነት ነገር አጋጥሞኝም እስከ ዛሬ ይቅርታ አንድ ጊዜ ትዝ ይለኛል፣ሁለት ተማሪዎች አንዱ የኔ ሃሳብ ይቅረብ ይላል፣ ሌላኛው ደግሞ የኔ ሀሳብ ይቅረብ ትላለች:: በዚህ ነው የተጋጩት::

29. አ፡- አለመግባባቶቹ እንዴት?

መ3:- ቡድኑ እንዲፈርድ አድርጌ፣ ሁለቱም በተለያዩ ቡድኖች እንዲሆኑ አድርጊያለሁ::

30. አ፡- የቡድን ስራዎች የሚገመገሙትና ውጤት የሚሰጣቸው እንዴት ነው?

መ3:- ቀድም እንዳልኩት፣ የተወሰኑ ስራዎችን ብቻ ነው ለውጤት፣ ለማርክ የሚሰሩት:: በተለይም በፅሁፍ የሚያቀርቡት ከሆነ፣ የራሳቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ በማድረግ፣ ደግሞ በአጠቃላይ ስራውን በአንድነት በመመልከት ነው ውጤት የምሰጠው::

31. አ፡- ለአንድ የቡድን ሥራ፣ ለአባላቱ በሙሉ ተመሳሳይ ውጤት ነው የሚሰጠው?

መ3:- ለአባላቱ ሁሉ በተመሳሳይ የሚሰጠበት ሁኔታም አለ፤ ደግሞ የያንዳንዱን የግል ስራ የሚታየበትም መንገድ አለ::

32. አ፡- ተማሪዎች የቡድን ሥራዎችን በመለዋወጥ፣ የቢጤ እርማት የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ?

መ3:- አለ ይህንን ዘዴ በጣም እጠቀማለሁ:: ተማሪዎችም በጣም ወደውት፣ ይህንን ስራ ለመስራት ፈቃደኛ ስለሆኑ፣ ያንዱ ስራ ላይ አስተያየት በሚሰጡበት ጊዜ፣በጣም ደስተኛ ሆነው ለማረም፤ ሃሳባቸውን ለመስጠት ይቸኩላሉ::

33. አ፡- የራሳቸውን የቡድን መማር ለውጥንስ እንዲገመግሙ የማድረግ ሁኔታ አለ?

መ3:- እንደ አጋጣሚ ሆኖ እንደዚህ አይነት ተግባር አላደረኩም:: እንዲገመግሙ ዕድል አልሰጠሁም::

34. አ፡- የቡድን መማር ማስተማር ሂደቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች የሚገመግሙት እንዴት ነው?

መ3:- በያንዳንዱ ጊዜ ባላየሁት እንቅስቃሴ አንዳንድ ጊዜ ጥሩ እንቅስቃሴ የማደርግበት ጊዜ አለ:: በተለይም የሚሰጣቸው ይዘት በጣም ግልፅ ከሆነ፤ በጣም ብዙ ተሳታፊዎችን አያለሁ:: አዲስ ሃሳብ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተሳትፎአቸው አናሳ ይሆናል:: እነዚህን ሁኔታዎች አያለሁ:: በእርግጥ የተመዘገቡ እነዚህ የቡድን ስራዎች ከነዚህ የቡድን ስራዎች ለማለት የተመዘገቡ ስራዎች የሉም::

35. አ፡- የራስዎን የማስተማር ሂደት ሪፍሌክት የሚያደርጉበት ሁኔታስ?

መ3:-ይህንን ከተማሪዎቹ አጠቃላይ ሁኔታ ነው:: ለምሳሌ፣ የፅህፈት ክሂል ሊሆን ይችላል፣ የንባብ ክሂል ሊሆን ይችላል፤ የመናገር ክሂል ሊሆን ይችላል:: በያንዳንዱ እንቅስቃሴ የተማሪዎቹን ግላዊ እንቅስቃሴ፣ በግላቸው የሚያሳዩትን ባህሪ በተለያየ ዘዴዎች በመመልከት::

35. አ፡-በመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ፣ የቡድን ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት፤ የጋጠሙዎት ችግሮች ካሉ፣ ዘርዝር አድርገው ቢገልፁልኝ?

መ3:- የተለየ ነገር አላጋጠመኝም:: እንደችግር የምጠቅሰው::

37. አ፡- በአጠቃላይ ስለ ቡድን ማስተማር ዘዴ ያለዎት አስተያየት ምንድነው?

መ3:- የቡድን ማስተማር ጥሩ ነው:: እና ከተጠቀምንበት በጣም ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚረዳ እምነት አለኝ:: ከኮርሶች ባህሪ አንፃር አንዳንድ ኮርሶች በጣም ሰፋፊ ሊሆኑ ይችላሉ:: ሁልጊዜ የቡድን ስራዎችን የምንከተል ከሆነ ደግሞ፣ ምናልባት የተመደበውን የኮርሶቹን ይዘት በተመደበው ጊዜ ለመጨረስ እንቸገር ይሆናል:: ስለዚህ፣ እንደየኮርሱ ባህሪና ጊዜ ተግባራዊ ብናደርገው ለማሪዎቹም ለመምህራኖቹም የተሻለ ነው::

38. አ፡- ውድ ጊዜዎን ሰጥተው፣ ስላደረጉልኝ ትብብር እጅግ በጣም አመሰግናለሁ::

መ3:- እኔም አመሰግናለሁ::

አባሪ 8

የኮሌጁ ስም ...........................

መምህሩ/ሯ/ ...........................

የተማሪ ብዛት ........................... የትምህርቱ /የኮርሱ/ መጠሪያ ...........................

የትምህርት ርዕስ ...........................

ክፍለ ጊዜ የክፍለ ጊዜ መጠን

ቀን ...........................

# የክፍል ውስጥ የንኡስ ቡድን ማስተማር አተገባበር መከታተያ ቅጽ

## Small Group Teaching-Classroom Observation Check list

| የመምህሩ/ሯ/ ተግባራት | ምልከታው ያተኮረባቸው ተግባራት | የምልከታው ወቅት | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | ነበር | አልነበረም | |
| የንኡስ ቡድኖችና የመቀመጫዎች አደረጃጀት | • በየቡድኖቹ የነበረው የተማሪዎች ቁጥር ተገቢ ነበር:: | | | |
| | • ቡድኖቹ የተመሰረቱበት ስልት ተገቢ ነበር:: | | | |
| | • የተማሪዎቹ የቡድን አቀማመጥ ተገቢ ነበር:: | | | |
| | • ክፍሉ ለቡድን አቀማመጥ በሚገባ የተደራጀ ነበር:: | | | |
| | • ተማሪዎች በየቡድኑ የተመቻች ሁኔታ መቀመጣቸውን የመከታተል ሁኔታ ነበር:: | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የቡድን ስራዎች አሰጣጥ | • የዕለቱን የቡድን ስራ የማስተዋወቅ ተግባር ነበር:: | | | |
| | • የቡድን ስራ ትዕዛዝ አሰጣጡ ግልፅ ነበር:: | | | |
| | • ተማሪዎች የቡድን ስራውን መረዳት አለመረዳታቸውን የማረጋገጥ ተግባር ነበር:: | | | |
| | • የቡድን ስራው በምን ያህል ጊዜ መሰራት እንዳለበት የመግለፅ ሁኔታ ነበር:: | | | |
| የቡድን ስራዎች የመከታተል ሁኔታ | • እየተዘዋወሩ የቡድን ስራዎችን የመከታተል ሁኔታ ነበር:: | | | |
| | • ሁሉም ተማሪዎች እኩል እንዲሳተፉ የማያደርግ ጥረት ነበር:: | | | |
| | • ተማዎችን የማበረታታት ሁኔት ነበር:: | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | • ለተማሪዎች የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት ሁኔታ ነበር፡፡ | | | |
| | • ለቡድን ስራዎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን የመስጠት ሁኔታ ነበር፡፡ | | | |
| | • በተማሪዎች የቡድን ስራ ተሳታፊ የመሆን ሁኔታ ይታይ ነበር | | | |
| | • ተማሪዎች ስራዎችን በሰዓቱ እንዲያጠናቅቁ የማሳሰብ ሁኔታ ነበር፡፡ | | | |
| | • ተማሪዎቹ የቡድን ስራ ውጤቶችን እንዲያቀርቡ የማድረግ ሁኔታ ነበር፡፡ | | | |
| | • ለትምህርቱ ማጠቃለያ የመስጠት ሁኔታ ነበር፡፡ | | | |

አባሪ ፱

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በሆሣዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ የሁለተኛ ዓመት የአማርኛ ትምርት ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

ውድ ተማሪ

የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በመሰረታዊ አማርኛ ኮርስ ስለሚከናወነው ቡድናዊ መማር፣ የተማሪዎችን አስተያየት ለመሰብሰብ ነው። አስተያየቱም ለሁለተኛ ( ማስትሬት) ዲግሪ ማሟያ ጥናት በመረጃነት የሚያገለግል ነው። ለጥናቱ መሳካት አንቺ ( አንተ) የምትሰጪው ( የምትሰጠው) አስተያየት ወሳኝ ነው፤ ስለዚህ መጠይቁን በጥንቃቄ እንድትሞይልኝ ( እንድትሞላልኝ) በትህትና እጠይቃለሁ።

ውድ ጊዜሽን ( ጊዜህን) በመስጠት መጠይቁን በመሙላት ስለተባበርሽኝ (ስለተባበርከኝ) ከልብ አመሰግናለሁ።

አጥኚው

መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም

ሚያዚያ 2000 ዓ.ም

ክፍል አንድ

ከቁጥር 1-4 ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መረጃዎችን በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ ፃፊ/ፃፍ/።

1. ፆታ -------------------------
2. ብሔረሰብ -------------------------
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ -------------------------
4. ኃይማኖት -------------------------

ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ለያንዳንዳቸው አምስት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ የምትስማሚበትን/ የምትስማማበትን/ መልስ መርጠሽ/ መርጠህ/ ከጥያቄው ፊት ለፊት ባለው ቦታ የ "✓" ምልክት አድርጊ/ አድርግ/፡፡

አማራጮቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

5. ሁል ጊዜ
4. አብዛኛውን ጊዜ
3. አንዳንድ ጊዜ
2. አልፎ አልፎ
1. በጭራሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማረጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | አብዛኛውን ጊዜ 4 | አንዳንድ ጊዜ 3 | አልፎ አልፎ 2 | በጭራሽ 1 |
| 1. | በክፍል ውስጥ በቡድን በምንቀመጥበት ወቅት፣ የቡድኑ አባላት በሙሉ ፊት ለፊት መተያየት እንችላል፡፡ | | | | | |
| 2. | መምህሩ/ሯ/ በቡድን ተባብሮ መስራት እንዴት እንደሚቻል ትምህርት ይሰጡናል፡፡ | | | | | |
| 3 | የሚሰጡት የቡድን ስራ ትዛዞች ግልጽ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 4 | በቡድን ስራ ወቅት፣ የቡድን አባለት ተቀራርበን ስለማንቀመጥ ለመደማመጥ እንቸገራለን፡፡ | | | | | |
| 5 | መምህሩ/ሯ/ የቡድን ስራ ሲሰጡ ስለ አሰራሩ ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ | | | | | |
| 6 | የሚሰጡት የቡድን ስራዎች የመስራት ፍላጎታችንን የሚያነሳሱ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 7 | በክፍል ውስጥ የሚሰራ የቡድን ስራ ሲሰጠን፣ ስራውን በምን ያህል ደቂቃ መስራት እዳለብን በቅድሚያ ይገለጽልናል፡፡ | | | | | |
| 8 | የሚሰጡት የቡድን ስራዎች የትምህርት ደረጃችንን የሚመጥኑ ናቸው፡፡ | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማረጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | አብዛኛውን ጊዜ 4 | አንዳንድ ጊዜ 3 | አልፎ አልፎ 2 | በጭራሽ 1 |
| 9. | ስለ ቡድን ስራ አሰራር ተማሪዎች ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች መምህሩ/ሯ/ ማብራሪያ ይሰጣሉ:: | | | | | |
| 10 | በክፍል ውስጥ በቡድን በቡድን ሆነ በሚቀመጡ ተማሪዎች መካከል አንደልብ መዘዋወር የሚያስችል ክፍተት አለ:: | | | | | |
| 11 | መምህሩ/ሯ/ የቡድን ስራ ሲሰጡ ለያንዳንዱ የቡድን አባል የየስራ ድርሻውን ያከፋፍላሉ:: | | | | | |
| 12 | የክፍል ውስጥ የቡድን ስራን ለመስራት የሚሰጠው ጊዜ በቂ ነው:: | | | | | |
| 13 | ከክፍል ውጭ የሚሰሩ የቡድን ስራቻችን ለመስራት በቂ ጊዜ ይሰጣል:: | | | | | |
| 14 | ከክፍል ውጭ የሚሰራ የቡድን ስራን አንድ የቡድን አባል ብቻውን ሰርቶ የሚያቀርብበት ሁኔታ አለ:: | | | | | |
| 15 | ውጤት የሚኖረው የቡድን ስራ ሲሰጥ፣ የመገምገሚያ መስፈርቱ በቅድሚያ ይገለጽልናል:: | | | | | |
| 16 | በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የቡድን ስራ ሲሰሩ መምህሩ/ሯ/ ስራዎቹን እየተዘዋወሩ ይከታተላሉ:: | | | | | |
| 17 | መምህሩ/ሯ/ እየተዘዋወሩ የቡድን ስራዎችን በሚከታተሉበት ወቅት ሁሉም ቡድኖች ጋ ይደርሳሉ:: | | | | | |
| 18 | በክፍል ውስጥ የምንሰራውን የቡድን ስራ ከሰጡን በኋላ፣ መምህሩ/ሯ/ ከክፍል ወጥተው ይሄዳሉ:: | | | | | |
| 19 | ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ላይ፣ ሁሉም ተማሪዎች መሳተፍ አለመሳተፋቸውን መምህሩ /ሯ/ ይከታተላሉ:: | | | | | |
| 20 | በቡድን ስራ የማየሳተፉ ተማሪዎች እንዲሳተፉ መምህሩ /ሯ/ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ:: | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማረጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ 5 | አብዛኛውን ጊዜ 4 | አንዳንድ ጊዜ 3 | አልፎ አልፎ 2 | በጭራሽ 1 |
| 21. | ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራወች ላይ ጨርሶ የማይሳተፉ ተማሪዎች አሉ:: | | | | | |
| 22 | በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የቡድን ስራ ሲሰሩ፣ መምህሩ/ሯ/ የግላቸውን ስራ /ፈተና ማረም፣ መጽሃፍ ማንበብ፣ ወዘተ./ ያከናውናል:: | | | | | |
| 23 | መምህሩ ለቡድን ስራ የሚያስፈልጉንን መሳሪያዎች / ቻርት፣ ማርከር፣ ወረቀት ወዘተ/ ለየቡድኖቹ ያከፋፍላሉ:: | | | | | |
| 24 | ከክፍል ወጭ እንዲሰሩ የሚሰጡ የቡድን ስራዎች የሚሰሩት በጥቂት አባላት ብቻ ነው :: | | | | | |
| 25 | በቡድን ስራ ወቅት መምህሩ/ሯ/ ተማሪዎችን ያበረታታሉ:: | | | | | |
| 26 | መምህሩ (ሯ) በቡድን አባላት መካከል መግባባት መኖር አለመኖሩን ይከታተላሉ:: | | | | | |
| 27 | ከቡድን ስራ በኋላ ሁሉም ቡድኖች የስራ ውጤታቸውን የማቅረብ (የማስደመጥ) እድል ያገኛሉ:: | | | | | |
| 28 | ከቡድን ስራ በኋላ መምህሩ/ሯ/ ማጠቃለያ ይሰጣሉ:: | | | | | |
| 29 | መምህሩ/ሯ/ ከክፍል ውጭ በሚሰሩ የቡድን ስራዎች ሁሉም ተማሪዎች መሳተፍ አለመሳተፋቸውን በተለያዩ ዘዴዎች ያረጋግጣሉ:: | | | | | |
| 30 | ቡድኖች ስራቸውን በመቀያየር፣ አንዱ ቡድን የሌላውን ቡድን ስራ እንዲገመግምና አስተያየት እንዲሰጥ ይደረጋል:: | | | | | |
| 31 | ለአንድ የቡድን ስራ ውጤት ሲሰጥ፣ የቡድኑ አባላት በሙሉ አንድ አይነት ውጤትን ያገኛሉ:: | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 32 | ተማሪዎች የቡድን አሰራራቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን እንዲገመግሙ ይደረጋል:: | | | | | |
| 33 | መምህሩ/ሯ/ በቡድን መማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጡ ይጋብዛሉ:: | | | | | |
| 34 | ለአንድ የቡድን ስራ ውጤት ሲሰጥ፣ የቡድኑ አባላት በስራው ላይ እንዳላቸው ተሳትፎ መጠን የተለያዩ ውጤቶችን እንዲያገኙ ይደረጋል:: | | | | | |

## ክፍል ሶስት

**ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ በአጭሩ መልሱ::**

1. አብዛኛውን ጊዜ የአንድ ቡድን አባላት ቁጥር ከስንት እስከ ስንት ነው?

_______________________________________________

2. ከክፍል ውጭ ለሚደረግ የቡድን ስራ፣ ተማሪዎች በአንድ ቡድን ስር የሚመደቡት በምን መስፈርት ተመርጠው ነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

3. የአንድ ቡድን አባላት፣ በአንድ ቡድን አባልነት ለምን ያህል ጊዜ አብረው ይቆያሉ?

_______________________________________________

4. ለቡድን ስራ ውጤት የሚሰጠው እንዴት ነው? በሚሰጠው የቡድን ስራ ውጤት ደስተኛ ነሽ/ነህ/ ምላሹ አዎ ከሆነ ለምን? ምላሹ አይደለሁም ከሆነ ለምን?

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

5. በአጠቃላይ በመሰረታዊ የአማርኛ ኮርስ የቡድን መማር ሂደት ጠንካራና ደካማ ጎኖች ናቸው የምትያቸውን/ የምትላቸውን/ ዋና ዋና ነጥቦች ከዚህ በታች ዘርዝሪ /ዘርዝር/

ጠንካራ ጎኖች:-

---

---

---

ደካማ ጎኖች:

---

---

---

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተገለጸውና የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራ መሆኑን፣ በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎችና ምንጮችም በሙሉ የጠቆምኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም: ዑመር ዳውድ

ፊርማ: [signature]

አድራሻ: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል አዲስ አበባ።

ቀን: 12/10/2000 ዓ.ም.